# ምድብ ስድስት
# የገሊላ አገልግሎቱ
## *ታኅሣሥ 27 ዓ.ም. - ሚያዝያ 29 ዓ.ም.*

---

ኢየሱስ በሰማርያ የቈየው ሁለት ቀን ብቻ ቢሆንም፣ በጣም ብዙ አዝመራ ሰብስቧል:: በገሊላ በእርሱ ያመኑት በቀላሉ የሚመጡ አልነበሩም፤ ሆኖም በይሁዳ ከነበሩት ይልቅ የተሻሉ ተቀባዮች ነበሩ:

ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ስላከናወናቸው ተግባሮች ስናስብ ብዙውን ጊዜ ትዝ የሚሉን በገሊላ ያደረጋቸው ናቸው (ማቴ 4÷12-15÷20፤ ማር 1÷14-7÷23፤ ሉቃ 4÷14-9÷17፤ ዮሐ 4÷46-54፤ 6÷1-71):: ይህ ሰዎች ሊያውቁት የሚገባቸው ኢየሱስ ነው:: በዚህ የተለያዩ ብሔሮች በነበሩበት ገራገርና ገጠራማ አካባቢ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ዐሥራ አንዱን ይጠራል፣ የተራራው ስብከቱን ይሰብካል፣ ታዋቂ የሆኑ አብዛኞቹ ተአምራቱን ያደርጋል፣ በሺዎች የሚቈጠሩትን ይመግባል፣ በውሃ ላይ ይራመዳል፣ ቅፍርናሆምን የአገልግሎቱ «ማዕከል» ያደርጋል ሌሎች አስደናቂ ሥራዎችንም ያደርጋል:: በውበትም ሆነ ፍሬያማነት ገሊላን የሚበልጥ ቢኖር እዚያ ያገለገለው ጌታ ብቻ ነው:: በዮሐንስ ለመጠመቅ ኢየሱስ ገሊላን ለቅቆ ከሄደ ከአንድ ዓመት በላይ ሆኖአል (ማቴ 3÷13፤ ማር 1÷9):: አሁን ደግሞ ከሳምንት እስከ ዘጠኝ ወሮች በይሁዳ ካገለገለ በኋላ፣ ኢየሱስ እንደ ገና ወደ ትውልድ ቦታው ተመልሷል::

**§ 36**
**ኢየሱስ ወደ ገሊላ መመለሱ**
**(ዮሐ 4÷43-45)**

43ከሁለቱ ቀናት በኋላም ወደ ገሊላ ሄደ፤
44ነቢይ ገበዛ አገሩ እንደማይከበር ኢየሱስ ራሱ ተናገሮ
ነበርና:: 45ገሊላ እንደ ደረሰም የገሊላ ሰዎች በደስታ
ተቀበሉት፤ ምክንያቱም፣ እነርሱም በፋሲካ በዓል
ኢየሩሳሌም ስለ ነበሩና በዚያ ያደረገውን ሁሉ ስላዩ ነው::

«ነቢይ በገዛ አገሩ ስለማይከበር» (ሉቃ 4÷24)፣ ቤተ መቅደሱን በማንጻቱ ብቻ ሳይሆን (ዮሐ 2÷13-22)፣ ሌሎች ብዙ ተአምራቶችን በማድረጉ ኢየሱስ መጀመሪያ ታዋቂነትን ያገኘው በይሁዳ ነበር (ዮሐ 2÷23፤ 3÷26፤ 4÷1):: ከሐና ጭፍሮች ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጦ ሲያሸንፍ ከእነዚህ ገሊላውያን አብዛኞቹ በበዓሉ ቦታ እንደ ነበሩ የሚጠረጠር አይደለም:: የአካባቢው ጀግና ሆኖ መታየት ይጀምራል:: አንድ ትንሽ የገጠር ልጅ ወደ ትልቁ ከተማ በመሄድ ታላላቅ የተባሉትን ሁሉ ልክ ያስገባቸዋል:: በእርግጥም የገሊላ ሰዎች ዮሐንስ ከጠቀሳቸው ከመጀመሪያዎቹ አማኞች (ዮሐ 2÷3) መካከል ሊሆኑ ይችሉ ነበር:: አሁን መጠነኛ ዝና ይዞ ወደ ገሊላ መምጣቱ፤ የገዛ ሕዝቡ ሊቀበሉት ፈቃደኞች ነበሩ:: [ማሳሰቢያ:- ኢየሱስ የገሊላ ሰው በመባል ይታወቅ ነበር - ዮሐ 1÷46፤ 7÷41-52፤ ሉቃ 23÷5-7::]

ይሁን እንጂ ኢየሱስ፣ በትውልድ አገሩ በናዝሬት አንድ ነገር ለመጀመር ዝግጁ አልነበረም (ማቴ 13÷58፤ ሉቃ 4÷22-31):: እንዲያውም ወደ ገሊላ በተመለሰበት በሁለቱም ጊዜ ኢየሱስ በመጀመሪያ በቃና በሰርግ ግብዣ ላይ (ዮሐ 2÷1-11)፣ በኋላም የሹሙን ልጅ በመፈወስ አገልግሏል (ዮሐ 4÷46-54):: በተጨማሪም ወደ ናዝሬት ከመመለሱ ቀደም ሲል (ዮሐ 4÷16-31) ኢየሱስ በገሊላ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ያገለግል እንደ ነበር ሉቃስ 4÷15 ፍንጭ የሚሰጥ ሐሳብ ያቀርባል:: በኢየሱስ የገሊላ አገልግሎት ከቃና (ዮሐ 4÷45-54)፣ ወደ ናዝሬት (ሉቃ 4÷16-13)፣ ወደ ቅፍርናሆም (ማቴ 4÷13-17፤ ሉቃ 4÷31) ያደረገውን ዝውውር መመልከት ይቻላል::

**§ 37**
**የኢየሱስ የገሊላ አገልግሎት ባሕርይ**
**(ማር 1÷14-15፤ ከማቴ 4÷17፤ ሉቃ 4÷14-15 ጋር)**

[17ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ፣ መስበክ ጀመረ
ማቴ] 14የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ፤... 15ጊዜው
ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት [መንግሥተ ሰማይ ማቴ]
ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ እያለ ይሰብክ
ነበር:: ...

14ዝናውም በአካባቢው ባለው አገር ሁሉ ወጣ:: 15እርሱም በምኩራቦቻቸው
ያስተምር ነበር፤ ሰውም ሁሉ ያመሰግነው ነበር::

በክፍል 34 ኢየሱስ ይሁዳን ትቶ የወጣው በሦስት ምክንያቶች እንደ ነበር ተመልክተናል፤ እነርሱም (1) የፈሪሳውያን ፓለቲካዊ ተፅዕኖ (ዮሐ 4፥1)፣ (2) መጥምቁ ዮሐንስ በሄሮድስ ታስሮ ወህኒ ቤት መጣሉ (ማቴ 4፥12፤ ማር 1፥14፤ ሉቃ 3፥19-20)፣ (3) ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መመራቱ (ሉቃ 4፥14) ናቸው:: እዚህ ላይ ዮሐንስ ሦስቱ ተነጻጻሪ ወንጌሎች ባቀረቡት ላይ ሁለት በጣም አስፈላጊ ግንኙነቶችን ማለትም ስለ ሳምራዊቷ ሴት (ዮሐ 4፥5-42) እና ስለ ሹሙ ልጅ (ዮሐ 4፥46-54) ጨምሯል:: እነዚህ ትረካዎች የሚያመለክቱን ኢየሱስ ወደ ገሊላ በመጣበት ጊዜ ሃይማኖተኞቹን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ዓይነት ሰዎች ማገልገሉን ነው::

ከኢየሱስ ቀደም ያለው የስብከት አገልግሎት ሁለት ነገሮች ይገርሙናል:: የመጀመሪያው፣ መልእክቱ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ከሚለው ከመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ነው:: መልእክቱ በጣም ቀላልና ደስታን አብሣሪ ነበር:: የእግዚአብሔር አገዛዝ የሰዎችን ክልል ዘልቆ እየገባ ነው የሚል «የምሥራች» (በግሪክ «ኀስፐል») ነበር:: ሁለተኛው አስገራሚ ነገር ደግሞ ሰዎች በጉጉት ኢየሱስን መቀበላቸው ነበር:: የገሊላ ሰዎች ወደውታል:: ከአንዱ ምኩራብ ወደ ሌላው ምኩራብ እየተሸጋገረ ስለ ኢየሱስ ያለው አድናቆት ወደ ገጠራማው ማኅበረ ሰቦች ዘለቀ::

**§ 38**
**ኢየሱስ በቃና የሹሙን ልጅ በቅፍርናሆም መፈወሱ**
**(ዮሐ 4፥46-54)**

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የታወቀውን ሁለተኛ ተአምር አደረገ:: አሁንም ተአምራቱን ያደረገው የናትናኤል ትውልድ ቦታ በነበረው በገሊላ ቃና ነበር:: ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህንን ታምራት ከመቶ አለቃው አገልጋይ ፈውስ ጋር



ያነጻጽሩታል (ማቴ 8፥1:5-13፤ ሉቃ 7፥1-10)::[1] የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ነገሮች አሉ፣ (1) ኢየሱስ ውድ የሆነ ልጅን/አገልጋይን እንዲፈውስ ልመና ቀረበለት:: (2) ኢየሱስ ታምራቱን ያደረገው ሩቅ ቦታ ሆኖ ነበር:: (3) ሁለቱም ታምራቶች የተደረጉት በቅፍርናሆም ነበር:: ሆኖም፣ በርካታ ልዩነቶችም አሉ፤ (1) ኢየሱስ በቅፍርናሆም ሳይሆን በቃና ነበር (ሉቃ 7፥1):: (2) ሹሙ ኢየሱስ ወደ ቤቱ እንዲመጣ ሲጠይቅ፣ መቶ አለቃው ግን ወደ ቤቱ መምጣቱን አልፈለገም:: (3) የአይሁድ ሽማግሌዎች የአሕዛብ ወገን ስለ ሆነው ስለ መቶ አለቃው ኢየሱስን ማለዱ:: (4) ኢየሱስ የመቶ አለቃውን እምነት ሲያደንቅ፣ ሹሙን ግን ምልክት በመጠየቁ ነቅፎታል:: ምንም እንኳ ሁለቱ ታሪኮች ተመሳሳይ ቢመስሉም አጠቃላይ ሁኔታቸው፣ የተከናወኑበት ጊዜና ዓላማቸው ግን የተለያዩ ናቸው:: መቶ አለቃውን በተመለከተ የተነገረው ታሪክ ዓላማ በኢየሱስ ላይ የነበረውን ትልቅ እምነት ማሳየት ነበር:: ሹሙን በተመለከተ የተነገረው ታሪክ ዓላማ ግን እያደገ የመጣውን የኢየሱስን ታዋቂነትና ተአምራቱ በሕዝቡ ላይ ያሳደረውን እምነት ማሳየት ነበር::

**ዮሐ 4፥46-48**

46ኢየሱስ ውሃውን የወይን ጠጅ ወዳደረገበት፣
በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ቃና ደግመኛ መጣ፤
በቅፍርናሆምም ልጁ የታመመበት አንድ የቤተ መንግሥት
ሹም ነበረ፤ 47ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
መምጣቱን በሰማ ጊዜ፣ ወደ እርሱ ሄዶና በሞት አፋፍ
ላይ የነበረውን ልጁን መጥቶ እንዲፈውስለት ለመነው::
48ኢየሱስ «መቼውንም እናንተ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ
አታምኑም» አለው::

---

[1] አርጌነስን፣ ዮሐንስ አፈወርቅን፣ (Chrysostom)፣ ኤሬንየስና አውሳቤዎስን የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ ያዘጋጁ ታላላቅ ምሁራን እንኳ ቢያንስ በከፊልም ቢሆን እነዚህ ሁለት ታሪኮች እንደ አንድና ተመሳሳይ እንደሆኑ አድርገው አቅርበዋል::

ይህ የቤተ መንግሥት ሹም የሄሮድስ አንቲጳስ አገልጋይ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል:: የሄሮድስ አገልጋይን አስመልክቶ ጆሴፈስ ይህንኑ ቃል ስድስት መቶ ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምናልባትም ከዚህ ሰው ጋር ሲያገለግሉ የነበሩ ኩዛን፣ (ሉቃ 8÷3) እና ምናሔን (ሐሥ 13÷1) የመሳሰሉ ሌሎች የሄሮድስ ሹማምንት አገልጋዮችን ተጠቅሰው እናገኛለን:: «ይህ ባለሥልጣን ከአሕዛብ ወገን ሊሆን ይችላል:: እንደዚያ ከሆነ በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ ኢየሱስ ያነጋገራቸው ሰዎች አይሁድን፣ ሳምራውያንና አሕዛብን በአጭር ቃል ለማዳን የመጣውን ዓለም ይወክላሉ ማለት ነው» (Tenney, p. 60):: ሰውየው ማንም ይሁን ማን ዝነኛው መምህር በጸሎት የበረታ ነው የሚለውን ባሕላዊ አባባል መሠረት በማድረግ እርምጃ እየወሰደ ነበር:: ይሁን እንጂ የሹሙ እምነት ለፈውስ ጸሎት እንዲደረግ ከመጠየቅ ያለፈ እንደ ነበር እንገነዘባለን:: ኢየሱስ ወደ ቤቱ እንዲመጣና ተአምር አድራጊ ሆኖ እንዲቀርብ ነበር የጠየቀው::

ለጥያቄው ምላሽ ሲሰጥ ኢየሱስ ይህን ሰውና ሌሎችንም ምልክት በመጠየቃቸው (የብዙ ቍጥር መሆኑን ልብ ይሏል) ገሥጾአቸዋል:: ተአምር ናፋቂዎችን ለመውቀስና ለመገሥጽ ለኢየሱስ ይህ የመጨረሻው ጊዜ አልነበረም (ማቴ 11÷20-24 ጋር ያነ):: ኢየሱስ በእርሱ እንድናምን የሚፈልገው ከማንነቱ የተነሣ እንጂ ስለሚያደርገው ነገር አይደለም (ዮሐ 10÷38፤ 14:11፤ 15÷22-24፤ 20÷29):: ተአምራት የኢየሱስ ማንነት ማረጋገጫዎች ናቸው:: ሌላው ቀርቶ የመጥምቁ ዮሐንስን እምነት ለማጽናት እንኳ አስተዋፅዖ አድርገዋል (ማቴ 11÷4-5)፣ ሆኖም ዘወትር አስደናቂ ነገሮችን የሚፈልጉ ሰዎችን ማርካት ወይም ለኢየሱስ መገዛት የማይፈልጉ ሰዎችን ማሳመን ግን አይችሉም (ማቴ 12÷38-45):: በሰማርያ በነበረችው በሲካር በነበረ ጊዜ ሰዎች ቃሉን በመስማት ብቻ ወደ እርሱ መምጣታቸውና አሁን ግን የገዛ



ወገኖቹ የሆኑት ገሊላውያን አስደናቂ ትዕይንት እንዲያሳያቸው መጠየቃቸው ምን ያህል የኢየሱስን ልብ አሳዝኖ ይሆን?

ኢየሱስ ይህን እምነት የጐደለውን ምስኪን ሰው የገሠጸው ለምን ነበር? አነጋገሩ ትንሽ ኮስተር ያለ አይመስላችሁም? እንዲያውም ልጁ ሞት አፋፍ ላይ ስለ ነበር፤ ወደ ኢየሱስ የመጣው መለኮታዊ ረድኤት ለመጠየቅ ነበር:: ሆኖም እምነቱ በሁለት አንጻር የተሟላ አልነበረም:: መጀመሪያ፣ ኢየሱስ ልጁን ለመፈወስ ወደ ቤቱ እንደ መጣ አስቦ ነበር:: ሁለተኛ፣ ኢየሱስ ልጁን ከሞት ማስነሣት ሳይሆን መፈወስ ብቻ እንደሚችል ነበር ያመነው:: ኢየሱስ የገሠጸው ይህን ሰው ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቡንም ጭምር መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል:: ምናልባትም ከሁኔታቸው እንደሚነበበው ኢየሱስ ሌላ ምልክት ሊያሳይ ነው በማለት ተደስተው ይሆናል:: በኢየሱስ ላይ ጠንከር ያለ ትችት ከመሰንዘራችን በፊት ልጁን እንደ ፈወሰው መገንዘብ አለብን!

**ዮሐ 4÷49-54**

49ሹሙም፣ «ጌታዬ ልጄ ከመሞቱ በፊት እባክህ
ድረስልኝ» አለው::
50ኢየሱስም፣ «ልጅህ በሕይወት ይኖራልና ሂድ» አለው፡
ሰውዬውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አምኖ ሄደ፤ 51በመንገድ ላይ
እንዳለም፣ አገልጋዮቹ አግኝተውት ልጁ በሕይወት መኖሩን ነገሩት::
52እርሱም ልጁ በስንት ሰዓት እንደ ተሻለው ሲጠይቃቸው «ትኩሳቱ የለቀቀው
ትናንት በሰባት ሰዓት ላይ ነው» አሉት::
53አባትዬውም ሰዓቱ ኢየሱስ፣ «ልጅህ በሕይወት ይኖራል» ያለበት ሰዓት
መሆኑን ተገነዘበ፤ እርሱና ቤተ ሰቡም ሁሉ አመኑ::
54ይህም፣ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረገው ሁለተኛው ታምራዊ
ምልክት ነው::

ይህ ሹም እየተጣደፈና እርዳታ እየለመነ ነበር። ኢየሱስም ይጣደፍ ለነበረው አባት ምላሽ ሰጠ። ልጁን አርባ አራት ኪ.ሜ. የሚያህል ርቀት ላይ ሆኖ ፈወሰ። በተመሳሳይ መልኩ ሹሙ ለኢየሱስ ምላሽ ሰጠ። ኢየሱስ የነገረውን አምኖ፣ ወደ ቅፍርናሆም ጉዞ ጀመረ።

ልጁ ሰባት ሰዓት ላይ ትኩሳቱ ለቀቀው። አገልጋዮቹ ሌሊቱን ያሳለፉት ዓይኖቻቸውን ከእርሱ ላይ ሳያነሡ ነበር። ሲነጋ ልጁ ደኅና እንደሚሆን ግልጽ ነበር። አገልጋዮቹ በጣም ከመደነቃቸው የተነሣ ጌታቸው ወደ ቤት እስኪመጣ ድረስ እንኳ መታገሥ አልቻሉም። እርሱን ለማግኘት ግማሽ መንገድ ያህል ሄዱ። ይህ በዚህ እንዳለ ሹሙ በቃናና በቅፍርናሆም መካከል ባለው የአርባ አራት ኪ/ሜ ርቀት ሌሊቱን አንድ ቦታ አሳልፎ ነበር።[2] በማግሥቱ የተወሰነ ሰዓት ላይ ደስ እያላቸው ወደ እርሱ እየመጡ የነበሩትን አገልጋዮቹን አገኛቸው። የምሥራች ይዘው መጥተዋል! ልጁ ተፈውሷል። አባትዬው ትኩሳቱ በስንት ሰዓት እንደ ለቀቀው አረጋገጠ። ጊዜው ኢየሱስ ልጁ ተፈውሷል በማለት ከተናገረበት ሰዓት ጋር በትክክል የሚጣጣም ነበር።

ይህ በሽታው በአካል ውስጥ ሳይሆን በአስተሳሰቡ ብቻ ነው ወይም አጋጣሚ ነው ሊባል አይችልም። እርሱ ብቻ ሳይሆን ቤተ ሰቡ በሙሉ አመነ። (ስለ መላ ቤተ ሰብ በእምነት መለወጥ ስለሚናገሩ ጥቅሶች:- ሐሥ 10÷23-26፤ 16÷14-15:34፤ 18÷8 ጋር ያነ)።

---

[2] ሰባት ሰዓት ስለ ነበርና ከቅፍርናሆምም አርባ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ብቻ ስለ ነበር፣ ይህ አባት ልጁ በተፈወሰ ቀን እንዴት እቤቱ እንዳልደረሰ የሚገርም ነው። ምናልባት በኢየሱስ ኀይል በጣም ከመተማመኑ የተነሣ ረጋ ብሎ ወደ ቤቱ መመለስ ፈልጎ ይሆናል። ምናልባትም አገልጋዮቹ መንገድ ላይ ያገኙት ምሽት ላይ በመሆኑ፤ ፀሐይ ጠልቃ ስለ ነበር እንደ አዲስ ቀን ቆጥረውት ይሆናል። ይሁን እንጂ ይበልጥ አሳማኙ ሹሙ በሆነ ምክንያት መንገድ ላይ ዘገዬ የሚለው ነው።



**§ 39**
**ኢየሱስ በናዝሬት ተቀባይነት ማጣቱ**
**(ሉቃ 4÷16-31)**

ኢየሱስ በዚህን ጊዜ ለአንድ ዓመት ያህል ናዝሬት አልነበረም። በዮሐንስ ተጠመቀ፤ በሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀንና ሌሊት በምድረ በዳ አሳለፈ፤ የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ተከታዮች አስከተለ፤ በቃና ተአምር አደረገ፤ በፋሲካ በዓል ሰሞን ቤተ መቅደሱን አነጻ፤ በርካታ ተአምራቶችን አደረገ፤ ደቀ መዛሙርትን ሲያሰባስብና በይሁዳ ሲያጠምቅ ከስምንት እስከ ዘጠኝ ወሮች አሳለፈ። አሁን ደግሞ ወደ ቤቱ ባይሆንም ወደ ትውልድ አገሩ እየተመለሰ ነው። የስብከት አገልግሎቱ የሹሙን ልጅ የፈወሰበትን ቃናን ጨምሮ በአንዳንድ ከተሞችና ምኩራቦች እንዲጓዝ አድርጎታል። ስብከት የተወደደ አገልግሎት ነው፤ የተወደደ ሰባኪ ደግሞ ተከታዮች ይኖሩታል። ኢየሱስን በተመለከተም የሆነው ይሄው ነበር። አጠያያቂነቱ በአካባቢው ሁሉ እየተስፋፋ ነበር።

አሁን ደግሞ፣ ወዳደገበት (ቍ 16) እንዲያውም በ«እንክብካቤ» ወደተያዘበት ከተማ ተመለሰ። በዚህ ከተማ ማደግ ብቻ ሳይሆን ምቾት፣ እንክብካቤና ብስለትም አግኝቷል። ትምህርት ቤት የገባው፣ ሙያም የተለማመደውና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ወዘተ ያደረገው እዚህ ነበር። እያደገ የመጣ የከተማይቱ ልጅ ነበር።

**ሉቃ 4÷16-21**

16ከዚያም ወዳደገበት ከተማ ወደ ናዝሬት
መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ወደ ምኵራብ ገባ፤
ሊያነብም ተነሥቶ ቆመ። 17የነቢዩ ኢሳይያስ ጥቅልል
መጽሐፍም ተሰጠው፤ ጥቅልሉንም መጽሐፍ በተረተረው
ጊዜ እንዲህ ተብሎ የተጻፈበትን ክፍል አገኘ፤
18«የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤
ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣
እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣

ስታወሯት ማየትን እንዳውጅ፣
የተጨቁኑትን ነጻ እንዳወጣ፣
[19]የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል።»

[20]ከዚያም መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገልጋዩ መልሶ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኩራብ የነበሩትም ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር። [21]እርሱም፣ «ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ» ይላቸው ጀመር።

ኢየሱስ በየሳምንቱ በምኩራብ አምልኮ ውስጥ የመገኘት ልማድ ነበረው። ወደ ትውልድ ቀዬው በተመለሰ ጊዜ እርሱን ምኩራብ ውስጥ ማየት ብዙ የሚገርም አይሆንም። የሰዎች ሁሉ ዓይን በእርሱ ላይ ነበር። ኢየሱስ ምን ያህል ጉበዝ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ እንደ ነበር ሽማግሌዎቹ ሳያሰላስሉ እንዳልቀሩም መገመት ይቻላል። እንደ ደንቡ ኢየሱስ የዕለቱ ተጋባዥ ሰባኪ መሆን ነበረበት።

ከአይሁድ ባሕል አንጻር ይሄ ሁሉ የተለመደ ነገር ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ ሰባኪው ተነሥቶ ይቆማል፤ ከዚያ በኋላ ሕዝቡን ለማስተማር ይቀመጣል። ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነበር (ቊ 16፣20፤ ማቴ 5÷1፤ ማር 4÷1፤ ዮሐ 8÷2 ጋር ያነ)። ከዚህም በላይ፣ ማንኛውም የምኩራብ አገልግሎት ሁለት ክፍሎች ነበሩት፤ ቅዳሴና ትምህርት። ቅዳሴው ተከታታይ ጸሎቶችንና የቃል ንባቦችን የያዘ ሲሆን፤ ከዚያም ትምህርት በማቅረብ ይጠቃለላል። ትምህርቱ እያንዳንዱ ከሦስት ያላነሱ ጥቅሶች ያልበለጠ ያሉባቸው ሰባት ተከታታይ ንባቦችን የያዘ ሲሆን፣ ከዚያ ስብከት ይከተላል። የሙሴ ሕግ ንባብ የሦስት ዓመት ዑደት የተከተለ ነበረ። ከነቢያት መካከል መምረጥ ግን የሰባኪው ፈንታ ሳይሆን አይቀርም (Nolland, p. 194)። ስለዚህም ኢየሱስ ለስብከቱ የሚሆነውን ክፍል መረጠ።

ስብከቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ያገናዘበ፣ እጥር ምጥን ያለና ከሥነ ጽሑፋዊ ይዘቱ አንጻር ማራኪ እንዲሆን ይጠበቅ ነበር።



ከዚያ በኋላ ደግሞ ሕዝቡ ለሰባኪው ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ይፈቀድላቸዋል። እንደ ደንቡ ከሆነ የስብከት አገልገሎት የሚሰጠው በዚሁ ሙያ ለሠለጠነ መምህር ቢሆንም፣ ኢየሱስን የመሰለ የተከበረ እንግዳም ንግግር እንዲያደርግ ሊጠየቅ ይችላል።

ኢየሱስ የመረጠው ምንባብ ኢሳይያስ 61÷1-2 ያለውን ነበር። የመሲሑን አገልግሎት በሚገባ የሚገልጥ ነበር። እንዲያውም «መቀባት» የሚለው ቃል «መሲሕ» የሚለው የተገኘበት ሥርወ ቃል ነው። ኢየሱስን ሲያደምጡ የነበሩት ሁሉ ይህን አያጡትም።

አገልግሎቱ በበርካታ መንገዶች ተገልጿል

(1) በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ/የተሞላ ነበር

(2) የታሰሩትን የሚፈታ ነበር - ቃል በቃል ሲወሰድ፣ «ተሰባብረው የደቀቁትን»። ኢየሱስ ካለባቸው ጭቈና የተነሣ የተሰባበሩ ሰዎችን ይፈታል። ለተጐዱት አዛኝና ሩኅሩኅ ነው። ኢሳይያስ 61÷2 በማከል፣ «የሚያለቅሱትን ሁሉ እንዳጽናና» ይላል።

(3) ተአምራትን የሚያደርግ - ዕውራንን የሚያበራ ነው።

(4) ጌታ የወደደውን የሚያውጅ ነው - ቃል በቃል፣ «ጌታ የወደደውንና የተቀበለውን» ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው ነገሮች ሁሉ ወደ መጀመሪያ ባለቤታቸው የሚመለሱበትን ወይም ተፈትተው የሚሄዱበትን የኢዮቤልዩ ዓመት ነው። በየሃምሳ ዓመቱ የሚከበረው የኢዮቤልዩ ዓመት ኢየሱስ በቀራንዮ ለእኛ ያደረገውን የሚያመለክት ተምሳሌት ነው። ኢዮቤልዩ መሲሐዊ አገዛዝ ነው።

ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር (ቊ 20)። በሌላ በኩል የዚህ ቃል ሌሎች አጠቃቀሞች ከፍተኛ ስሜትን ያመለክታሉ። ሰዎች ጥሩ

ስብከት ይወዱ ነበር:: ከእዚያ ተለይቶ በነበረባቸው ጥቂት ወሮች ኢየሱስ እንደ ሰባኪ ከፍ ያለ ዝና አትርፎ ነበር:: እርሱ መሲሕ የመሆኑ ወሬ በየአቅጣጫው መናፈስ ጀምሮ ነበር:: እርሱስ ምን ይል ይሆን? በዚያ ጉባኤ ታላቅ ናፍቆት፣ ትዕቢት፣ ቅንዓት፣ ወዳጅነትና የበላይነት ስሜት ተደበላልቀው ነበር:: ለዘመናት ሲናፍቁ የኖሩትን ኢየሱስ በግልጽ በሚጋፈጥበት ወቅት የሚሆነውን ልብ አድርጉ::

ኢየሱስ ጥቅልሉን ለአስተናጋጁ[3] መልሶ ሰጠና ማስተማር ጀመረ:: «ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ» አላቸው (ቊ 21):: «ተፈጸመ» የሚለው ቃል ያለቀና የተጠናቀቀ ነገርን ነው የሚያመለክተው:: ይህ ትንቢት እነርሱ እየተመለከቱ ሳሉ አልተፈጸመም ቀደም ብሎ ግን ተፈጽሞ ነበር፤ አሁንም በኢየሱስ በኩል ፍጻሜውን በገሃድ እያዩ ነበር:: ለእነዚያ ምስኪን የናዝሬት ሰዎች ይህ ዓይነቱ የድፍረት አነጋገር ምን ያህል አነጋጋሪ እንደሚሆን መረዳት አንችልም:: ይህ የስብከቱ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ብቻ ነበር:: የተቀረው ግን በአሳዛኝ ሁኔታ ሳይተላለፍልን ቀርቷል::

22ሁሉም ስለ እርሱ በበጐ ይናገሩ ነበር፤ **ሉቃ 4÷22-27**
ደግሞም ከአንደበቱ በሚወጣ የጸጋ ቃል እየተገረሙ፣
ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን?» ይሉ ነበር::
23እርሱም፣ «ባለ መድኃኒት ሆይ፣ ራስህን ፈውስ፤ በቅፍርናሆም ስታደርግ
የሰማነውን ነገር እዚህ በራስህ ከተማ ደግሞ አድርግ» የሚለውን ምሳሌ
እንደምትጠቅሱብኝ ጥርጥር የለውም» አላቸው::
24ደግሞም እንዲህ አላቸው፣ «እውነት እላችኋለሁ፤ ነቢይ በገዛ አገሩ
አይከበርም:: 25ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ተዘግቶ

[3] ካዛን (*Chazzan*) በመባል ይታወቅ የነበረው ይህ ሰው ደመወዝ የሚከፈለው የምኵራብ ሠራተኛ ነበር:: በዘመናችን አነጋገር በሰባኪውና በጽዳት ሠራተኛው መካከል የሚሆን ሰው ነበር:: ጥቅልል መጻሕፍቱን ጨምሮ ቅዱሳን አገልግሎቶችን ማስፈጸምና ንዋየ ቅዱሳቱን መጠበቅ የእርሱ ኀላፊነት ነበር::



ጽኑ ራብ በምድሪቱ ሁሉ ላይ በነበረበት በኤልያስ ዘመን፣ ብዙ መበለቶች በእስራኤል
ነበሩ፤ 26ኤልያስ ከእነዚህ መካከል ወደ አንዷም አልተላከም፤ ነገር ግን በሲዶና አገር
በሰራጵታ ወደ ነበረችው መበለት ተላከ:: 27በነቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም በእስራኤል ብዙ
ለምጻሞች ነበሩ፤ ነገር ግን ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር ከእነዚያ መካከል ማንም
አልነጻም::»

*27 የግሪኩ ቃል ከለምጽ (የሥጋ ደዌ) ጋር ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የቆዳ በሽታዎችም ጋር በተያያዘ ይጠቀሳል::*

አዲሱ መደበኛ ትርጒም ቊጥር 22ን፣ «ሁሉም ስለ እርሱ በበጐ ይናገሩ ነበር» በማለት ማብራሪያዊ ትርጒም ሰጥቶታል:: ቃል በቃል ሲወሰድ ሉቃስ፣ «ይመሰክሩለት ነበር» ነበር ያለው:: «መመስከር» (ማርትየሮ - *martyreo* የሚለው የግሪክ ቃል) በትክክል «በጐ መናገር» ማለት ሳይሆን፣ «አማኝ መሆንን» ነው የሚያመለክተው:: በተለይ ደግሞ፣ እውነተኛ እምነትን[4] ከማመልከት የጐደለ ሃሳብ ካለው «መደነቅ» ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ መቅረቡ የዚህን ትርጒም እውነትነት ያሳያል:: እንግዲህ እዚህ ላይ ዋናው ሐሳብ እነዚህ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ይነጋገሩ ነበር እንጂ በእርሱ አላመኑም ነበር:: በስብከት ችሎታው ተደንቀዋል፤ ይሁን እንጂ ያቀርብ የነበረው መልእክቱ አስቆጥቷቸዋል:: ይህ ራሱ «ምስክርነታቸው» ምን ያህል ፈጥቶ ወደ ጠላትነት እንደሚለወጥ አመልካች ነው (ቊ 28-29)::

«ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን?» አዎን ነገሩ እንደዚያ ነው፤ ማንም ያንን ያውቃል! ይህንን ሰው ያውቁታል:: የሚናረገው ሁሉ

[4] John Nolland, "Impressed Unbelievers as Witnesses to Christ," *JBL* 98/2 (1979): 219-229). ኢየሱስን በተመለከተ የማያምኑ ሰዎችንም ምስክርነት ሉቃስ በተደጋጋሚ ይጠቅስ እንደ ነበረም አመልክቷል (ገጽ 226):: እንደ ዘበት እነዚህ «ከውኹንብር የጸዱ» የኢየሱስ ኃይለኛ ስብከት ምስክር በመሆን ያገለግላሉ::

በእርግጥም መልካም ይመስላል:: ይህን ሁሉ ጥበብ በድንገት ከወዴት አገኘው?

በዚህን ጊዜ ኢየሱስ፣ «ባለ መድኀኒት ሆይ፣ ራስህን ፈውስ» (ቍ. 23) የሚለውን እውቅ ምሳሌ አስታወሳቸው:: ኢየሱስ በቅፍርናሆም በርካታ ተአምራቶች ሳያደርግ አልቀረም የአገሬው ሰዎች ደግሞ እነዚያን ተአምራቶች በድጋሚ እንዲያደርግ ፈልገው ነበር:: አንድ ቧንቧ ሠራተኛ የሚያንጠባጥብ ቧንቧ፣ ሜካኒክም ልትነዳ የማትችል መኪና ሊያጋጥማቸው መቻሉ የተለመደ ነው:: እነርሱ ሙያቸውን በሌሎች ስፍራዎች እንደሚገባ ያከናውናሉ:: የዚህ ምሳሌ መሠረታዊ ሐሳብ ይኸው ነው:: ሕዝቡ፣ «በሌሎች ከተሞች እነዚህን ግሩም ተአምራቶች ሁሉ አድርገሃል፣ በዚህ ባደግህበት አገርስ የማታደርገው ለምንድነው?» እንደሚሉት ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ:: ለመጨረሻ ጊዜና በድጋሚ ኢየሱስ ወደ ናዝሬት በተመለሰ ጊዜ መልሱ ተሰጥቷል፤ ባለማመናቸው ምክንያት እዚያ ብዙ ታምራቶችን አላደረገም (ማር 6÷5-6)::

ይህ በመስቀሉ ግርጌ በማሾፍ መንፈስ ይጮኽ የነበረ የሕዝብ አጀብ ያስታውሰናል:: «ሌሎችን አዳነ፤ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ እርሱ ከሆነ፣ እስቲ ራሱን ያድን» ይሉ ነበር (ሉቃ 23÷35):: ወታደሮቹም፣ ሌላው ቀርቶ ከእርሱ ጐን ተሰቅሎ የነበረው ወንጀለኛ እንኳ ተመሳሳይ ነገር እየተናገረ ነበር (ሉቃ 23÷36-39):: ይህ ሁሉ በመዝሙር 22÷8 በትንቢት ተነግሮ ነበር::

ኢየሱስ የእነርሱን አባባል በራሱ አባባል በመመለስ (ቍ. 24)፣ ነቢይ በገዛ አገሩ አይከበርም አላቸው:: የምሳሌው እውነተኛነት የእነርሱን ሐሰተኛነት ያሳያል:: ፍቅር ከቤት ይጀምራል የሚለውን አባባል ያጸናሉ:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ወደ እነርሱ ፍቅር ይዞ መምጣቱ እውነት ቢሆንም፤ እነርሱ ግን ፍቅሩን መቀበል አልፈለጉም:: ኢየሱስ በገዛ ወገኖቹ የተገፋው ምን ያህል ጊዜ ነው? «ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤



የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም» (ዮሐ 1፡11):: ዮሐንስ ይህን ምሳሌ ኢየሱስ ወዲያውኑ ወደ ናዝሬት ለምን እንዳልተመለሰ ለመግለጽ ተጠቅሞበታል (ዮሐ 4÷43-45):: ኢየሱስ ይህን መናገር ብቻ ሳይሆን በሁለት ታዋቂ ነቢያት (ቍ. 25-27) ማለትም በኤልያስና በኤልሳዕ ሕይወት ዘመን የተከናወኑ ሁነቶችን በማንሣት ይህንኑ እውነት በማስረጃ በማስደገፍ ሊያስረዳቸው ነው::

ይህም በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ ሥርዓት በመሆን የሚቀጥል ይሆናል:: ኢየሱስ ወደ ወገኖቹ ቢሄድም አልተቀበሉትም፣ ስለዚህ ወደ ሌሎች ዘወር አለ:: ከአሕዛብ ወገን የነበረውን የመቶ አለቃውን እምነት ሲያደንቅ (ሉቃ 7÷1-10)፣ ናዝሬትን ትቶ ወደ ቅፍርናሆም ሲሄድ (ማቴ 4÷13)፣ ከኢየሩሳሌም ትይዩ በነበረ ተራራ ላይ ሆኖ መሲሐቸውን ለመቀበል ባለመፈለጋቸው እንባውን ሲያነባ እንመለከታለን (ማቴ 23÷37):: ኢየሱስ በየጊዜው ይገፋ ነበር፤ ስለዚህም ዘወር አለ:: በተመሳሳይ መንገድ ሐዋርያቱ ኢየሱስን ለአይሁድ እንደ ሰበኩላቸው ሆኖም ስላልተቀበሏቸው ወደ አሕዛብ ዘወር ይሉ እንደ ነበረ በሐዋርያት ሥራ ተዘግቦ እንመለከታለን:: በተለይም ይህ በጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ እውነት ነበር:: በገባበት ከተማ ሁሉ መጀመሪያ ወደ ምኩራብ ሄዶ ኢየሱስን ይሰብክ ነበር:: በዚያ ስፍራ ተቀባይነት ሲያጣ ወደ አሕዛብ ዘወር ይል ነበር:: ኢየሱስን ተቀብለው ቢሆን ኖሮ በእርግጥም ፍቅር በናዝሬት ይጀምር ነበር::[5]

የኤልያስንና የመበለቷን ታሪክ ከ1ነገሥት 17÷1-16 ማንበብ ይቻላል:: መልእክቱ ይህ ነው - አይሁድ ነቢዩ ኤልያስን መቀበል ባለመፈለጋቸው ከአሕዛብ ወገን የነበረችውን መበለት እንዲረዳ ይላካል::

---

[5] L.C. Crockett, "Luke 4:25-27 and Jewish-Gentile Relations in Luke-Acts, *JBL* 88 (1969): 177-183, ላይ እንደሚለው የዚህ ክፍል ዋናው ትኩረት የአይሁድ አለመቀበል ሳይሆን የአሕዛብ መካተትና (ሐሥ 13÷46 ያነ) በኋላም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአይሁድና የአሕዛብ መታረቅ ነው::

የኤልያስንና የንዕማንን ታሪክ በ2ነገሥት 5፥1-14 ማንበብ ይቻላል:: መልእክቱ ይህ ነው - አይሁድ ነቢዩ ኤልሳዕን መቀበል ባለመፈለጋቸው አይሁዳዊ የነበረውን ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን የነበረውን ለምጻም ፈወሰ:: በተመሳሳይ መንገድ ኢየሱስ በገዛ ራሱ ሕዝብ ተቀባይነት እያጣ ስለነበረ፤ እሱም ወደ ሌሎች ሄዶ ሊያገለግል ነው::

*ሉቃ 4፥28-31*

[28]በምኵራብ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ በቍጣ ገነፈሉ፤ [29]ከተቀመጡበትም ተነሥተው ከከተማው አስወጡት፤ ቍልቍል ሊጥሉትም ከተማቸው ወደ ተሠራችበት ኰረብታ አፋፍ ወሰዱት፤ [30]እርሱ ግን በመካከላቸው ሰንጥቆ ሄደ::

[31]ከዚያም በገሊላ አውራጃ ወደምትገኘው ከተማ ወደ ቅፍርናሆም ወረደ::

ሕዝቡ በጣም ተናድደዋል:: ስለ አሕዛብ አንዳች መልካም ነገር ሲሰሙ አይሁድ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያደርጋቸው እንደ ነበር ይህ ምላሻቸው ዓይነተኛ ምስክር ነው:: እግዚአብሔር አሕዛብን የፈጠረው የገሃነም እሳት እንዳይጠፋ ማገዶ እንዲሆኑ ነው የሚለውን ብሂል እያመኑ ነበር ያደጉት:: በዚሁ ምክንያት ጳውሎስም ችግር ላይ ወድቆ ነበር (ሐሥ 22፥21)::

ቀጥሎ የተፈጸመ ነገሮችን ውጣ ውረድ ማወቁ አስገራሚ ይሆናል (ቍ 29-30) ኢየሱስን ወደ ኮረብታው የወሰዱት አስገድደው ነበር? ወይስ በራሱ ፈቃድ ነበር የሄደው? በመካከላቸው ሰንጥቆ መሄዱ ተአምር ነበር? ወይስ ጸድቅነቱ እንዳይነኩት አደረጋቸው? ተአምር ከሆነ በድንገት ተሰወረ ወይስ እሱ ገፍትሮአቸው ሄደ ወይስ እነርሱ ድንገት ደነዘዙ?

ማንም የሰውን ልጅ ሕይወት ማጥፋት እንደማይችል ይህንን ያህል እዚህ ድረስ እናውቃለን:: በራሱ ፈቃድ ሕይወቱን አሳልፎ



ይሰጣል:: የሚሞትበት ጊዜ ገና አልደረሰም ነበር:: እጃቸውን በእርሱ ላይ ለመጫን (ዮሐ 7፥30፤ 10፥39) እንዲያውም እሱን በኃይል ለመያዝ የሚሞክሩበት ጊዜ ይመጣል (ዮሐ 8፥59፤ 10፥31):: ጊዜው እስኪደርስና እርሱም ሕይወቱን በፈቃዱ እስኪሰጥ ድረስ ማንም አይነካውም::

**§ 40**
**ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ**
**(ማቴ 4፥13-16)**

[13]የናዝሬትንም ከተማ ትቶ በዛብሎንና በንፍታሌም አካባቢ በባሕሩ አጠገብ በምትገኘው በቅፍርናሆም ከተማ መኖር ጀመረ:: [14]በዚህም በነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ::

[15]«የዛብሎን ምድር፣ የንፍታሌም ምድር፣ ከዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ አጠገብ፣ ያለው የአሕዛብ ገሊላ፣ [16]በጨለማ የሚኖር ሕዝብ፣ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ ምድር ላሉ ብርሃን ወጣለት::»

ኢየሱስ እንዲህ ያለ እርምጃ መውሰዱ ፋይዳ ያለው ነው:: ቅፍርናሆም ትልቅ ከተማ እንደ መሆኗ መጠን ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን እንዲያገኝና ለመስበክ ሰፊ ዕድል እንዲያገኝ ታስችለዋለች:: ወደዚያ መሄዱ በናዝሬት ጨርሶ አለመፈለጉንም ያሳያል:: ለሚቀጥለው አንድ ዓመትና ከዚያም ለሚበልጥ ጊዜ ቅፍርናሆም የኢየሱስ አገልግሎት ዋነኛ «ማዕከል» ልትሆን ነው:: ቅፍርናሆም የምትገኘው ከገሊላ ባሕር ሰሜናዊ ምዕራብ ዳርቻ ላይ ሲሆን ቅይጥ ባሕል ያላቸው ወገኖች የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉባት ከተማ በመሆኗ ለኢየሱስ ስብከት አገልግሎት የተመቸች ነበረች::

በ722 ዓ.ቅ.ክ. ተካሂዶ ከነበረው የአሦራውያን ቀደም ብሎ ይህ አካባቢ የዛብሉንና የንፍታሌም ነገዶች ድርሻ ነበር:: እስራኤል በግዞት ከተወሰደች በኋላ በባዕዳን ተያዘ:: ኢየሱስ እያገለገለ በነበረበት ዘመን እንኳ ከሕዝቧ 50% ያህሉ ከአሕዛብ ወገን ነበሩ (Blomberg, p. 88):: ማክጋርቪ እንደሚለው፣ «ስትራቦና ሌሎችም ባመለከቱት መሠረት

የአሕዛብ ገሊላ ተብላ ትጠራ የነበረው» (ገጽ 160) እንደ አይሁዳውያን ሁሉ የግብፃውያን፣ የአረቦች፣ የፊንቃውያን መኖሪያ ስለ ነበረች ነው:: ኢሳይያስ 9÷1-2 ገሊላ ወደፊት ስለምትባረከው በረከት ትንቢት ይናገራል::[6] ጨለማ ውጦት ወደ ነበረው ባሕል፣ የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ መጣ (ዮሐ 1÷4-5፣9፤ 3÷19፤ 7÷52)::

**§ 41**
**ኢየሱስ አራት ዓሣ አጥማጆችን መጥራቱ (ማቴ 4÷18-22፤ ማር 1÷16-20፤ ሉቃ 5÷1-11)[7]**

ይህ ለደቀ መዛሙርቱ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ጉዳይ እንደነበረ ግልጽ ሲሆን፣ ለጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያንም ቢሆን ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ሁኔታ ነበር:: ኢየሱስን የመከተል ልምምዳቸው በእነዚህ አራት ዓሣ አጥማጆች ተንጸባርቋል:: ኢየሱስ፣ ፍርሃትና አምልኮ በሰፈነበት ሁኔታ «ሰዎችን አጥማጆች» እንዲሆኑ መጥራቱ ለብዙ ክርስቲያኖች በጣም የተለመደ ነበር::

ከዚህም በተረፈ ይህ ሁኔታ ኢየሱስ ከዝቅተኛው የኅብረተ ሰብ ክፍል ጋር መቀራረቡን ብቻ ሳይሆን መንግሥቱን ለማስፋፋትም ጉልህ በሆነ ሁኔታ እንደ ተጠቀመበት ያሳያል:: «አስተምህሮአዊ እምነታቸው»

---

[6] ይህ አዲስ ኪዳን ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ይልቅ ከማስሬቲክ ዐውድ ጋር ከሚቀራረብባቸው ጥቂት ጥቅሶች አንዱ ነው (Archer & Chirichigno, *Old Testament Quotations in the New Testament*, ገጽ 98 ይመ)::

[7] ስለ ዓሣ አጥማጆቹ መጠራት ሉቃስ በሚያቀርበውና ማቴዎስና ማርቆስ በሚያቀርቡት ገለጻ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ:: ይህም ወንጌሎችን ከማጣጣም አኳያ የሚሠሩ ብዙዎች ይህንን ሁኔታ እንደ ሁለት የተለያዩ ገለጻዎች እንዲመለከቷቸው አድርጓቸዋል:: ይሁን እንጂ ዝርዝር ጉዳያቸውን በበቂ ሁኔታ ማስማማት ስለሚቻልና ኢየሱስ ጴጥሮስ ሁሉን ትቶ እንዲከተለው ሁለት ጊዜ ጠርቶት ነበር ማለቱ አግባብ ባለ መሆኑ እዚህ ላይ በአንድነት አቅርበናቸዋል:: ያም ሆኖ ሉቃስን ከመደበኛው አሠራር ወጣ አድርገን ከምንወስድባቸው ጥቂት ቦታዎች ይሄ አንዱ መሆኑን እንገነዘባለን:: ሉቃስ ይህን ታሪክ ያቀረበው ከኢየሱስ የቅፍርናሆም አገልግሎት (4÷31-37)፣ የጴጥሮስን አማት ፈውስና (4÷38-41) ከመጀመሪያው የገሊላ የአገልግሎት ጉዞ በኋላ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል (4÷42-44)::



የምንመኘውን ቅርስ የጣለ ባይሆንም፣ «ተግባራዊ እምነታቸው» ግን አርአያ የሚሆን ነው:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስን በተመለከተ የነበራቸው እምነት የተሳሳተ እንደ ነበር ግልጽ እንደሆነ ሲከሰት፤ በኢየሱስ የነበራቸው መታመን ግን ትክክል ነበር ማለት ነው::

ዓሣ የክርስቲያኖች ዓርማ መሆን የጀመረው ከዚህ ሁኔታ በመነሣት ነበር:: ዓሣ የሚለው ግሪክኛ ቃል ማለትም *ichtys* (ኤክቲየስ) አምስቱ ግሪክ ፊደሎች እያንዳንዳቸው የሚከተሉትን ቃላት ይወክላሉ፣ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር፣ ልጅ፣ አዳኝ:: የካታኮምቡ አምልኮ ሥርዓት ምስጢራዊ የይለፍ ቃል (መግባቢያ) በመሆን አገልግሏል:: ክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት እጥር ምጥን ባለ መልኩ በዚህ ዓርማ (ትዕምርት) ይጠቃለላል::

**ማቴ 4÷18 ከሉቃ 5÷1 ጋር**

[አንድ ቀን[ሉቃ]] 18 ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ
ሲያልፍ፣ ሁለት ወንድማማቾች ማለትም ጴጥሮስ የተባለውን
ስምዖንንና ወንድሙን እንድርያስን አያቸው:: ዓሣ
አጥማጆች ነበሩና መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ ነበር::

**ሉቃ 5÷1-3**

1 ሕዝቡ ዙሪያውን እያጨናነቁት የሚያስተምረውን
የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ፣ ኢየሱስ በጌንሳሬጥ አጠገብ
ቆሞ ነበር፤ 2 በዚህ ጊዜ ሁለት ጀልባዎች በባሕሩ ዳርቻ
ቆመው አየ፤ ዓሣ አጥማጆቹ ግን ከጀልባዎቹም ወርደው መረባቸውን ያጥቡ ነበር::
3 ከጀልባዎቹም መካከል የስምዖን ወደነበረችው ገብቶ፣ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ
እንዲያደርጋት ስመነው፤ ከዚያም ጀልባዋ ላይ ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ጀመር::

*[1] ይህ የገሊላ ባሕር ነው::*

ኢየሱስ ጴጥሮስና እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ የሚባሉ ሁለት ጥንድ ወንድማማቾችን ማለትም አራት ሰዎችን ጠራ፤ ሁሉም ዓሣ በማጥመድ ሥራ የተጠመዱ ነበሩ:: የሚሠሩትም በብዛት የገሊላ ባሕር

(የጌንሴሬጥን ወይም የጥብርያዶስ ባሕርም ይባላል) በመባል በሚታወቀው ባሕር ነበር፡፡ ሆኖም በመሠረቱ ሐይቅ እንጂ ባሕር አልነበረም፡፡ የአቦካዶ ዓይነት ቅርጽ ያለው ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ርዝመቱ ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ሲሆን ሰፋ ባለው ጐኑ አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡ ባልተለመደ ሁኔታ ከባሕር ወለል በታች ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ጫማ (ወይም ሦስት መቶ ሃያ መሬት) ረባዳ ስፍራ ላይ አርፎአል፤ ዙሪያ ገባውን አንድ ሺህ ጫማ (ወይም ሦስት መቶ ሰላሳ ሜትር) በሚሆን ኮረብታ ተከቦአል፤ በዓሣ ክምችቱ የበለጸገ ነበር፡፡

ግብርና በግ ዕርባታን ጨምሮ ዓሣ ማስገር የፓለስቲና ሦስት ከፍተኛ ገቢ ማስገኛ ዘርፎች ነበሩ፡፡ ከዚህ ሐይቅ ዓሣ ማስገር አትራፊ ሥራ ነበር፡፡ የአይሁድ መምህራን በገሊላ ባሕር ሦስተ መቶ የተለያዩ የዓሣ ዓይነቶች እንደሚገኙ በማጋነን ይናገሩ ነበር፡፡ ስለ ዓሣና ዓሣን ለምግብነት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል የአይሁድ መምህራን የሚናገሯቸው ይህንን የመሰሉ በርካታ አባባሎች እንደ ነበሩ ኤደርሼይም ያመለክታል (I:473)፡፡ በእርግጥም ዓሣ ማስገር በፓለስቲና ከፍተኛ ሥራ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ከኢየሩሳሌም በሮች አንዱ፣ «የዓሣ በር» ይባል ነበር (ነህ 3፥3)፡፡

ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ሲያልፍ ሌሊቱን በሙሉ ሲደክሙ አድረው ምንም ያላገኙት ዓሣ አጥማጆች መረባቸውን እያጠቡ ነበር (ሉቃ 5፥5)፡፡ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ከመረባቸው ላይ በጥንቃቄ የማይፈለጉ ነገሮችን ማለትም በመረቦቻቸው የተጠላለፉትን ጠጠሮችን፣ ሰርዶዎችንና አሸዋን ማስወገድን በአገልግሎት ብዛት የተቀደዱ መረቦችን መጠገንን ይጨምር ነበር፡፡

ስምዖንና እንድርያስ ከኢየሱስ ጋር ለመገናኘት የመጀመሪያዎቹ ናቸው፡፡ መረባቸውን ወደ ባሕሩ እየጣሉ ነበር፡፡ እንዲህ ያለ መረብ



መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው (*amphiblestron*) እዚህ ላይ ብቻ ነው፡፡ በአንጻራዊ መልኩ የተጣለው መረብ አነስተኛ ሲሆን ባሕር ውስጥ ሲጣል ውስጡ ያለውን ይዞ በቀላሉ ሰምጦ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ተጐትቶ ይወጣና «ቋቱ» ውስጥ ያለው ሁሉ ይወሰዳል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ሁለተኛው ዓይነት መረብ *sagene* የተባለው ሲሆን ከጀልባ ኋላ ኋላ እንዲጐተት ሆኖ ነበር የሚጠምደው (የተጠቀሰው በማቴ 13፥47 ብቻ ነው)፡፡ በጣም የተለመደው የመረብ ዓይነት *diktya* ሲሆን በምንባቡ ሁለቱ ተጠቅሷል፡፡ ብዙ ጊዜ የተለመደው ይህ ዓይነቱ መረብ ነበር፡፡ ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ አድሮ ባዶ እጅ ከመግባት በማለት ከሰዎቹ አንዱ ጥልቀት በሌለው ቦታ መረቡን (*amphiblestron*) እየጣለ ወዲያ ወዲህ ሲባዝን ትልልቆቹ መረቦች ይታጠባሉ፡፡

ሕዝቡ ኢየሱስን እየተጋፋትና እያጨናነቁት ነበር፡፡ በዚህ ወቅት በጣም ታዋቂ ሆኖ ስለ ነበረ እንደ ልቡ ወዲያ ወዲህ ማለት አይችልም ነበር፡፡ እንደ እውቅ የድራማ ተዋናይ ታጅቦ በነበረበት ወቅት ኢየሱስ ባዶ የነበረችውን የጴጥሮስ ጀልባ እንደ መስበኪያ መድረክ የባሕሩን ዳርቻ ደግሞ እንደ መድረክ የተጠቀመበት፡፡

**ሉቃ 5፥4-7**

[4]ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ስምዖንን፣ «ወደ ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ በልና ዓሣ ለመያዝ መረባችሁን ጣሉ»
አለው፡፡ [5]ስምዖንም መልሶ፣ «መምህር ሆይ፣ ሌሊቱን ሙሉ ስንደክም አድረን ምንም አልያዝንም፤ አንተ ካልህ ግን መረቦቹን እጥላለሁ» አለው፡፡
[6]እንደዚያም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረባቸውም ይበጣጠስ
ጀመር፡፡ [7]በሌላ ጀልባ የነበሩት ባልጀሮቻቸው በጥተው እንዲያግዟቸው በምልክት ጠሩቸው፤ እነርሱም መጥተው ሁለቱን ጀልባዎች በዓሣ ሞሏቸው፤ ጀልባዎቹም መስጠም ጀመሩ፡፡

ለማስተማር እንዲያመቸው በማሰብ ጀልባዋን ከባሕሩ ዳርቻ ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጋት ኢየሱስ ጴጥሮስን ጠየቀው። ማስተማሩን ከፈጸመ በኋላ ግን መረቡን ወደ ጥልቁ ውሃ እንዲጥል ለጴጥሮስ ነገረው። በጣም ስሜትን የሚነካ ሁኔታ ነበር። ጴጥሮስ ደክሞታል፣ ተስፋም ቆርጧል። ሌሊቱን ሁሉ ላይ ታች ሲሉ አድረው ምንም ኣላገኙም ነበር። እነዚህ ወቅቶች ለመዝናናት ዓሣ በመንጠቆ የምናጠምድባቸው ዓይነት ወቅቶች አልነበሩም። ትልልቅ መረቦችን የተሸከሙ በጣም ከባድ ጀልባዎች ነበሩ፤ ዋነኛ መተዳደሪያቸውን የሚያገኙት በእነርሱ ነበር። ከዚህም በላይ ጴጥሮስ ገና መረቡን አጥቦ ማብቃቱ ነበር። አሁን ግን ኢየሱስ እንደ ገና መረቡን እንዲያቆሽሽ እየነገረው ነው። ይህ እንግዳ ሰው ጊዜው ዓሣ የማስገሪያ ሰዓት አለመሆኑን እንኳ የሚያውቅ አይመስልም። ከዚህም በላይ ዓሣ ለማጥመድ የሚመረጠው ባሕሩ ዳርቻ እንጂ ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በማለት አልነበረም።

ጴጥሮስ፣ «መምህር ሆይ፣ አንተ ካልህ ግን መረቦቹን እጥላለሁ» አለ። ይህንንም «መምህር» (*epistata*) የሚለውን ያልተለመደ ቃል የተጠቀመበት ሉቃስ ብቻ ሲሆን ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብቻ ነበር የተጠቀመበት። ይህ ልብ አንጠልጣይ የሆነ አስፈላጊ ሐረግ ነው። ጴጥሮስ ባለሙያ ዓሣ አጥማጅ ነበር። ባሕሩን በሚገባ ያውቀዋል፤ እንዴት ዓሣ በማጥመድም ያለውን ችግር ያውቃል። ሆኖም ቀደም ሲል ኢየሱስ ያደረገውን ያውቃል። ከአንድ ዓመት በፊት መጥምቁ ዮሐንስን ይከተል በነበረበት ወቅት ኢየሱስ ሲጠመቅ አይቶአል። ኢየሱስ መቅደሱን ሲያነጻ ተመልክቶአል፤ በሰማርያ በጉድጓዱ አጠገብ የነበረችውን ሴት ካነጋገረ በኋላ በስፍራው ነበር። በይሁዳ ያደረጋቸውን ፈውሶች በዓይኑ አይቶአል፤ ታምራት በማድረግ በቃና ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ሲለውጥም አይቶአል። ኢየሱስን ለዘጠኝ ወሮች ያህል ከተከተለ በኋላ ኢየሱስ በትውልድ አገሩ እየሰበከ ሳለ ጴጥሮስ ቤተ ሰቦቹ



ዓሣ ወደሚያጠምዱበት ባሕር ተመልሶ ነበር። አሁን እንደ ገና ተገናኝተዋል። ኢየሱስ ይህንን ቀላል ሆኖም ሞኝነት የሚመስል ጥያቄ ያቀርባል። ለኢየሱስ ከነበረው አክብሮትና መታማመን የተነሣ ጴጥሮስ መታዘዝን መርጧል።

ጴጥሮስ መረቡን እየጐተተ እያለ ጡንቻው ተወጣጠረ ዓይኖቹ ተጐልጉለው የሚወጡ መሰሉ፣ ሳያውቀው ድንገት ፊቱ በፈገግታ ተሞላ። ጀልባዋም እስክትሰምጥ ድረስ ያጠመዱት ዓሣ በጣም ብዙ ነበር። ፈገግታቸው ወደ ዓይነ አፋርነት ተለወጠ። ጴጥሮስ የሆነ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ገባው። ሉቃስ፣ «በምልክት ጠራቸው» የሚል ሐረግ ተጠቅሟል። ይሄ ትርጉም ያለው አባባል ነው። እጆቹ መረቡን ስለያዙ በእጆቹ መጣራት አስቸጋሪ ይሆንበታል፣ በእጁ የያዘውም እንዲያመልጠው አይፈልግም። ከዚህም በላይ በጣም ርቀ ስለ ነበር ቢጣራ እንኳ ሊሰሙት አይችሉም፤ ሥራ በዝቶበት ስለ ነበር ከባልጆሮቹ ጋር መነጋገር አይችልም።

ያዕቆብና ዮሐንስ በውስጧ ይዛ ሁለተኛዋ የቤተ ሰባቸው ጀልባ ለእርዳታ መጣች መረቡ በሁለቱ ጀልባዎች መካከል እንዲንጠለጠል በሌላኛው ወገን ዞረው መሳብ ጀመሩ። እየሳቡ ሳሉ ዓሣዎች ጀልባው ላይ ይንጠባጠቡ ጀመር። ጨርሶ እንዳይሰጥሙ እስኪያሰጋ ድረስ ሁለቱም ጀልባዎች የያዙት ወደ ታች እየዘቀጡ እስኪሄዱ እጅግ ብዙ ነበር። ማስተናገድ የሚችሉት የበረከት ብዛት ይህን ያህል ነበር! ምናልባትም ኢየሱስን መከተል ከጀመሩ ዘጠኝ ወሮች እንሥቶ ዕዳ እየበዛባቸው ሳይሄድ አልቀረም። አሁን ግን በዚያ ግሩም ቅጽበት ኢየሱስ ለራሳቸውና የቤተ ሰቦቻቸውን የረጅም ጊዜ ወጪ ሊሸፍን የሚችል በረከት አዘጋጀላቸው።

ሉቃ 5፥8-10

[8]ስምዖን ጴጥሮስም ይህ ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቀ፣ «ጌታ ሆይ፣ እኔ ኀጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ

ተሰዶ አለው፡፡ [9]ይህንን ያለው እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት በያዙት ዓሣ ብዛት ስለ ተደነቁ ነው፤ [10]ደግሞም የስምዖን ባልንጀሮች የነበሩት የዘብዴዎስ ልጆች፣ ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ፡፡

ምናልባት ኢየሱስ ከእርሱ እንዲኖር ጴጥሮስ ሳይፈልግ እንዳልቀረ አስባችሁ ይሆናል፡፡ መቼም ለትርፋማ ሥራ እሱ መልካም ነው፡፡ ጀልባቸውን ጥግ ካስያዙና ልባቸውም ከተረጋጋ በኋላ ጴጥሮስ በጉልበቱ በዓሣዎቹ ክምር አጠገብ ተንበረከከ፡፡ የኢየሱስን ማንነትና ምን ማድረግ እንደሚችል በእርግጥ አይቶአል፡፡ ስለዚህም፣ «እኔ ኀጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ» አለ፡፡ እዚህ ላይ ጥቂት ነገሮችን ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ (1) ጴጥሮስ ትክክል አስቦአል፡፡ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እሱ ተአምር ናፋቂ አልነበረም፡፡ ፍጹምና ንጹሕ በሆነ ሕልውና ፊት መቆም ምን ማለት እንደ ሆነ ነበር ሲያስብ የነበረው፡፡ የኢየሱስ ንጽሕና ታዛዥነትን ይጠይቃል፤ ፍርድንም የሚያስከትል ነው፡፡ (2) ጴጥሮስ ይህንን ያለው ከራሱ ከእግዚአብሔር ሐልዎት የተነሣ ፍርሃት እየተሰማው ነበር፡፡ ለእርሱ የሚያስፈራ ታምራት ነበር፡፡ ዙሪያውን ቆመው የነበሩት ሰዎች እንደ ሳቁ ወይም እንደ ቀለዱ አይጠረጠርም፤ ሆኖም ልትሰምጥ በነበረችው ጀልባ ውስጥ አልነበሩም፡፡ እንደ ጴጥሮስና አብረውት እንደ ነበሩት ሰዎች በተደረገው ታምራት በግላቸው አልተነኩም፡፡ ከዚህም ባሻገር እዚህ ላይ የምንመለከተው የባሕሩን ኀያልነትና የተደረገውን ታምራት ታላቅነት በሚገባ የተረዳን ባለሙያ ዓሣ አጥማጅ ነው፡፡ ኢየሱስ ባሕሩን ሰንጥቆ ዓሣዎቹን ማየት እንደ ቻለ ሁሉ የጴጥሮስን ጥልቅ ማንነት አልፎ ልቡን መመልከት ችሎ ነበር፡፡

ሉቃ 5፥10-11
ከማቴ 4፥19-20፤
ማር 1፥17-18
ጋር

ኢየሱስም ስምዖንን፣ «አትፍራ፣ [ተከተለኝ[ማቴ፣ማር]] ከእንግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ» አለው፡፡ [11]እነርሱም ጀልባዎቹን ወደ ምድር ካስጠጉ በኋላ ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡



ማቴ 4፥21-22
ከማር 1፥20
ጋር

[21]አለፍ እንዳለም፣ ሌሎች ሁለት ወንድማማቾች፣ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን አየ፡፡ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ ውስጥ መረባቸውን ያበጁ ነበር፡፡ [ወዲያውኑ[ማር]] ኢየሱስም ጠራቸው፤ [22]ወዲውኑም ጀልባቸውንም ሆነ አባታቸውን ትተው [ከቅጥር ሠራተኞቹ ጋር በጀልባ ላይ ትተው[ማር]] ተከተሉት፡፡

ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕሩ ዳርቻ እንደ ተመለሱ ሕዝቡ ሰብሰብ ብለው በየዓይነታቸው እየተለዩ ሳሉ ዓሦችን መቍጠር ይጀምራሉ፡፡ የጴጥሮስ ቅጥር ሠራተኞችም (ማር 1፥20) እንደ ገና መረባቸውን ማጠብ እንደሚጀምሩ አይጠረጠርም፡፡ እንግዲህ በሕሊናቸው ሊስሉት በሚችሉበት በእዚህ ወቅት ነበር ኢየሱስ እያከናወኑት የነበሩትን ሥራ መሠረት በማድረግ «ሰዎችን የሚያጠምዱ እንዲሆኑ» የጠራቸው፡፡ እንደ ሌሎቹ ምሳሌዎች ሁሉ በንጽጽር የቀረቡት ነጥቦች ሁሉ ተግባራዊ ግንዛቤ ሊያገኙ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ኢየሱስ የተናገራቸው ሰዎችን እንዲያጠምዱ ወይም ምርኮኛ አድርገው እንዲይዙ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲያመጧቸው ነበር፡፡ ጴጥሮስና እንድርያስ የኢየሱስን ጥሪ ተቀበሉ፡፡

እዚህ ላይ ሉቃስ ከሌሎቹ ተወራራሽ ወንጌሎች ይለያል፡፡ ማቴዎስና ማርቆስ ሁለቱም፣ «ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ» ይላሉ፡፡ ሉቃስ የተጠቀመበት ቃል ግን ዓሣ ማጥመድን ሳይሆን ከነሕይወታቸው መማረክን ነው የሚያሳየው፡፡ ይህ ቃል የተጠቀሰው አንድ ሌላ ቦታ ብቻ ነው (2ጢሞ 2፥26)፡፡ እዚያ ላይ የሚገልጸው በሕይወታቸው እያሉ ሰይጣን በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋቸውን እንዴት ማስጣል እንዳለብን ነው፡፡ ይህ ለጦርነት እንደሚደረግ ጥሪ ነው፡፡ ሰይጣን በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋቸውን ነፃ ለማውጣት ወደ ጠላት ግዛት አልፈን እንገባለን፡፡

ሦስቱ ሰዎች ጥቂት ርቀው እንደ ሄዱ ከባልንጀሮቻቸው ማለትም ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ተገናኙ:: ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጠንካራ ጀልባቸው ላይ ተቀምጠው መረባቸውን እያጠቡና ካጠመዱት ብዙ ዓሣ የተነሣ የተቀደዱ መረቦቻቸውን እየጠገኑ ነበር:: ኢየሱስ እነርሱንም ጠራቸው፤ እነርሱም አባታቸውን ከቅጥር ሠራተኞቹ ጋር ጀልባ ላይ ትተው ተከተሉት (ማር 1÷20)[8]:: በኋላ ከመጡት ከእነዚህ ከሁለቱ በሐዋርያት ሥራ 12 ላይ አሟሟቱ የተገለጸው ያዕቆብ የመጀመሪያው ሰማዕት ሐዋርያ ነበር:: በ95 ዓ.ም. ራእይን የጻፈ እንደ መሆኑ መጠን ዮሐንስ ሳይሞት በሕይወት የቆየ የመጨረሻው ሐዋርያ ሲሆን፣ ትውፊት እንደሚለው የተለመደውን ዓይነት አሟሟት የሞተ እርሱ ብቻ ነበር::

ዘብዴዎስ ብቻውን በመቅረቱና መረቡን ለብቻው በማጠቡ ደስተኛ ይሆናል ብዬ አላስብም:: እርግጥ ነው የሚያካሂዱት ሥራ ትልቅ ስለ ነበር ትንንሹን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች መቅጠር እንኳ አስችሏቸዋል:: የቤተ ሰቡን ሥራ እንዲሠራ እነዚህ ልጆች አባታቸውን ብቻውን ትተውት መሄዳቸው ተገቢ አይመስልም፤ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ግን ይኸው ነው (ማቴ 10÷37 ጋር ያነ)::

ጥሪው ድንገት በመሆኑ በአስቸኳይ ምላሽ መስጠታቸው የሚገርም ነው:: ሆኖም፣ እነዚህ አራት ሰዎች ከኢየሱስ ጋር ለአንድ ዓመት ያህል አብረው ይጓዙ እንደነበረና (ዮሐ 1÷35-51 ጋር ያነ) አሁን ደግሞ በታምራት የተጠመደውን ዓሣ ብዛት እየተመለከቱ እንደነበሩ መዘንጋት የለብንም:: ኢየሱስ ወደ ሕይወታቸው ክልል ገብቶ ኀይሉን አሳይቶአቸዋል:: አሁን ደግሞ ሰዎችን አጥማጆች እንዲሆኑ ኀይል

[8] አገልጋዮቹን አስመልክቶ ማርቆስ የሰጠን ፍንጭ ምናልባት ከጴጥሮስ ስብከት ያገኘው ይሆናል:: ከዚህ በስተቀር በማቴዎስና ማርቆስ ውስጥ የቀረበው የዚህ ጥሪ ዘገባ አንድ ዓይነት ሁኔታን የሚያመለክት ነው::



ይሰጣቸው ዘንድ ወደ ራሱ ክልል ጠርቶአቸዋል:: ኢየሱስን የመሰለ ሰው ወደ ራሱ ሥራ ሲጠራችሁ ሌላ ምን የምታደርጉት ይኖራል?

ኢየሱስ እነዚህ ሰዎችን በተለየ ሁኔታ ነበር የጠራቸው፤ (1) በዚያ ወቅት ኢየሱስን በተመለከተ በኢየሩሳሌም ተቃውሞ ነበር:: የዚህ ሰው ተከታይ መሆን አደገኛ እንደ ሆነ ያውቃሉ:: (2) አትራፊ፣ ተወዳጅና በተረጋጋ ሁኔታ ይካሄድ የነበረውን ሥራቸውን እንዲተዉ ነበር የጠራቸው:: ለእነርሱ ይህ ትልቅ የእምነት እርምጃ ነበር:: (3) ኢየሱስ የጠራቸው ወደ አዲስ አቅጣጫ እንጂ ወደ አዲስ ዓይነት አስተምህሮ አልነበረም:: በዘመኑ የነበሩ የአይሁድ መምህራን በዙሪያቸው ተማሪዎች ማሰባሰብን እንደ አንድ የተቀደሰ ተግባር ይመለከቱ ነበር:: ኢየሱስ ግን መጥተው እንዲማሩ ሳይሆን፣ መጥተው እንዲሠሩ ወይም መጥተው የተማሩትን እንዲሆኑ ነበር የጠራቸው:: ብልጭ ድርግም እያለ የነበረው የመንግሥቱ ብርሃን በድምቀት ማብራት ሊጀምር ነው::

**§ 42**
**በምኩራብ ማስተማሩና ርኩስ መንፈስ ማስወጣቱ**
**(ማር 1÷21-28፤ ሉቃ 4÷31-37)**

ቀጥሎ የምንመለከታቸው ሁለት ሁነቶች (42-43) የተፈጸሙት በአንድ ሰንበት ቀን ነበር::[9] እዚህ ላይ የኢየሱስ አገልግሎት ቀደም ሲል ስለ ነበረበት ሁኔታ በጥቂቱም ቢሆን እንመለከታለን:: ከኢየሩሳሌም የመጡ ጣልቃ የሚገቡ ፈሪሳውያን አልነበሩም:: ታላቁ ሐኪም ኢየሱስ በክብር የተቀበሉትን ሕዝብ ችግር እየፈታ ነበር:: በትሕትናውና በመለኮታዊነቱ ሕዝቡን እየነካ ነበር:: ናዝሬት በነበረው ምኩራብ ኢየሱስ

[9] ሉቃስ ምኩራብ ውስጥ ሁለት እርስ በርስ የሚነፃፀሩ ሁኔታዎች መፈጸማቸውን ያቀርባል:: በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ከመጠላቱ የተነሣ፣ ባደገበት ከተማ ከነበረው ምኩራብም ተባርሮአል (4:16-31):: ሁለተኛ፣ በቅፍርናሆም ምኩራብ ርኩስ መንፈስ ካወጣ በኋላ ግን ተከብሯል (4:32-37):: በሁለቱም ሁኔታዎች ኢየሱስ ብርቱ በሆነ ትምህርቱ ሕዝቡን አስገርሞ ነበር::

የጠቀሰው ትንቢት እየተፈጸመ ነበር (ሉቃ 4÷18-19፤ ኢሳ 61÷1-2):: ግጭትም ሆነ የተወሳሰበ ነገር ገና አልተፈጠረም:: ኢየሱስ ራሱን በዚህ ሁኔታ መግለጥ አለመቻሉ እውነት ባይሆን ኖሮ ይህን መሳይ ገራገር ንፅሕና እንዲኖር እንፈልግ ነበር:: ሆኖም ከኢየሱስ ተአምራትና ማንነት ባሕርይ የተነሣ የብዙ ሰዎችን ትኵረት መሳቡ፣ ብዙዎች ለእርሱ መሰጠት ማሳየታቸውና በእሱም ሳቢያ ግጭት መነሣቱ የማይቀር ነው::

ማር 1÷21-22

[21]ከዚያም ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ፤ ኢየሱስም
ወዲያው በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገብቶ ማስተማር
ጀመረ:: [22]እንደ ጸሐፍት ሳይሆን፣ እንደ ባለ ሥልጣን
በማስተማሩ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ::

ሊፈጸሙ ለሚችሉ ለጥቂት ሳምንቶች የማስተማር አገልግሎትና አራቱን ዓሣ አጥማጆች ለመጥራት በቂ ስፍራ በመስጠት ኢየሱስ በየሰንበቶች (ብዙ ቍጥር) በምኵራብ እያስተማረ እንደ ነበር ሉቃስ ያመለክታል (ሉቃ 5÷1-11):: ኢየሱስ በሥልጣን ነበር ያስተማረው:: በእርሱና በጸሐፍት መካከል ጉልህ ልዩነት ነበር:: በጸሐፍት ዘንድ የተለመደው ዓይነት ማስተማሪያ መንገድ ከሌሎች ታዋቂ ጸሐፍት ረጃጅም ጥቅሶችን መደርደር ነበር:: ይህም ትምህርታቸው ተአማኒነት እንዲኖረው የሚያደርግ ነበር:: ከዚያ በተለየ ሁኔታ ኢየሱስ ግን፣ «እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ» ነበር ያለው:: ከዚህም በላይ የቃሎቹ እውነተኛ ነት የራሳቸው የሆነ ሥልጣን ነበራቸው:: ሕዝቡ ግን አንድን እውነት፣ እውነት ብሎ ለመቀበል፣ «የባለ ሙያ ማረጋገጫ ማኅተም» አያስፈልገውም ነበር:: እንደ ተለመደው ሕዝቡ ተደነቁ (ማቴ 7÷28፤ 13÷54፤ 19÷25፤ 22÷33፤ ማር 1÷22፤ 6÷2፤ 7÷37፤ 10÷26፤ 11÷18፤ ሉቃ 2÷48፤ 4÷32፤ 9÷43፤ ሐሥ 13÷12 ጋር ያነ)::



ሉቃ 4÷33-35
ከማር 1÷26
ጋር

[33]በምኵራብ የርኩስ ጋኔን መንፈስ ያደረበት
ሰው ነበረ፤ እርሱም ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ፣ [34]ወዮ!
የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፣ ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለ
የመጣኸው ልታጠፋን ነውን? አንተ ማን እንደ ሆንህ
ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ! አለው::
[35]ኢየሱስም፣ «ጸጥ ብለህ ከዚህ ሰው ውጣ!» ብሎ ገሠጸው:: ጋኔኑም
ሰውየውን በሕዝቡ ሁሉ ፊት ጣለውና [በኀይል ካንፈራገጠው በኋላ[ማር]] ምንምም ጉዳት
ሳያደርስበት [እየጮኸ[ማር]] ለቀት ወጣ::

ኢየሱስ ጋኔንን[10] ወይም ደግሞ ሉቃስ እንደሚለው «ርኩሳን መናፍስትን» ካስወጣባቸው በርካታ ወቅቶች ይህ የመጀመሪያው ነበር:: የነበረበት ባሕል ከአጋንንት ጋር በተያያዙ የተለያዩ የፈጠራ አስተሳሰቦች የተሞላ ነበር:: (cf. Edersheim, Appendix XVI)[11] እንዲያውም አይሁዳውያን ስለ አጋንንት የሚናገሩ ብዙ የሥነ ጽሑፍ ስብስቦች ነበሯቸው:: ሥነ ጽሑፎቹም በዋነኛነት ደረጃ የሚነሷቸው ሁለት ነገሮች፣ (1) አጋንንት በሞት የተለዩ ክፉ ሰዎች መንፈሶች መሆናቸውንና፣ (2) በአስማትና ድግምት ማስወጣት እንደሚቻል ነበር::

---

[10] ይህ በማርቆስ የተጻፈ የመጀመሪያ ተአምር ነው:: ኢየሱስ በአጋንንት ላይ የነበረው ኀይል ተአምር የማድረግ ችሎታውንና የእግዚአብሔርን መንግሥት በይፋ ያስተዋወቀ መሆኑን በጉልህ ይገልጻል:: የዚህ ታሪክ ዋነኛ ሐሳብ፣ «ይኸው ንጉሡ መጥቷል!» የሚል ነበር:: ከዚህም በላይ ይህ ማርቆስና ሉቃስ በየበኩላቸው ያቀረቡት የመጀመሪያ ተአምር ነበር:: ማቴዎስ በዝምታ ያለፈውን ጉዳይ ማርቆስና ሉቃስ መናገራቸው በጣም ያልተለመደ ነበር::

[11] ለምሳሌ ያህል ፒ.ቲ. በትለር (ገጽ 76) የሚከተለውን ይላል፣ «በዘመኑ የነበሩ መናፍስት አስወጪዎች አየሩ በርኩሳን መናፍስት ተበክሎአል፤ በአንዳንድ አጋጣሚዎች አጋንንቱ ከምግብና መጠጥ ጋር ሰዎች ውስጥ ይገባሉ ... አንዳንድ የአይሁድ መምህራን ደግሞ አጋንንት የማይታዩ እንደመሆናቸው መጠን አንድ ሰው ዐመድ ነፍቶ በራፉ ላይ ቢነሰንስ የዶሮ እግር የመሰለ ኮቴ ንጋት ላይ ሊታይ ይችላል በማለት ያምኑ ነበር:: አጋንንት እንደ ሰዎች ሁሉ እንስሳትንም የሚያጠቁ በመሆናቸው አንድ የአይሁድ መምህር ገላውን ለመታጠብ ወደ መታጠቢያው ክፍል በሚገባበት ጊዜ መከላከያ የሚሆነው የበግ ግልገል ሁል ጊዜ ይዞ ይገባ ነበር::»

ይሁን እንጂ የአይሁዶች የፈጠራ አስተሳሰቦች ሲባል አጋንንት የሉም ይላሉ ማለት አይደለም። ኢየሱስ ፊት ለፊት የተጋፈጠው ከእውነታው ጋር እንጂ ከፈጠራ አስተሳሰብ ጋር አልነበረም።

ኢየሱስ አጋንንትን እንደ ፈጠራ ወይም የአእምሮ ሕመም ሳይሆን በእውን ሕልውና እንዳላቸው አድርጎ ይመለከታቸው እንደ ነበር ኤደርሼይም ይገነዘባል (I:480)። (1) አጋንንትን እንዲያስወጡ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአል (ማቴ 10፥8)። (2) ስለ አጋንንት መውጣት እግዚአብሔርን አመስግኗል (ሉቃ 10፥17-18)። (3) አጋንንት ማስወጣት ባቃታቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ገስጿል (ማቴ 17፥17)። እንግዲህ እዚህ ላይ ወይ ኢየሱስ በዘመኑ ከነበረው የተሳሳተ እምነት የነጻ አልነበረም፣ ወይም የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ሲል አጋንንት በእውን ሕልውና እንዳላቸው አስመስሏል ወይም ደግሞ፣ በእርግጥም አጋንንት ሕልውና ያላቸው ናቸው።

እንደ አሁኑ ሁሉ ያኔም አጋንንት እውን ነበሩ።[12] በአንዳንድ ባሕሎች የሚታየውን አጋንንታዊ መገለጥ ያህል በሌሎች ላይኖር ይችላል። ይሁን እንጂ ጨርሶ የሉም ማለት አይደለም። ሰይጣን በእንዴት ያለ መሣሪያ መጠቀም እንዳለበት ያውቃል። አንድ አናጢ

[12] ምንም እንኳ ይህ የአብዛኞቹ ወንጌልን አማኝ ክርስቲያኖች አቋም ቢሆንም፣ በዚህ ዘመን አጋንንት መኖራቸውን የሚቀበሉ ግን ሁሉም አይደሉም። ለምሳሌ ያህል ኤደርሼይም በኢየሱስ አገልግሎት ብቻ የታዩ ክስተት እንደ ነበር ነው የሚያምነው ለዚህ እምነቱ እንደ መሠረት የሚያቀርበው በአጋንንት መያዝ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በተረፈ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወይም በሚሽናህ (Mishnah I:481) አለመጠቀሱን ነው። ከዚህም በላይ አንዳንዶች ስለ አጋንንታዊ አሠራር የሚቀርበውን ዘገባ ሁሉ ከአእምሮአዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ችግር ጋር ብቻ ሊያያይዙት ይሞክራሉ። (J.K. Howard, "New Testament Exorcism and its Significance Today" *ExpT* 96 [Jan 1985]: 105-109 ጋር ያነ)። ይሁን እንጂ እንዲሁ ያለው አመለካከት ጭፍን ከመሆኑም በላይ ነባራዊ ሐቆችን በሙሉ ያገናዘበ አይደለም John Mantgomery, ed, *Demon Possession* [Minneapolis: Bethany Fellowship, 1976]).



በአስፈላጊው ጊዜ በምን ዓይነት መሣሪያ መጠቀም እንዳለበት እንደሚያውቅ ሁሉ፣ ሰይጣንም በአስፈላጊው ቦታና ጊዜ በምን ዓይነት የዓመፅ መሣሪያ መጠቀም እንዳለበት ያውቃል።

አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎችን መካድ ስሕተት እንደ ሆነ ሁሉ ከተገቢው በላይ ማጋነንም እንዲሁ ስሕተት ነው። በዚህ ዘመን ብዙዎች የጥንቆላ አሠራርን (occult) በተመለከተ ከፍተኛ ጉጉት አሳይተዋል፤ ሌላው ቀርቶ በአንዳንድ ክርስቲያን ነን በሚሉ አካባቢ እንኳ፣ «ኃይልን መሞላት» በሚል ሽፋን ብዙ ስሕተት እየተፈጸመ መሆኑን እናውቃለን። አጋንንትን አስመልክቶ በሚኖረን ነገረ መለኮታዊ አመለካከት ወይም የግል ሕይወት ልምምድ የሚከተሉት እውነቶችን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፦

1. ሰይጣን ሁሉን ቻይ ወይም ሁሉን ዐዋቂ አይደለም። አንዳንዴ ሰይጣን እየፈተነኝ ነው ማለት ጉረኝነት ሊሆን ይችላል - ምናልባትም እርሱ የሚያጠምደው ሌላ ትልቅ ዓሣ ይኖረዋል።
2. እንንት፣ ከካንሰር፣ ከቁጣ፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከትዕቢት፣ ከስርቆት ወዘተ ጋር የተያያዙ ስለመሆናቸው ምንም ማስረጃ የለም። በሌላ አነጋገር አጋንንት ሰብዕና ያላቸው ቢመስሉ እንኳ (ማር 5÷8፤ 9÷25)፣ የአንዳንድ ሕመሞች ምክንያት ጋኔን ስለመሆኑና ጋኔኑ ከመውጣቱ በፊት ራሱን መግለጽ አለበት ለማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለንም።
3. የአጋንንቱን ስም ካወቃችሁ ልታስወጡት አትችሉም የሚለው አስተሳሰብ ሥረ መሠረት፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ይልቅ የግሪኮችና የአይሁዶችን አስማታዊ ልምምድ ነው ።
4. መንፈሳዊ ውጊያ ላይ መሆናችን የሚካድ አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ ውጊያ ምንታዌነት ያለው እንደ ሆነ አድርጎ ማሰብ ስሕተትና እምነት ማጣትን የሚያመለክት ነው፤ እኩል ኃይል

ባላቸው ሁለት ተጻራሪዎች ማለት በብርሃንና በጨለማ መካከል የሚደረግ ውጊያ እንደ ሆነና አንዱ ሌላውን የሚያሸንፈው በብዙ ውጊያ እንደ ሆነ ማሰብ ትክክል አይደለም:: ፍጡራን ከሆኑና ከተጣሉ (ርኩሳን መናፍስት ይልቅ መንፈስ ቅዱስ እጅግ ኃያል ነው:: ስለዚህ በሁለቱ መሐል ምንም ፉክክር የለም ማለት ይቻላል::

5. መልካሞቹ መላእክት ድል የሚያገኙት በቅዱሳን ጸሎት ሲታገዙ ለመሆኑ ማስረጃ የለም:: በምልጃ ጸሎታቸው አማካይነት ሰዎች ለመላእክት ድጋፍ ሲያደርጉ መቻላቸው መሠረት የለሽ ተረት ነው::
6. አጋንንት በሽታዎች አይደሉም:: ወንጌሎች ውስጥ በሽታዎችና ሕመሞች ከአጋንንት ተለይተው ነው የቀረቡት:: በሽታ በኃጢአት የወደቀው ዓለም አንድ አካል ነው:: አጋንንት ግን፣ «ከሰማይ የተጣሉ» መናፍስታዊ ፍጡራን ናቸው

ኢየሱስ በምኩራብ ካስተማረ በኋላ ርኩስ ጋኔን የነበረበት ሰውዬ፣ «ወዮ ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለ?» በማለት ጮኸ:: «ወዮ» የሚለው ቃል ጥልቅ ስሜትን ያመለክታል:: በአንድ ጊዜ የፍርሃት፣ የጥላቻና የቁጣ መፈራረቅን ያሳያል:: «ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለ?» የሚለው የዐረፍተ ነገሩ ሁለተኛ ክፍል፣ «እኛና አንተን ምን የሚያደራርሰን ነገር አለ?» ወይም፣ «ለምን ጣልቃ ትገባብናለህ?» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

ከዚያ በኋላ ጋኔኑ የመጣው እነርሱን ለማጥፋት እንደሆነ ኢየሱስን ጠየቀ:: ኢየሱስ አጋንንትን ሲያስወጣ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ ነበር:: ውጊያው ከመጀመሩ በፊት ተሸነፉ፤ መሸነፋቸውን እስኪቀበሉ ድረስ ኢየሱስ በረታባቸው:: በክርስቶስ መንፈስ የተሞላን እስከ ሆንን ድረስ አጋንንትን መፍራት የለብንም::



በጣም አስገራሚው ነገር፣ የራሱ የኢየሱስን ደቀ መዛሙርትን ጨምሮ ምኩራብ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ይልቅ አጋንንቱ የኢየሱስን ማንነት መረዳታቸው ነው:: ጋኔን የነበረበት ሰው፣ «ማን እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!» አለ:: ይህ፣ «አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሃትም ይንቀጠቀጣሉ» የሚለውን ያዕቆብ 2÷19 ላይ ያለውን ያስታውሰናል::

ኢየሱስ ግን እንዳይናገሩ ከለከላቸው:: ለምን? ምክንያቱም፣ (1) ኢየሱስ ስለ መሲሕነቱ እውነተኛ ማንነት ገና ባለማስተማሩና ይህንኑም ባለማሳየቱ:: መሲሑን በተመለከተ የተሳሳተ አመለካከት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ (2) ከአጋንንት አንደበት ምንም የምስጋና ቃል ባለመፈለጉ፤ እና (3) ተግባር ከቃላት ይልቅ ጮኽ ብሎ እንደሚሰማ በማወቁ ናቸው:: ኢየሱስ የፈለገው ተግባሩ እንዲመሰክርለት ነበር::

ስለዚህም ኢየሱስ ዝም እንዲሉ በማዘዝ፣ «ለጐማቸው::» ኢፒቱሜሰን - [*epetimesen*]:: ቃሉ ትኩረት የሚያሻው ነው:: ኢየሱስ በሚቀጥለው ሁኔታ (ሉቃ 4÷39፣41) የጴጥሮስን አማት ሲፈውስ በዚሁ ቃል መጠቀሙን እንመለከታለን:: የዚህን ክፍል ዓላማ በመረዳት ረገድ ቁልፍ ቃል ነው ኢፒቲማ - [*epitimao*] ለሚለው ቃል ኤች.ሲ.ኪ. የሚከተለውን ገለጻ ሰጥቷል፤ «የእግዚአብሔር መልእክተኛ ጠላቶቹን የሚያሸንፍበት፤ በዚህም ምክንያት ለእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት የሚያዘጋጅበት የትእዛዝ ቃል ነው::»[13] ቃሉ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደሚውል በስፋት የአይሁዶችን ጽሑፍ ከመረመረ በኋላ በሕመምና በአጋንንት በይፋ የሚታየውን የጨለማ ኃይላት ለማሸነፍ እግዚአብሔር የሚያደርገው ውጊያ መሆኑን አመልክቷል:: ስለሆነም ይህ ሁኔታ ቀጣይ የሆነው ውጊያ ክፍል መሆኑን ያሳያል ማለት ነው::

[13] H.C Kee, "The Terminology of Mark`s Exorcism Stories." *NTS* 14 (1967-8): 232-246.

በተጨማሪም የሰይጣን ግዛት ፍጻሜ መቃረቡን የሚያበስር የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ጥሶ መግባት በተግባር ያሳያል::

ጋኔኑ ቀር ሳይፈልግ ከሰውየው ወጣ:: የሚፈልገውን ያላገኘ ሞልቃቃ ልጅ እንደሚያደርገው ሁሉ ሰውየውን መሬት ላይ ጣለው። ሆኖም ለመጨረሻ ጊዜ ሰውየው ላይ የሚያሳርፈው የፈሪ በትር መሆኑ ግልጽ ነበር:: ባለ መድኃኒቱ ሉቃስ ጋኔኑ ሰውየውን እንዳልጎዳው ተናግሯል:: ሌላው ቢቀር፣ አምላክና ሰው በሆነው ክርስቶስ ፊት ይህን የማድረግ ድፍረት አይኖረውም::

ይህ ሁኔታ ሌሎች በሚያደርጉት መልኩ አጋንትን ማስወጣት አልነበረም:: ምንም ዐይነት አስማታዊ ድግምት ወይም ቀመር አልተጠቀመም:: ይልቁንም ሁኔታው እንደ ማንኛውም ዐይነት ፊውስ ነበር::[14] ኢየሱስ እንዲሁ በቃሉ ሥልጣን ብቻ ጋኔኑ እንዲወጣ አዘዘ፤ እርሱም ከመታዘዝ ሌላ አማራጭ አልነበረውም:: እዚህ ላይ ዋናው ነጥብ ስለ አጋንንት መመራመር ሳይሆን፣ የኢየሱስ ሥልጣን ነው::

የአጋንንትን ኀይል አጋንኖ ከሚያቀርብ ሐሰተኛ አስተሳሰብ መጠበቅ አለብን:: እርግጥ ነው የአጋንንት መኖር እውነት ነው፣ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውም እውነት ነው፤ ያም ሆኖ ግን ለክርስቶስ ቃል እንደሚታዘዙ እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል:: በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን እስከሆንን ድረስ፣ ርኩስ መንፈስን መፍራት የለብንም:: «በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል» (1ዮሐ 4÷4):: ኢየሱስ፣ «የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ» ተገለጠ (1ዮሐ 3÷8):: በመጨረሻውም ቀን ሥራውን ሁሉ እንዳልነበረ ያደርጋል (ማቴ 25÷41)::

[14] Cf. J.K. Howard, "New Testament Exorcism and its Significance Today," *ExpT* 96 (Jan 1985): 105–169



**ማር 1÷27-28**

[27]ሕዝቡ በሙሉ በመገረም፣ «ይህ ነገር ምንድን ነው? ሥልጣን ያለው አዲስ ትምህርት መሆኑ ነው! ርኩሳን መናፍስትን እንኳ ያዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታል!» እያሉ እርስ በርስ ተጠያየቁ:: [28]ወዲያውም ዝናው በገሊላ ዙሪያ ባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተዳረሰ::

ሕዝቡ የተደነቁበት በኢየሱስ ተግባር ሳይሆን፣ በቃሉ ኃይል ነበር:: ተግባሩ ቃሉን ለማጽናት ያገለግላል እንጂ ጉዳዩ የተገላቢጦሽ አይደለም:: ብርታት ያለው የኢየሱስ ቃል በማስተማርም ሆነ አጋንንትን በማዘዝ ችሎታው እጅግ የላቀ ነው::

**§ 43**
**የጴጥሮስን እማት መፈወሱ**
**(ማቴ 8÷14-17፤ ማር 1÷29-34፤ ሉቃ 4÷38-41)**

[ማር1:]29ወዲያው ከምኩራብ እንደ ወጡ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና ወደ እንድርያስ ቤት ገቡ [30]የስምዖን አማት በትኩሳት በሽታ (ኃይለኛ[ሉቃ]) ታማ ተኝታ ነበር፤ ስለ እርሷም ነገሩት፤ [31]ስለዚህም እርሱ ወደ ተኛችበተ በመሄድ (ጠጋ ብሎ በማጐንበስ ትኩሳቱን ገሠጸው[ሉቃ]) እጇን ይዞ አስነሣት፤ ትኩሳቱም ተዋት፤ ተነሥታም ታገለግላቸው ጀመር::

ኢየሱስ ከምኩራብ ወጥቶ ወዲያውኑ ወደ ጴጥሮስና እንድርያስ ቤት ሄደ:: ምናልባትም ሁለቱም ከቤተ ሳይዳ (ዮሐ 1÷44፤ «የዓሣ ቤት») ወደ ቅፍርናሆም ሳይዛወሩ አልቀረም፤ ወይም ደግሞ ቤተ ሳይዳ፣ ቅፍርናሆም አካባቢ ያለች ገጠር ልትሆን ትችላለች::

ጴጥሮስ የሚስቱን እናት እያስታመመ ነበር (1ቆሮ 9÷5 ጋር ያነ):: «ኃይለኛ ትኩሳት» ይዟት አልጋ ላይ ነበረች:: በዘመኑ የነበሩ ሐኪሞች ትኩሳትን፣ «ኃይለኛ» እና «ቀላል» በማለት ይከፍሉት ነበር:: ቀላል ትኩሳት የሚባለው ተራ ሕመም ነበር:: «ኃይለኛ ትኩሳት» የሚባለው ግን ወባን ጨምሮ ሌላ ዓይነት ጠንካራ ሕመም ሊሆን

ይችላል::[15] የጴጥሮስ አማት በጠና ታምማለች፤ ምናልባትም ከታመመች ጥቂት ቀን ሳይሆናት አልቀረም::

ይህን ፈውስ በተመለከተ ሦስቱም ወንጌሎች የተለያየ ዝርዝር አቅርበዋል:: ሉቃስ ጠጋ ብሎ በማጐንበስ ሲል፣ ማቴዎስ እጇን ደሰሳት ይላል፣ ማርቆስ ደግሞ እጇን ይዞ አስነሣት ይላል:: በዚሁ ጊዜ ኢየሱስ፣ «ትኩሳቱን ገሠጸው::» ቃሉ ምኩራብ ውስጥ ጋኔኑን የገሠጸበትን ሁኔታ ለመግለጽ ከተጠቀመበት ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው (ሉቃ 4÷35):: ይህም አንዳንዶችን ምናልባት ኢየሱስ በዚህና በሌሎች በሽታዎች መካከል የአጋንንት እንቅስቃሴን ሳይመለከት አልቀረም በማለት እንዲያስቡ ምክንያት ሆኗቸዋል:: ይሁን እንጂ ቁጥር 40 እና 41 በበሽታና በአጋንንት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ግልጽ አድርጓል:: ለሁሉም ዓይነት በሽታና የአእምሮ ሕመም አጋንንትን ተጠያቂ ማድረግ አንችልም፤ በኃጢአት የወደቀው ዓለም ተፈጥሮአዊ ውጤቶች ናቸው:: ሆኖም ኢየሱስ በሽታንና አጋንንትን መገሠጹ እርሱ የመጣው የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ መሆኑን ያሳያል:: የመንግሥቱ መምጣት በአጋንንት አማካይነት የሰይጣን ግዛት፣ እንዲሁም በሽታ ሞት የኤደን እርግማን ፍጻሜ የማግኘቱ ጅማሬ ልዩ ምልክት ነው::

የጴጥሮስ አማት ሙሉ በሙሉ በመፈወስዋ ወዲያውኑ ተነሥታ፣ «ታገለግላቸው ጀመር::» ይህ ሐረግ በአንድ የግሪክ ቃል ይጠቃለላል:: «ዲያቆን» (*diakoneo*) የሚለውን የምናገኘው ከዚሁ ሥርወ ቃል ነው:: ቃሉ በጣም የተለመደ ሲሆን ገበታ አካባቢ ቆሞ

[15] የትኩሳት ሕመምን በተመለከተ ኤደርሼም የሚከተለውን አስገራሚ ነገር ያቀርባል:: ታልሙድ ይህን ሕመም በዚሁ ስም (*Eshatha Tsemisrta*) ማለት፣ «የሚያቃጥል ትኩሳት» በማለት ይጠራዋል፤ ለዚህ ሕመም መድኃኒቱ አስማታዊ ኃይል ሲሆን ዋናው ሙሉ በሙሉ ብረት የሆነ ቢላዋ ላይ በተገመደ ጸጉር ከእሾህ ጭራሮ ጋር አብሮ ይታሠርና ዘፀአት 3÷2፣3 ከዚያ በኋላ 4 እና በመጨረሻም 5 ተደጋግሞ ይነበብና አንድ ዓይነት አስማታዊ ድግምት ከተነበነበ በኋላ እሾሁ ተቆርጦ ይጣላል» [Shabb. 37 a], (I:468).



ማስተናገድን (ምግብ ቤት ውስጥ ሳይሆን መኖሪያ ቤት ውስጥ) ያመለክታል:: በዚያ ዓይነት ፍጥነት ይህን ማድረግ መቻሏ ራሱ የሚገርም ነው:: ሰዎች በተፈጥሮአዊ መንገድ ከትኩሳት ቢፈወሱ እንኳ ኃይል ስለማይኖራቸው እስኪያገግሙ ድረስ ጊዜ መውሰዱ የማይቀር ነው:: ኢየሱስ ሲፈውስ ሙሉ በሙሉ ይፈውሳል፤ ይህች ሴት ሌላው ቀርቶ ትኩሳቱ ማስከተል ይችል ከነበረው ዐቅመ ቢስነት እንኳ ተፈትታለች::

ሉቃ 4÷40-41ከ
ማር 1÷32፤ ማቴ
8÷16 ጋር

[40]ፀሐይ መጥለቂያ ሳይም፣ (ጀንበር ከጠለቀች በኋላ[ማር]) የተለያየ ሕመም ያደረባቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤ እርሱም እጁን ጭኖ ፈወሳቸው:: [41]አጋንንትም ደግሞ፣ (መናፍሳትን በቃሉ አስወጣ [ማቴ]) «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!» እያሉና እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ:: እርሱ ግን ገሠጻቸው፤ ክርስቶስ[ሀ] መሆኑንም ያውቁ ስለ ነበር አንዳች እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም::

ማቴ 8÷17

[17]በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤ «እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም[ለ] ተሸከመ::»

*[ሀ]ሉቃ 4÷41 ወይም መሲሕ*
*[ለ]ማቴ 8÷17 ኢሳይያስ 53÷4*

ፀሐይ እየጠለቀች ነበር:: የከተማው ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ነበር:: ይህ የሰንበት ቀን በመሆኑና ሰንበት ደግሞ የሚጀምረው ከአርብ ፀሐይ መጥለቅ እስከ ቅዳሜ ፀሐይ መጥለቅ መሆኑን በማሰብ ሕዝቡ በተቻለ መጠን በተገቢው ሰዓት መጠቀምን መርጠዋል:: ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ በጣም የሚገርሙና ልብን የሚነኩ ትዕይንቶች አንዱ ነው:: የጀንበር ማዘቅዘቅ ስፍራውን ለምሽት

ሲለቅና ከዋክብት ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ በሽተኞችን ይዘው የሚመጡ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ቤት በሚወስደው መንገድ ላይ ተከማቹ:: ያለ ምንም ተቃውሞና ጥላቻ ጌታ ቤተሰቦቻቸው ይዘዋቸው በመጡ ሕመምተኞች መካከል እየሄደ በግል እያንዳንዱን ዳሰሰ [*heni hekasto*]:: ሕመምተኞች ተፈወሱ፤ የጌታን ፊት ጨምሮ የሰዎች ሁሉ ፊት ፈገግ አለ:: የደስታ እንባ በጉንጮቻቸው ይወርዱ ጀመር:: በቅፍርናሆም የደስታ ሳቅ አስተጋባ፤ እስከ ማለዳ ድረስ ያ ሁሉ ሕዝብ በዚያው በነበረበት ቦታ ሳይቆይ እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል:: በሚቀጥለው ጠወት ማለዳ ላይ ፈዋሹን ማግኘት ፈልገዋል::

እንደ ልማዳቸው አጋንንቱ ኢየሱስ የእግዚአብሐር ልጅ መሆኑን እየመሰከሩ ነበር:: ኢየሱስም ደግሞ እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም ነበር:: እርሱ ክርስቶስ መሆኑ ይፋ የሚወጣበት ጊዜ ገና አልደረሰም:: ሕዝቡ መሲሑን እየጠበቀ ቢሆንም ሊቀበሉት ግን ዝግጁ አልነበሩም:: አጥብቀው መሲሑን እየጠበቁ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ እነርሱ በጠበቁት መንገድ ይመጣል ብለው ነበር ያሰቡት:: ኢየሱስ ግን እነርሱ ከሚጠብቁት የተለየ፣ ከዚያም የበለጠ ነበር:: ስለሆነም የአጋንንቱ ምስክርነት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የበለጠ ነበር ማለት ነው፤ አጋንንት ለእግዚአብሐር መንግሥት መስፋፋት አስተዋፅዖ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ለአፍታ እንኳ ማሰብ የለብንም::

ማርቆስና ሉቃስ በጣም በሚገርም ግሥ ተጠቅመዋል:: «ክርስቶስ መሆኑንም ያወቁ ስለ ነበር» ሲሉ፣ ቀደም ሲል ይህን «ይገነዘቡ» እንደ ነበር ነው የሚያመለክተው:: የኢየሱስ ማንነት ለአጋንንቱ አዲስ አልነበረም:: ከረጅም ጊዜ በፊት ማንነቱን አውቀዋል::

እዚህ ላይ ማቴዎስ፣ «በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው» የሚለው ኢሳይያስ 53÷4 ላይ ያለው ትንቢት መፈጸሙን ያመለክታል:: ከዐውዱ አንጻር



ስንመለከተው፣ ይህ ስቅለቱን የሚያመለክት መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ጴጥሮስም ቢሆን በ1ጴጥሮስ 2÷24 መሠረት ከመስቀል ላይ ሞቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነበር የተጠቀመበት:: ሆኖም ማቴዎስ ከተፈጸሙት ፈውሶች ጋር በተያያዘ ሁኔታ አቅርቦታል:: ታዲያ፣ ኢሳይያስ 53÷4 የሚናገረው ስለ መንፈሳዊ ደዌያችን ፈውስ ነው ወይስ ስለ አካላችን ፈውስ? የሚናገረው ስለ ሁለቱም ነው! ኢየሱስ ከፊል እኛነታችንን በመፈወስ ብቻ አያበቃም፤ አካላችንን፣ ነፍሳችንንና መንፈሳችንን ሁሉ ነው የሚወደው:: ከዚህም በላይ መስቀሉ ሁለንተናችን የሚፈወስበት መንገድ ነው:: አሁን ባለው ሁኔታ ነፍሳችን ተዋጅታለች:: ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ደግሞ በመስቀሉ በኩል አካላችን ይታደሳል:: ምንባቡ ስለ ጤንነትና ብልጽግና የተሰጠ ተስፋ አይደለም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ የፈወሳቸው ሁሉ የኋላ ኋላ ታምመው ሞተዋል:: ይልቁንም እነዚህ ፈውሶች ወደፊት የሚሆነውን የሚያመለክቱ ትንቢታዊ ተስፋዎች ናቸው:: ወደፊት ለዘለቄታውና ፍጹም በሆነ ሁኔታ እንደምንዋጅ ብስራት ነጋሪዎች ናቸው::

**§ 44**
**የመጀመሪያው የገሊላ አገልግሎት**
**(ማቴ 4÷23-25፤ ማር 1÷35-39፤ ሉቃ 4÷42-44)**

ኢየሱስ ከፍተኛ መከናወን እያገኘ ነበር:: ስብከቶቹና የሚያደርጋቸው ፈውሶች ብዙዎችን እየሳቡ ነበር:: ደቀ መዛመርቱ ተስፋ ያደረጉት የዚህ ዓይነቱን ስኬት ነበር:: በእንዲህ ዐይነቱ ዝነኝነት ውስጥ እያለ ግን ኢየሱስ ገለል ሲል እናያለን:: ደቀ መዛሙርቱ እርሱን በማጀብ ወደ አደባባይ መውጣትን ፈልገው ነበር:: ኢየሱስ ግን ቅድሚያ የሚሰጠው የተለየ ነገር መኖሩን አሳየ::

**ማር 1፥35-37**
**ከሉቃ 4፥42 ጋር**

35ማለዳም ገና ጐሕ ሳይቀድ፣ ኢየሱስ ተነሥቶ
ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ
ጀመር። 36ስምዖንና ባልደረቦቹም ተከትለው ይፈልጉት
ጀመር። 37ባገኙትም ጊዜ፣ «ሰዉ ሁሉ ይፈልግሃል»
አሉት። (ከእነርሱ ተለይቶ እንዳይሄድ ሊከለክሉት
ሞከሩ።[ሉቃ])

**ሉቃ 4፥43**

43እርሱ ግን፣ «ወደ ሌሎቹም ከተሞች ሄጄ
የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል መስበክ ይገባኛል፤
የተላክሁት ለዚሁ ዐላማ ነውና» አላቸው።

ሌሊቱን ብዙ ከፈወሰ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲተኙ አደረገ። ምናልባትም ፈገግታ ፊታቸው ላይ እየታየ ሳይተኙ አልቀረም። ኢየሱስም እንዲሁ ዕረፍት አደረገ፤ እንቅልፍ የወሰደው ግን አይመስልም። ከጥቂት ሰዓት በኋላ ከተኛበት ተነሣ፤ ቀስ ብሎ ልብሱን ለበሰና ፀሐይ ከመውጣቷ በጣም ቀድሞ ከቤት ወጥቶ ሄደ። ፀጥተኛ ቦታ ሆኖ መጸለይን ከእንቅልፍ ይልቅ ይመረጠው ነበር። ጠዋት የኢየሱሱ መኝታ ባዶ መሆኑ ሲታወቅ ስምዖን ሕዝቡን እየመራ ኢየሱስን ፍለጋ ሄደ።

ኢየሱስን ባገኙ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «ሰው ሁሉ ይፈልግሃል» አለው። የተቀሩትም ኢየሱስ ተለይቷቸው እንዳይሄድ ለማድረግ ሞከሩ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ይንቀሳቀስ የነበረው በአባቱ ዕቅድ መሠረት እንጂ ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት አልነበረም። በአመለካከቱ ጠባብ ስላልነበር በአንድ ከተማ ብቻ መስበክ አልፈለገም። የእግዚአብሔር መንግሥት እነዚያ ደቀመዛሙርት ከሚጠብቁት በላይ እጅግ ሰፊ ነው።



**ማቴ 4፥23-25**
**ሉቃ 4፥44 ጋር**

23ኢየሱስም በምኵራባቸው እያስተማረ፣
የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ፣
በሕዝቡ መካከል ማንኛውንም ደዌና ሕመም እየፈወሰ
በመላው ገሊላ (ይሁዳ[ሉቃ]) ይዞዋወር ነበር። 24ከዚህም
የተነሣ ዝናው በመላዋ ሶርያ ተሰማ፤ ሕዝቡም በተለያዩ
በሽታዎች የታመሙትን፣ በክፉ ደዌ የሚሠቃዩትን፣ አጋንንት ያደረባቸውን፣
የሚጥል በሽታ ያለባቸውን፣ ሽባዎችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤ ፈወሳቸውም።
25ከዚህም የተነሣ ከገሊላ፣ ከዐሥሩ ከተሞች፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳኖስ ማዶ
የመጡ ብዙ ሰዎች ተከተሉት።

ከሕዝቡ ፍላጐት በተቃራኒ ኢየሱስ የመጀመሪያውን የገሊላ ጉዞ አደረገ። የሉቃስ አቀራረብ ከማቴዎስና ከማርቆስ የተለየ ነው። እርሱ የሚነግረን ኢየሱስ በይሁዳ ምኵራብ እንደ ሰበከ ነው። የንጉሥ ጀምስ ትርጒም፣ «ገሊላ» በማለቱ መጠነኛ ልዩነት አለ። በአመዛኙ ግን ሉቃስ የጻፈው፣ «ይሁዳ» በማለት ነው። ይሁን እንጂ የሐሳቡ ቅደም ተከተልና የኢየሱስ አገልግሎት እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም ተጓዳኝ ምንባቦቹ የሚያመለክቱት ኢየሱስ የሄደው ወደ ገሊላ መሆኑን ነው። ስለሆነም ሉቃስ ማለት የፈለገው፣ «በይሁዳ ምኵራብ» ሳይሆን፣ «በአይሁድ አገር ባሉ ምኵራቦች» ነው ወደሚል መደምደሚያ እንደርሳለን፤ ይህ ደግሞ ያለ ጥርጥር ገሊላን ይጨምራል (ሉቃ 1፡5፤ 6፡17፤ 7፡17፤ 23፡5 ጋር ያነ)። በሌላ አነጋገር ሉቃስ እየተናገረ ያለው ስለ መልክዓ ምድራዊ ክልል ብቻ ሳይሆን ስለ ሕዝብ ነበር ማለት ነው።

የኢየሱስ ዝና እንደ ሰደድ እሳት ይስፋፋ ጀመር። ማቴዎስ ከሐሳቡ ወጣ በማለት በአጋንንት የተጠቁትንና ሽባዎችን፣ እንዲሁም የሚጥል በሽታ[16] የነበረባቸውን ጨምሮ ኢየሱስ ማንኛውንም ሕመም

---

[16] የሚጥል በሽታ "epilepsy" (*seleniazomai*) የሚለውን መተርጐም አስቸጋሪ ነው። ሥርወ ቃሉ፣ «በጨረቃ የሚነካ» ማለት ነው። ምናልባትም የሚጥል

መፈወስ እንደሚችል ይናገራል:: እንደ ፈዋሽነቱ ዝናው ከእስራኤል ድንበር ዘልቆ ሄዷል:: በሰሜን ካለው ሶሪያ፣ በደቡብ እስካለው ይሁዳ፣ ከኢየሩሳሌም እስከ ዐሥሩ ከተሞች ድረስ ሰዎች ሕመምተኞቻቸውን ወደ ኢየሱስ አመጡ:: አንዳቸውም እንኳ የፈለጉትን ሳያገኙ አልተመለሱም:: እርሱ ያላስተካከለው፣ እርሱ ያልዳሰሰው አንድ እንኳ አልነበረም::

**§ 45**
**የለምጻሙ መንጻት**
**(ማቴ 8÷2-4፤ ማር 1÷40-45፤ ሉቃ 5÷12-16)**

[ሉቃ5:]12 ኢየሱስ ከከተሞች በአንዱ በነበረበት ጊዜ፤ አንድ ለምጽ[u] የወረሰው ሰው በዚያው ከተማ ነበር፤ ይህ ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ በፊቱ ተደፋና (ከፊቱ በመንበርከክ[ማቴ፣ማር]) «ጌታ ሆይ፤ ብተፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትችላለህ» ብሎ ለመነው::

[ማር1:]41 ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ «እፈቅዳለሁ፣ ንጻ» አለው:: ከበሽታውም ተፈወሰ::

*[u]12 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል::*

ኢየሱስ ለመጀመሪያ የገሊላ ጉዞው ወደዚያ ባቀናበት ጊዜ ከአንድ ለምጻም[17] ጋር ተገናኘ:: ለምጽ ተብሎ የተተረጐመው ቃል፣ "leprosy" የተሰኘና "Lepo" ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም፣ «እንደ ቅሪፊት መላጥ» ማለት ነው:: ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ (ዘኁ 12÷10፤ 2ነገ 5÷27) በሁለቱም፣ «እንደ በረዶ ነጭ» ከሚል ሐረግ ጋር ተያይዞአል:: ስለሆነም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ከpsoriasis እና ዝሆኔ (elephantiasis) ጋር አንድ ሳይሆን እንዳልቀረ ያስባሉ:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ሁኔታዎች አንዱ እንኳ በዘሌዋውያን 13[18] ከቀረበው ዝርዝር ገለጻ ጋር አይስማማም::

ለምጻሙ ወደ ኢየሱስ መጥቶ በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ ከዚያም በግንባሩ ተደፋ:: ድርጊቱ ትክክል አልነበረም፤ ምክንያቱም ማንኛውም ለምጻም ከሰዎች እንዲገለል ይጠበቅበት ነበር::

ለምጽ ያለበት ሰው ሐዘንተኛ የሚጐናጸፈውን መጐናጸፊያ ይለብስና በመንገድ በሚያልፍበት ጊዜ ሁሉ፣ «ርኩስ ነኝ!» እያለ መጮኽ ነበረበት፤ ይህም በአንድ በኩል እንዲጸለዩለት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሱ እንዲርቁ ለማድረግ ነበር:: ለሳምንታ የሚሰጠው ሰው አይኖርም፤ አለጋው ወደ መሬት እስኪጠጋ ድረስ ዝቅ እንዲል ይደረጋል:: እርሱ የነካው ነገር ሁሉ እንደ ርኩስ ይቆጠር ነበር:: ማንኛውም ሰው ከለምጻም ስድስት ክንድ ያህል መራቅ ነበረበት፤ እርሱ ካለበት አቅጣጫ ነፋስ እየመጣ ከሆነ ግን መቶ ጫማ ያህል እንዲርቅ ይጠበቅ ነበር:: ሜይር የተባለው የአይሁድ መምህር ለምጻም ካለበት መንገድ የተገዛ እንቁላል ለመብላት ፈቃደኛ እንዳልነበር ይነገራል:: ሌላው የአይሁድ መምህር ደግሞ ለምጻሞችን ሲያይ እነርሱን ለማባረር ሁሌም ድንጋይ እንደሚወረውር ተነግሮአል፤ ሌሎችም ይደበቁ ወይም ርጠው ያመልጡ ነበር (ኢደርሺም፣ ገጽ 495)::

---

በሽታን፣ አንድ ዐይነት አካላዊ ሕመምን ወይም ዕብደትንና ሶሥነ ልቦናዊ መታወክን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን የነበሩ ሰዎች ከጨረቃ ጋር አያይዘው ሳያስቡ አልቀረም:: ማቴ 4÷24 ላይ ይህን ቃል መተርጐም አዳጋች መሆኑን J.M. Ross, "Epileptic or Mooanstruck? *BT* 29 (Jan 1978): 126-128 ላይ ማብራሪያ አቅርቧል::

[17] ማቴዎስ እንደሚያቀርበው ይህ ለምጻም ከኢየሱስ ጋር የተገናኘው ከተራራው ስብከት በኋላ ከተራራው በወረደ ጊዜ ይመስላል:: ይሁን እንጂ ከማርቆስና ከሉቃስ ጋር አያይዘን ስንመለከተው ጉዳዩ ቅደም ተከተላዊ ሳይሆን፣ አጉልቶ ለማሳየት ከሚደረግ ሙከራ ጋር የተያያዘ መሆኑን እንረዳለን::

[18] Cf. Cochrane, "No Wonder you're Confused about Leprosy," *Eternity* (September 1965): 12-14, K.P. Gramberg "Leprosy and the Bible," *BT* (Jan 1960): 10-23; and J.L. Swellengrebel, "Leprosy and the Bible," *BT* (April 1960): 69-81.

በመሠረቱ አንድ ሰው ወደ ለምጻሞች ከተጠጋ፣ «ርኩስ ነኝ፣ ርኩስ ነኝ፣» በማለት የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት ነበረባቸው (ዘሌ 13÷45-46):: ይህ ለምጻም ግን ወደ ኢየሱስ በመቅረብ፣ «ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትችላለህ» በማለት ለመነው:: ለልመናው ምንም ቅድመ ሁኔታ አልነበረም:: ሌላውን ውርደት ሳይጨምር እርሱን ለማባረር በሚያደርጉት ሙከራ አንዳንዴ ጉዳት ሊያደርሱበት ከሚችሉ የአይሁድ መምህራን ይሸሽ ነበር::[19] ከዚህም በላይ በዚህ ሁኔታ ከለምጽ ስለ ነጻ ሰው ከብሉይ ኪዳን አንድ ምሳሌ እንኳ ማቅረብ አይቻልም ነበር:: ለምጻም ስለ መንጻቱ ብሉይ ኪዳን የሚናገረው አንድ ቦታ ብቻ ላይ ሲሆን ይህም ከኤልሳዕና ከንዕማን ታሪክ የምንመለከተው ነው (2ነገ 5÷1-19):: እዚህም ላይ ቢሆን የለምጻሙ አካል ስለ መዳሰሱ አይናገርም፤ በዚህ ላይ ንዕማን አይሁዳዊ እንዳልነበር ይታወቃል:: ይህ ለምጻም ኢየሱስ ሊፈውሰው እንደሚችል ወይም ሊፈውሰው ፈቃደኛ እንደ ሆነ እርግጠኛ የሚያደርገው ጥቂት ምክንያት ብቻ ነበረው:: ቀጥተኛ ከሆነ የእግዚአብሔር ተአምር ውጪ ለምጻም ስለ መፈወሱ አንድ ምሳሌ እንኳ ማቅረብ አለመቻሉ ራሱ በጣም የሚገርም ነው::

ኢየሱስ፣ «ለሰውየው በመራራት»[20] እጁን ዘርግቶ ዳሰሰው (*hapto*):: ለምጻምን መንካት ማንኛውንም ሰው ያረክሳል:: ይሁን እንጂ

[19] ኤደርሼይም እንደሚለው (ገጽ 493) «አንድ ሰው ለምጻም መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ከሃይማኖት መምህራን ይህ ነው የማይባል ግፍ ይፈጸምበት ነበር:: ምናልባትም ሰውየው በግንብ ከተከለሉት ከተሞች ውጪ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፤ ይህን ተላልፎ ከተገኘ 39 ጊዜ በጅራፍ ይገረፋል::» ይሁን እንጂ C.R. Kazmierski, "Evangelist and Leper: A Socio-Cultural Study of Mark 1:40-45," *NTS* 38 (1992): 37-50 ላይ እንደሚለው ከሆነ ይህ ደንብ በትንንሽ መንደሮች በተለይም ከኢየሩሳሌም በጣም ርቀው በነበሩበት ዘንድ 'ጠንከር ባለ ሁኔታ ተግባር ላይ አይውልም ነበር::

[20] C.H. Cave, "The Leper: Mark 1:40-45," *NTS* 25 (1979): 245-250 ላይ የሐሳብ ልዩነቱን አስመልክቶ፣ «በመራራት» [*splanchnistheis*] ሳይሆን፣ «በመቆጣት» [*ogistheis*] የሚል እንደ ሆነ ያመለክታል:: ይህ ደግሞ ስለ ፈውስ የተነገረውን ታሪክ ወደ ሌላ ዐይነት አለመግባባት እንዲያመራ ያደርገዋል:: ስለዚህም



ኢየሱስ ለምጻሙን በመንካቱ አልረከሰም፤ ይልቁንም ለምጻሙ ንጹሕ ሆነ:: እርግጥ ነው፣ ኢየሱስ በቃል ብቻ ሰውየውን መፈወስ ይችል ነበር:: እንደሚታወቀው የሹሙን ልጅ የፈወሰው ከ32 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነበር (ዮሐ 4÷45-54):: ታዲያ፣ እዚህ ላይ እንደዚያ ያላደረገው ለምን ነበር? ሰውየው የተለያዩ ችግሮች እንደ ነበሩበት በመረዳቱ ነበር፤ (1) ከለምጹ መንጻት ነበረበት፤ (2) የሌላው ሰው እጅ በመዳሰስ የሚገኘውን ደስ የሚል ስሜት መለማመድ ነበረበት:: ለረጅም ጊዜ በመገለልና በሌሎች በመናቅ ኖሯል፤ አሁን ግን ከማኅበረሰቡ ጋር መቀላቀል ነበረበት፤ (3) በለምጹ ምክንያት ከደረሰበት ማኅበረሰባዊ መገለልም ነጻ መሆን ነበረበት:: ስለሆነም መንጻቱ ሦስት ገጽታዎች፣ ማለትም አካላዊ፣ ስሜታዊና ማኅበረሰባዊ አንድምታዎች ነበሩት ማለት ነው:: ለምጹን በማንጻት ኢየሱስ አካላዊ ጉድለቱን አሟላ:: ሰውየውን በመዳሰስ ስሜቱን አገለገለ:: ወደ መቅደስ ሄዶ ተገቢውን መባ እንዲያቀርብም በማድረግ ማኅበረሰባዊ ጉድለቱን አሟላለት::

**ማር 1÷43-45 ከ ሉቃ 5÷15-16 ጋር**

43ኢየሱስም ሰውየውን አጥብቆ በማስጠንቀቅ
እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ 44«ለማንም አንድ ነገር እንኳ
እንዳትናገር ተጠንቀቅ፤ ነገር ግን ምስክር እንዲሆናቸው
ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ስለ መንጻትህም ሙሴ
ያዘዘውን መሥዋዕት አቅርብ» አለው:: 45ሰውየው ግን በሄደበት ሁሉ ነገሩን በሰፊው
አወራ፣ ወሬውንም አሠራጨ:: በዚህ ምክንያት ኢየሱስ ወደ ማንኛውም ከተማ በግልጽ
መግባት አልተቻለውም፤ ከዚህም የተነሣ ከከተማ ውጭ በሚገኙ ሰዋራ ቦታዎች መኖር
ጀመረ፤ ሰዎች ግን ከየአቅጣጫው እርሱ ወዳለበት መምጣት አላቋረጡም:: (ይሁን

ታሪኩ የሚከተሉት ዐይነት ሐሳቦችን ሊያመለክት ይችላል ማለት ነው፤ (1) ኢየሱስ ጸጥ እንዲል ካዘዘው በኋላ በመጣበት ሁኔታ የሸኘው መሆኑን፤ (2) ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ [*embrimesamenos*] መጠቀሙን፤ (3) ዐውዱ ሌላ ዐይነት አለመግባባት የሚያሳይ መሆኑን ያመለክታል ማለት ነው:: ይሁን እንጂ ልዩነቱ በጣም ደካማ በመሆኑ መከተል አይቻልም ...:: ስለሆነም ዐውዱን በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መሠረት እንቀበላለን ማለት ነው::

እንጂ ስለ እርሱ የሚወራው ወሬ ይበልጥ እየሰፋ ሄደ፤ እጅግ ብዙ ሰዎችም ለመፈወስ ይሰበሰቡ ነበር:: 16ኢየሱስ ግን ብዙ ጊዜ ወደ ገለልተኛ ስፍራ ወጥቶ ይጸልይ ነበር(ሉቃ)::

አንድ ሰው ከለምጽ መንጻቱን በተመለከተ ሙሴ ማረጋገጫ መንገድ ደንግጎ ነበር (ዘሌ 14-15):: ለምጻም በእስራኤል ማኅበረሰብ ውስጥ በጣም የተናቀ ከመሆኑ የተነሣ ከለምጹ ከነጻ በኋላ እንኳ የመገለሉ ጥላ እንዳጠላበት ይቀጥል ነበር:: የሚቀርበው መሥዋዕት ሰውየው ከለምጽ በመንጻቱ በካህናቱና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘቱ ውጫዊ ምልክት ነበር:: ስለሆነም ያለ ምንም መገለልና ጥላቻ ሰውየው እንደ ገና ከማኅበረሰቡ መቀላቀለ ይችላል ማለት ነው::

ኢየሱስ ሰውየው ለማንም እንዳያወራ ያስጠነቀቀው ለምን ነበር? በመጀመሪያ ደረጃ፤ ኢየሱስ ላይ የነበረው ተቃውሞ እየጠነከረ በመምጣቱ ሰውየው ከኢየሱስ ጋር ግንኙነት እንዳለው ከታወቀ ከለምጽ የመንጻቱን ጉዳይ ካህናቱ አቅልለው ሊመለከቱት ይችላሉ፤ ስለሆነም፣ ለራሱ ለለምጻሙ ጥቅም ሲባል ነበር ማለት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ፣ ለኢየሱስ ጥቅም ሲባል ነበር:: ሰዎች እስኪያጨናንቁት ድረስ የኢየሱስ ዝና በአስገራሚ ሁኔታ እያደገ ሄዶ ነበር:: ለምጻሙ በየመንገዱ እያወራ በመሄዱ፣ ኢየሱስ በግልጽ ወደ ከተማው መግባት እስኪሳነው ድረስ[21] እጅግ በጣም ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ተሰብስቦ ነበር፤ እንግዲህ ኢየሱስ እንዳያወራ ያስጠነቀቀው እንዲህ ዐይነቱ መጨናነቅ እንዳይኖር ነበር ማለት ነው (ማር 1÷45):: በተጨማሪም ከሉቃስ 5÷15 እንደምንመለከተው የኢየሱስ በአካባቢው መገኘት የማያስፈልግ መጓጓትና ስሜታዊነት ፈጥሮ ነበር:: ሕዝቡ ከበሽታ መፈወስንና ከዚህም

---

[21] C.R. Kazmierski, "Evangelist and Leper: A Socio-Cultural Study of Mark 1:40 -45," *NTS* 38 (1992): 37-50 እንደሚያመለክተው ወደ ከተማው ለመግባት ጭንቅ የሆነበት ለለምጻሙ እንጂ ለኢየሱስ አልነበረም (ማር 1÷45):: ይሁን እንጂ፣ «ኢየሱስ» የሚለውን ቃል በግሪኩ ጽሑፍ ባናገኝም ተጓዳኙ (ሉቃ 5÷15-16) ወደ ከተማው ለመግባት ጭንቅ የሆነበት ለኢየሱስ እንጂ ለለምጻሙ እንዳልነበረ በግልጽ ያመለክታል::



ጋር ያለውን አስደናቂ ትዕይንት ማየት በጣም ይፈልጉ ነበር:: ይህ ደግሞ፣ ስለ እውነተኛ ማንነቱ እንዳያስተምር ሁኔታውን አዳጋች አድርጎታል:: በመጨረሻም፣ በኢየሱስና በሃይማኖት ባለሥልጣኖቹ መካከል የነበረው ውጥረት በጣም እየተከረረ የመጣበት ወቅት ነበር:: ኢየሱስ ግን ትክክለኛው ጊዜ ከመምጣቱ በፊት የማያስፈልግ ግጭትና አለመግባባት እንዲኖር አልፈለገም::

በዚህ ሁሉ ዝነኝነትና ታዋቂነት መካከል እያለ እንኳ ኢየሱስ ለጸሎት ወደ ገለልተኛ ቦታ ይሄድ ነበር (ሉቃ 5÷16):: ኢየስስ ሥራ በበዛበት መጠን የዚያኑ ያህል በብዛት[22] ይጸልይ ነበር:: ይህ ማንኛችንም ልንማረው የሚገባን ነገር ነው:: የዕለት ተዕለት ፕሮግራማችን የመጣበቡን ያህል ከጸሎት የሚገኘውን ኃይልና ትክክለኛ ምሪት ካልተቀበልን በቀር በአግባቡ ተግባራችንን መወጣት አንችልም::

**§ 46**
**የሽባው መፈወስና ይቅር መባል**
**(ማቴ 9÷1-8[23] ማር2÷1-12 ሉቃ 5÷17-26)**

ኢየሱስ የመጀመሪያው የገሊላ አገልግሎቱ ማብቂያ አካባቢ ላይ እንደገና በቅፍርናሆም እንደ ነበር እንመለከታለን፤ ያረፈው በአመዛኙ በጴጥሮስ ቤት ሳይሆን አልቀረም (ማር 1÷29):: የለምጻሙና (ከመጀመሪያው የአገልግሎት ጉዞው የምንመለከተው ይህን ብቻ ነው) የሽባው መፈወስ የኢየሱስን ሥራና አንዳንድ ነገሮችን የሚወክሉ ናቸው፤ (1) ኢየሱስ ከአካላዊ ደኅንነታቸው የበለጠ የሚያስብ መሆኑን፤ (2) እነዚህ ፈውሶች ከዚያ ቀደም ማንም ያደረጋቸው አልነበሩም:: ከዚያ በፊት እንዲህ ያለ ነገር ተደርጎ አያውቅም ነበር (ማር 2÷12 ጋር ያነ)፤ (3)

---

[22] እዚህ ላይ ግሡ የአሁን ጊዜ (*hypohoron*) መሆኑን መረዳት ያሻል::
[23] ማቴዎስ ስለ ርዕሰ ጉዳይ እንጂ ስለ ቅደም ተከተል እየተናገረ አለመሆኑን እንደ ገና መረዳት አለብን፤ ስለሆነም የገሊላን ባሕር ስለ መሻገሩ ያቀረበው መግቢያ (1÷9) የአጻጻፉን ፍሰት እንጂ ትክክለኛ እንቅስቃሴውን ለማመልከት አልነበረም::

ፈውሱ መለኮታዊ ኃይልን ያመለክታል፤ (4) ኢየሱስ ያገለግል የነበረው በዘመኑ ከነበሩ የሃይማኖት መምህራን አሠራር በተቃራኒው ነበር::

አሁን በምንመለከተው ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢየሱስ ላይ ስለ ተነሣ የሃይማኖት ባለ ሥልጣናት ተቃውሞ እናያለን:: ብዙም ሳይቆይ ከአራት አቅጣጫ ተቃውሞ ማቅረባቸው ግልጽ ይሆናል (McGarvey, ገጽ 183)፤ (1) ኢየሱስን በተሳዳቢነት መክሰሳቸው፣ (2) የቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች ወዳጅ ነህ ማለታቸው፣ (3) የመቅደስ ሥርዓትን (እንደ መተጣጠብ፣ ጾምና ሌሎችም የመሳሰሉ) ችላ ትላለህ ብለው መውቀሳቸውና፣ (4) ሰንበትን ስለመሻር መወንጀላቸው::

ማር 2÷1-2

[1]ኢየሱስ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆም
እንደ ተመለሰ፣ ወደ ቤት መግባቱን ሕዝቡ ሰማ:: [2]ስለዚህ
ከበሩ ውጭ እንኳ ሳይቀር ስፍራ እስኪታጣ ድረስ ብዙ
ሕዝብ ተሰበሰበ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ሰበከላቸው::

ሉቃ 5÷17-21
ከማር 2÷3-4፤
ማቴ 9÷2 ጋር

[17]አንድ ቀን ኢየሱስ እያስተማረ ነበር፤ በዚያም
ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮች ሁሉ እንዲሁም ከኢየሩሳሌም
የመጡ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ተቀምጠው ነበር፤
ይፈውስም ዘንድ የጌታ ኀይል ከእርሱ ጋር ነበረ:: [18]በዚያን
ጊዜም፣ (አራት[ማር]) ሰዎች አንድ ሽባ በዐልጋ ተሸክመው አመጡ፤ ኢየሱስ ፊት
ለማኖርም ወደ ቤት ሊያስገቡት ሞከሩ፤ [19]ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ቤቱ ውስጥ
ማስገባት ስላቃታቸው፣ ጣራው ላይ ወጥተው (የቤቱን ጣራ እርሱ ባለበት በኩል
ነድለው ቀዳዳ በማበጀት[ማር]) የቤቱን ክዳን በመንደል በሽተኛውን ከነዐልጋው በሕዝቡ
መካከል ቀጥታ ኢየሱስ ፊት አወረዱት::

[20]ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ፣ «አንተ ሰው፤
(አይዞህ አንተ ልጅ[ማቴ]) ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል» አለው::
[21]ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም፣ «ይህ አምላክን በመዳፈር
እንዲህ የሚናገር ማን ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር
በስተቀር ኀጢአትን ሊያስተሰርይ ማን ይችላል?» ብለው
ያስቡ ጀመር::



ኢየሱስ ማንም ሳያውቅ እንደ ምንም ወደ ከተማ ገብቶ ለጥቂት ቀን ማረፍ ፈለገ (ምናልባት በጴጥሮስ ቤት):: ኢየሱስ የመመለሱ ወሬ በመስፋፋቱ ግን ሕዝቡ እንደ ገና በደጃፉ ተከማቸ:: ኢየሱስ ሕዝቡን ዕለት ዕለት ማስተማር ጀመረ:: ትምህርቱ ቀጣይነት ያለውና ሕዝቡም ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮች ሁሉ ወደ እርሱ እየጐረፈ መሆኑን ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ሰሙ:: ቤቱ በሰዎች ተሞልቶ ነበር::[24]

ከሁኔታው መመልከት እንደሚቻለው ይህ ቤት፣ «በመካከለኛ ደረጃ» ያለ ሰው ቤት ይመስላል:: ዙሪያውን ቤቶች ያሉበት ባለ አራት ማዕዘን አደባባይ ሳይኖረውም አልቀረም በማዕዘኑ አንድ በኩል ወደ መንገድ የሚያስኬድ በር ነበር:: ምናልባትም መከላከያ በሚሆን መደገፊያዎች የተከበበ ክፍት ጣራ ያለው ባለ ሁለት ፎቅ ቤት ሳይሆን አይቀርም:: ቤተሰቡ ፀሐይም ሆነ ዝናብ ሳይነካቸው ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ለመዘዋወር እንዲያስችላቸው ግቢው ዙሪያውን በዳስ የተከበበ ሊሆን ይችላል:: እንግዲህ ኢየሱስ ሕዝቡን ያስተምር የነበረው በዚያ በተጨናነቀ ግቢያ ውስጥ እንደ ሆነ በዐይነ ሕሊናችን መመልከት ይቻላል:: ከግቢው በር ፊት ለፊት ወደ ቤት መግባት የሚሞክሩ ብዙ ሰዎች ተደርድረው ነበር::

ሉቃስ (5÷17) ለዚያ ብዛት ለነበረው ሕዝብ ምን እየሆነለት እንደ ነበር ሲያመለክት፣ «ይፈውስም ዘንድ የጌታ ኀይል ከእርሱ ጋር ነበረ» ይላል:: አራት ሰዎች ይህን ሽባ «ቃሬዛ» ሊባል በሚችል «ዐልጋ» ተሸክመው መጡ:: ምናልባትም ዐልጋ የተባለው ዙሪያውን በአጠና የተሠራ ወይም በቆዳ የተወጠረ ወሳንሳ ሊሆን ይችላል:: ይህ ምስኪን ሰው በዚህ ሁኔታ ሰዎች እየተሸሙት ረጅም ጊዜ አሳልፏል:: ስለ ሰውየው አጠቃላይ ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ማወቅ እንፈልግ ይሆናል::

[24] ሉቃስ የአሁን ጊዜ በመጠቀም ፈሪሳውያን «እዚያው እንደ ነበሩ» ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር ለጥቂት ቀኖች በዚያው አካባቢ ነበሩ ማለት ነው:: ስለሆነም ኢየሱስ ሲያስተምር ሲሰሙ ይህ የመጀመሪያቸው አልነበረም::

ሽባ የነበረው ከተወለደ ጊዜ አንሥቶ ነበር? በኋላ የደረሰበት የአንገት ስብራት ውጤት ይሆን? ባለ ትዳርና የሚረዳው ቤተሰብ ያለው ይሆን? ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ይሁን እንጂ በአይሁድ ባሕል መሠረት ይህ ሰው ሊኖረው የሚችለው ዕድል ምፅዋት መጠበቅ ብቻ ነበር፤ ወዳጆቹ ይሸከሙና ሕዝብ በሚበዛበት አውራ መንገድ ዳር ያስቀምጡታል፤ እርሱም ከአላፊ አግዳሚው ምፅዋት ይጠብቃል፡፡

ይህን ሽባ ወደ ኢየሱስ ተሸክሞ የመሄድን ሐሳብ ያመጣው ማን እንደ ሆነ አናውቅም፡፡ ሆኖም፣ ምን ያህል አድካሚ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፡፡ ከበሩ ውጪ የተደረደሩ ሰዎች መንገድ የሚለቁ ዐይነት አልነበሩም፡፡ ምናልባት አንድ ትንሽ ሕፃን በእግራቸው ሥር ሾልኮ ማለፍ እንጂ ቃሬዛ የተሸከሙ አራት ትልልቅ ሰዎች ጨርሶ ማለፍ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ወደ ቤቱ ጣራ ወጡ፡፡ ምናልባትም ከውጪ በኩል ወደ ጣራው የሚያወጣ ደረጃ ይኖር ይሆናል ብሎ ማሰብ ይቻላል፤ ሆኖም እንዲህ ዐይነቱ ለሌባ ጥቃት ስለሚያጋልጥ የሚያዋጣ ሐሳብ አይመስልም፡፡ ይልቁንም በጐረቤት ቤት በኩል አድርገው ወደ ጴጥሮስ ቤት ጣራ ወጡ ማለቱ የተሻለ ይሆን ይሆናል፡፡ ብዙ ጊዜ ቤቶች የተጠጋጉ በመሆናቸው ይህን ማድረግ ይቻላል፤ ሆኖም የሌሎችን ትኩረት መሳቡ የማይቀር ነው፡፡ እነርሱም እንደዚያ ማድረግ ገና መጀመራቸው ነበር፡፡ ይህን ሰው በዚያች ቀን ወደ ኢየሱስ ሊያመጡ የፈለጉበት ምክንያት ምንድነው? ምክንያቱ የኢየሱስን እንቅስቃሴ ማወቅ ባለመቻሉ ነው፤ ዛሬ እዚያ ከዋለ፣ ነገ ወደ ሌላ ቦታ ሊሄድ ይችላል፡፡ ምናልባትም ያላቸው ዕድል ይህ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ ቆሞ የነበረበት መጠለያ ወይም ዳስ ጣራ ላይ ወጡ፡፡ የት እንደ ነበረ ማየት አይችሉም፤ ሆኖም ሕዝቡ ፊታቸውን አዙረው ካሉበት አቅጣጫ የት እንደ ነበር ማወቅ ይችላሉ፡፡ መጠለያው ከሣር ወይም ፍርግርግ እንጨቶች የተሠራ ነበር፡፡ ማርቆስ፣ «ቀዳዳ» በማበጀት (2÷4) የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሰውየውን ለማውረድ የሚያስችላቸውን ክፍት



ቦታ እስኪያገኙ ድረስ ሣሩን፣ ጭቃውንና እንጨቶችን አንድ በአንድ አነሡ፡፡[25] ግቢው ውስጥ ኢየሱስ ፊት ቆመው የነበሩ ሰዎች እየሆነ የነበረውን ማየት ይችሉ ነበር፡፡ የሕዝቡ ትኩረት መበታተኑንም ኢየሱስ ሳይመለከት አልቀረም፡፡ ወዲያውኑ እየሰበከ እያለም ሣርና አፈር ይንጠባጠብበት ጀመር፡፡ ዳሱ ወይም ከለላው ሲነሣ በተነደለው በኩል የፀሐይ ብርሃን ገባ፤ ወዲያውኑ አንድ በጣም የመነመነ ሰውነት ያለው ምስል በቃሬዛ ሆኖ ወደታች ሲወርድ ታየ፡፡ ከዚያ በቃሬዛ ከነበረው ከሲታ ሰው ፊት ላይ አነስተኛ ፈገግታ ብታዩ አትገረሙም? ያለ ጥርጥር የስብከቱ መቋረጥ ምክንያት በመሆኑ ድንጋጤ ሳይሰማው አልቀረም፡፡

ኢየሱስ የአራቱን ሰዎች እምነት በማክበር የሽባው ኀጢአት እንደ ተሰረየ ተናገረ (ከሉቃ 7÷48፤ 23÷43 ጋር ያነ)፡፡ ወደ ኢየሱስ የመጡት ፈውስ ፍለጋ ነበር (ምናልባትም ሰውየውን ተሸክመው ወዲያ ወዲህ ማለታቸው እንዲያከትም)፡፡ ሆኖም የሰሙት ኀጢአቱ መሰረዩን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን አራቱን ሰዎች ቅር ሳያሰኝ አልቀረም፡፡ ለፈሪሳውያን ግን በጣም የሚያስቆጣ ነበር፡፡ ኢየሱስ፣ እንደ እግዚአብሐር የተናገረ ነበር!

ፈሪሳውያኑ የክብር ወንበራቸው ላይ ሆነው በጸጥታ የኢየሱስን ስብከት እየሰሙ ነበር፡፡ ይህን ሲሰሙ ግን በጭራሽ መታገሥ

---

[25] ሉቃስ ስለ ጣራው ሲናገር የተጠቀመው፣ «ኬራሞን» *(keramon)* የሚል ቃል ሲሆን የሚያመለክተው፣ «ጡብን» ነው፡፡ ስለሆነም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን (ከማክጋርቪይ ገጽ 184 ጋር ያነ) ኢየሱስ የነበረው ቤቱ ውስጥ እንደ ነበርና እነዚህ አራት ሰዎች የነደሉት ጠንካራውን የቤት ጣራ ሳይሆን እንደማይቀር እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ እንዲህ ያለው ጉዳይ ደግሞ ከልኩ ያለፈ ነው፡፡ ምንም እንኳ ይህ የሚቻል ቢሆንም የምናቀርበው መላምት የቀረበ ትርጉም ያለው ይመስላል፡፡ ሉቃስ እያቀረበ ያለው ቴዎፍሎስ መገንዘብ የሚችለውን የግሪኮችና የሮማውያንን ባሕል መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ሉቃስ ታሪኩን በዝርዝር የሚያቀርበው ለአንባቢዎቹ ሲል እንጂ ከታሪካዊ ትክክለኛነቱ አኳያ አይደለም ማለት ነው፡፡ J. Vonnorsdall, "Mark 2:1-12," *Int* 36 (Jan 1982): 58-63 ላይ እንደሚለው፤

አልቻሉም፡፡ ከያሉበት ተሰባስበው ጥቂት ተመካከሩና ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየተሳደበ እንደ ሆነ በአንድነት ውሳኔ ላይ ደረሱ፤ «ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን ያለው ማነው?» በማለት ጠየቁ፡፡ አባባላቸው ትክክል ነው፤ ኀጢአትን የማስተሰረይ የባሕርይ ብቃት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው (ከኢሳ 43÷25 ጋር ያነ)፡፡ ትምህርተ መለኮታዊ ግንዛቤያቸው ትክክል ቢሆንም ስለ ኢየሱስ በነበራቸው አመለካከት ግን ተሳስተዋል፡፡

በመሠረቱ፣ መሳደብ ማለት «ክፉ መናገር» ወይም «መዳፈር» ማለት ነው (ቲቶ 3÷2፤ 2ጴጥ 2÷2፤ ይሁዳ 8 ጋር ያነ)፡፡ አንድ ሰው እግዚአብሔርን ተሳደበ የሚባለው፣ (1) ስለ እርሱ ክፉ ሲናገር፣ (2) ተገቢውን ምስጋና ለመስጠት እምቢተኛ ሲሆን፣ ወይም (3) ራሱን ወደ እግዚአብሔር ከፍታ ሲያወጣና፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን እርሱ ወዳለበት ደረጃ ዝቅ ማድረግ ሲሞክር ነው፡፡ ፈሪሳውያን ኢየሱስ በተናገረው የተናደዱት በዚህ በሦስተኛው የስድብ ዐይነት ነበር፡፡ በአይሁድ ሕግ መሠረት መለኮትን መሳደብ በሞት የሚያስቀጣ ከመሆኑ አንጻር ፈሪሳውያኑ ኢየሱስ ላይ ያን ያህል መቆጣታቸው ምክንያት ነበረው፡፡

[8]ኢየሱስም ወዲያው በልባቸው የሚያስቡትን ማር 2÷8-11
በመንፈሱ ተረድቶ፣ «እንዴት እንዲህ (ክፉ ነገር[ማ+]) ማቴ 9÷4 ጋር
ታስባላችሁ? [9]ሽባውን፣ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል ከማለትና
ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸከመህ ሂድ ከማለት የቱ ይቀላል? [10]ነገር ግን የሰው ልጅ
በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ በማለት ሽባውን፣
[11]«ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ» አለው፡፡

[25]እርሱም ወዲያው ተነሥቶ በፊታቸው ቆመ፤ ሉቃ 5÷25-26
ተኝቶበት የነበረውንም ተሸክሞ፣ እግዚአብሔርን ማቴ 9÷8 ጋር
እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ [26]በዚህ ጊዜ ሁሉንም መገረም
ያዛቸው፤ (እንደዚህ ያለ ሥልጣን ለሰው የሰጠውን[ማ+]) እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ፣
«ዛሬኮ ድንቅ ነገር አየን» እያሉ በፍርሀት ተዋጡ፡፡



እንደ ገና ኢየሱስ የሚያስቡትን፣ «በመንፈሱ» ተረድቶ ሐሳባቸው «ክፉ» እንደ ነበር ዐወቀ፡፡ ኢየሱስ ምላሽ የሚሰጠው ከተከራካሪነት አንጻር ሳይሆን፣ ሊካድ ከማይቻል መረጃ አንጻር ነው፡፡ «ሽባውን፣ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል ከማለትና ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸከመህ ሂድ ከማለት የቱ ይቀላል? » በማለት ጠየቀ፡፡ በመሠረቱ ግን፣ ሐቁ ሁለቱንም ለማለት በጣም ቀላል ሲሆን፣ ማድረግ ግን በፍጹም የማይቻል መሆኑ ነበር፡፡ ከዚህም በተረፈ ማንም ተነሥቶ ኀጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል ማለት ቢችልም፣ እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ አይኖርም፡፡ «ዐልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ» ቢል ግን በተግባር መታየት አለመታየቱን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አሁን ወደ ዐውዱ መካከለኛ ሐሳብ መጥተናል፣ «የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ ሥልጣን እንዳለው ታውቁ ዘንድ»[26] ኢየሱን ንግግሩን መሐል ላይ በማቋረጥ (ማር 2÷10) ወደ ሽባው ዞሮር አለና፣ «ዐልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ» አለ፡፡ ሁኔታውን ሳናስብ ኢየሱስ፣ «የማደርገውን ተመልከቱ!» በማለት የተናገረ ይመስላል፡፡

[26] አንዳንድ ምሑራን ይህን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ ምክንያቱም የኢየሱስን ዐላማና ማንነት በግልጽ የሚናገር በመሆኑ ነው፤ ምናልባትም በዚህ የፈውስ ታሪክ ላይ በኋላ የተጨመረ ሳይሆን እንደማይቀር ይናገራሉ (L.S. Hay, "The Son of Man in Mark 2:10 and 2:28" *JBL* 89 (1970): 69-75ን ይመ)፡፡ R.T Mead, “The Healing of the Paralytic – A Unit?” *JBL* 80 (1960): 348-354) ላይ፣ ምንም እንኳ ዐወደ ሐሳቡ ችግር አለበት ቢባልም የሰው ልጅ ማን መሆኑ ግልጽ ካልተደረገ የሽባው መፈወስ ይህን ያህል ላቅ ያለ ትርጉም አይኖረውም ነበር የሚል በጣም አሳማኝ መከራከሪያ አቅርቧል (ማር 2÷5-10)፡፡

ሽባውን መፈወስ መቻሉን በማሳየት፣ የሰውየውንም ኀጢአት ይቅር ማለት እንደሚችል አሳየ:: ማንኛውም አካላዊ ችግር የመንፈሳዊ ችግር ውጤት እንደ ሆነ አይሁድ ማመናቸው እርግጥ ነበር (ዮሐ 9÷2):: ስለሆነም ኢየሱስ ሰውየውን የፈወሰው ከሽባነት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ኀጢአተኛ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይደርስበት ከነበረው መገለል ጭምር ነበር ማለት ነው::

ሰውየው ወዲያውኑ ለኢየሱስ በመታዘዝ አልጋውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሄደ:: ሲመጣ አሳስገባ ያለው ሕዝብ አሁን ግን ገለል በማለት መንገድ ለቀቀለት:: እናንተ ብትሆኑ ኖሮ እንደዚያ ታደርጉ ነበር? ሽባው እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወጣ:: በሆነው ነገር ሕዝቡ እጅግ ተደነቀ:: ፈሪሳውያን ግን ጸጥ አሉ:: ኢየሱስ ካደረገው የተነሣ በጣም በተደነቀው ሕዝብ ፊት ሌላ ምን ማለት ይችላሉ? «ዛሬኮ ድንቅ ነገር አየን፣ ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ነገር አይተን አናውቅም» አሉ:: ሕዝቡ እንደዚያ የተደነቀው በዋናነት ደረጃ በተደረገው ፈውስ አልነበረም:: ከዚህ በፊት በዚሁ ቤት እንዲህ ያለ ነገር አይተው ነበር:: ኀጢአትን ይቅር የማለት መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ሰው ግን አይተው አያውቁም ነበር:: ስለሆነም ኢየሱስ ያደረገው ተአምር ሦስት ገጽታዎች ነበሩት ማለት ነው፤ (1) ኃጢአትን ይቅር ማለት፣ (2) የሰዎችን ሐሳብ ማወቅ፣ (3) ሽባውን መፈወስ:: ሦስቱም እጅግ አስገራሚ ናቸው::

**§ 47**
**የሌዊ/ማቴዎስ መጠራት**
**(ማቴ 9÷9፤ ማር 2÷13-14፤ ሉቃ 5÷27-28)**

ቀደም ሲል እንዳየነው ሁሉ እዚህም ላይ ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅር ማለቱን የምንመለከተው:: ይህን ታሪክ ስናነብ የግድ አንደኛው ከሌላው የቀጠለ እንደሆነ በማሰብ መሆን የለበትም:: እዚህ ላይ በአንድነት የተቀመጡት ከይዘታቸው ተመሳሳይነት የተነሣ ብቻ ነው::



ኀጢአት ማስተሰረይን በተመለከተ የኢየሱስ አመለካከት ምን ያህል ሥር ነቀል እንደ ነበር ስናስብ ብዙም ላይደንቀን ይችላል:: የአይሁድ ሃይማኖት ግን የኀጢአት ስርየት የሚገባቸው እነማን እንደ ሆኑ የራሱን ገደብ ያኖራል፤ ይህ፣ ሉቃስን ሳይጨምር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ውጫዊ ሥርዐቶችን ከመፈጸም አንጻር ይታይ ነበር:: ኢየሱስ ግን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት ርኅራኄንም የሚጨምር መሆኑን በማሳየት የእነርሱን አመለካከት ከላይ ወደ ታች ገለበጠው:: ይህ ደግሞ የአይሁድ ሃይማኖትን ገደብ በማለፍ፣ ሥርዐት ከማሟላት አኳያ ንጹሕ ወደሆኑት መድረስን ይመለከታል:: ኢየሱስ ለምጻምና ቀረጥ ሰብሳቢን ለመሳሰሉ እንኳ ርኅራኄ ያሳየው በዚህ ምክንያት ነበር::

**ማር 2÷13-14**
**ማቴ 9÷9፤ ሉቃ 5÷28 ጋር**

13ኢየሱስም ዳግም ወደ ባሕሩ ዳርቻ ወጣ፤ ሕዝቡም በብዛት ወደ እርሱ መጡ፤ እርሱም አስተማራቸው:: 14በዚያም ሲያልፍ የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን (ማቴዎስን[ማቴ]) በቀረጥ መቀበያው ስፍራ ተቀምጦ አየውና፣ «ተከተለኝ» አለው፤ እርሱም ተነሥቶ (ሁሉን ትቶ[ሉቃ]) ተከተለው::

ዳግም ኢየሱስ በጣም የሚወደውን ተግባር ሲፈጽም፣ ያም ሕዝብን ሲያስተምር እንመለከታለን:: የገሊላ ባሕር በሰዎች ተጨናንቆአል:: ኢየሱስ በሚኖርበት ቦታ ሁሉ ሌሎችም መሰብሰባቸው ግልጽ ነው:: ሌላው ቀርቶ ባሕሩ እንኳ ለጌታው እንደ መድረክ ለማገልገል የተዘጋጀ ይመስላል::

የዕለቱ ትምህርት ማብቂያ ላይ ኢየሱስ ቀረጥ ሰብሳቢ በሚቀመጥበት ቦታ እያለፈ ነበር:: ምናልባትም በባሕሩ ከሚመላለሱ ዕቃዎች ቀረጥ ለመሰብሰብ ባሕሩ ዳርቻ ያለ ወይም ወደ ቅፍርናሆም በሚወስደው መንገድ ላይ የነበረ ቀረጥ መቀበያ ቦታ ሊሆን ይችላል:: ሁለቱም ቦታዎች ለዚህ የሮም መንግሥት ሠራተኛ ጥሩ ገቢ ማስገኘት የሚችሉ ናቸው::

ሉቃስና ማርቆስ ሌዊ በማለት በአይሁዳዊ ስሙ ጠርተውታል:: እርሱ ግን ራሱን ማቴዎስ ብሎ ሲጠራ ትርጉሙም፣ (በአረማይክ) «የእግዚአብሔር ስጦታ» ማለት ነው::

ከሌሎች ሐዋርያት አንጻር፣ ይህ ሰው በፍጹም ለዚህ ዓላማ መታጨት አልነበረበትም:: ቀረጥ ሰብሳቢ እንደ መሆኑ መጠን በአይሁድ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ሊያስነሣበት ይችላል:: እንዲያውም ቀረጥ ሰብሳቢ (*mokhes*) ለማለት አይሁድ የሚጠቀሙበት ቃል ትርጉም በሥርወ ትርጉም ደረጃ፣ «ከጨቋኝ» እና «ወንጀለኝነት» ጋር የተያያዘ ይመስላል:: አይሁድ ይህን ጨቋኝ የሮም ሥርዐት አጥብቀው ይጠሉ ነበር:: በየጊዜው እየናረ የሚሄደውን የቀረጥ ክፍያም ይጠሉ ነበር:: የተለያዩ ዐይነት ቀረጦችን፣ ያም ለምሰሶዎች፣ ለድልድዮች፣ ለመንገዶች፣ ለወደቦች፣ ለገቢዎች፣ ለሰፈሮች፣ ለሰብሎች፣ ለወይን፣ ለዓሣ፣ ለፍራፍሬና ሌሎችም የሚከፍሉት በጣም ያንገበግባቸው ነበር:: ገንዘባቸው ለርኩስ ነገርና ለጣዖት አምልኮ እየዋለ መሆኑን ሲመለከቱ በጣም ይናደዱ ነበር:: ከሁሉም ይልቅ በጣም የሚያንገፈግፋቸው ግን ቀረጡ የሚከፍልበት ምክንያት ያም የእግዚአብሔር ሕዝብ በሮማውያን ጭቆና ቀንበር ሥር መሆናቸው ነበር::

ማንኛውም ለሮም መንግሥት፣ «አገር ውስጥ ገቢ» የሚሠራ አይሁዳዊ እጅግ ጸያፍ በሆነ መልኩ እንደ ከሐዲ ይቆጠር ነበር:: ስለሆነም ማቴዎስ ከማንኛውም የአይሁድ አኗኗር ሁኔታ፣ በተለይም ምኩራብ ውስጥ ከሚሰጠው አገልግሎት የመገለል ችግር ሊገጥመው ይችላል ማለት ነው:: «ገንዘቡ እንደ ጸያፍ ይቆጠር ነበር፣ ገንዘቡን የሚቀበል ራሱ እንደ ርኩስ ይታሰብ ነበር:: ፍርድ ቤት ቀርቦ መመስከር አይችልም:: የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ለቀረጥ ሰብሳቢው የሚጠቅም አንድ ቃል እንኳ አልነበራቸውም፤ ምክንያቱም



በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ለመገኘት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ሕጉን መጠበቅ እንዳለባቸው ይታሰብ ነበር» (Shepard ገጽ 143)::

የመጀመሪያው ወንጌል ጸሐፊ እንደ መሆኑ መጠን ከማንኛውም ጸሐፊ ይልቅ ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶችና የአይሁድ ባሕሎች ከማቴዎስ መማር እንችላለን:: መጽሐፉን ስናነብ በእርግጥም የአይሁዶች አይሁድ እንደ ሆነ እንረዳለን:: ታዲያ፣ ከዚህ የምንገነዘበው ምንድነው? ምናልባትም ማቴዎስ የአይሁድ ሥረ መሠረቱን አጥብቆ ይፈልገው ይሆናል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሥራው የሚያስገኘውን ገቢ ማጣት አይፈልግም:: ምናልባትም በግል ሕይወቱ በመሲሑ ስላለው ተስፋ መረዳት የቻለው ከሰዎች ተገልሎ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናቱ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል:: (ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን የተማረው ከኢየሱስ ብቻ ነበር ብሎ ማመን ይከብዳል::) ምንም እንኳ በሌሎች በመገለላቸው ምክንያት እንደ ጠላት ቢቆጠሩም አንዳንዶች ታላላቅ አገልጋዮች ሊወጣቸው እንደሚችል ከማቴዎስ ሕይወት መማር ይኖርብናል::

ኢየሱስ እያለፈ እያለ ወደ ሌዊ ተመለከተ ብዙ ሰዎች ሰላምታ እንኳ ሲነፍጉት፣ አንዳንዶች ደግሞ አይተው እንዳላየ ያልፉት ነበር:: ኢየሱስ ግን ከሁሉም የተለየ ነው:: ፊት ለፊት ከሌዊ ጋር ተገናኘ፤ ደቀ መዝሙሩ እንዲሆንም ወዲያውኑ ጠራው::

ማቴዎስም በአፋጣኝና ሁሉንም እርግፍ አድርጎ በመተው ምላሽ ሰጠ:: ምናልባትም ሌዊ ከዚያ በፊት ኢየሱስን ሳያውቀው አልቀረም:: የገሊላ ባሕር፣ በተለይም ደግሞ በቅፍርናሆም በኩል ያለው የባሕሩ ዳርቻ የኢየሱስ አገልግሎት፣ «ዋና ጣቢያ» ነበር ማለት ይቻላል:: ኢየሱስ ሲሰብክ መስማቱም ጥርጥር የለበትም:: ኢየሱስ አራቱን ዓሣ አጥማጆች በጠራ ጊዜም በቦታው በመገኘት ሳይመለከት አልቀረም:: ብዛት ያለው ገንዘብ፣ በተለይ ደግሞ በተአምር ብዙ ዓሣዎችን የያዙ ጊዜ ብዙ ገንዘብ በቀረጥ መልክ ከእነርሱ ሳይቀበል አልቀረም:: ከዚህም

በተረፈ የታሪኩ በጣም አጭር መሆን ወዲያውኑ ከቀረጥ መሰብሰቢያው ጠረጴዛ እንደ ተነሣና ሲሰበስብ የዋለውን ገንዘብ ሌሎች እንዲቀራመቱ የተወላቸው ያስመስለዋል:: እንዲህ ይሆናል ብሎ ማሰብ ግን አይታሰብም:: ይልቁንም የቀረጥ ዐቀበያ ቦታውን ከዘጋ በኋላ ሒሳቡን ከሮም ባለሥልጣናት ጋር አወራረደ ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል:: ከዚያ በተለየ ማድረግ ግን ኀላፊነትን አለመወጣት ከመሆኑም በላይ አደገኛም ነበር፤ የኢየሱስን አገልግሎትም የሚያስነቅፍ ይሆን ነበር::

የግል ሥራቸውን ለአባታቸው በመተው ኢየሱስን ስለ ተከተሉ አራት ዓሣ አጥማጆች ተመልክተናል:: ይሁን እንጂ ምንጊዜም ቢሆን ወደቀድሞ ሥራቸው የመመለስ ምርጫቸው እንደ ተጠበቀ ነው:: እንዲያውም፣ ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስን በመጠበቅ ላይ እያሉ አንዳንድ ደቀ መዛሙርት ወደ ገሊላ ተመልሰው የዓሣ ማጥመድ ሥራቸውን ጀምረው ነበር:: የሌዊ ጉዳይ ግን የተለየ ነው፤ ምንም አማራጭ አልነበረውም:: ከቀረጥ መቀበያው ቦታ የተነሣው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነበር:: በአንድ ግዙፍ ድርጅት ውስጥ እዚህ ግባ የማይባል ሠራተኛ ነበር:: የቀረጥ መሰብሰብ ሥራው ጠቀም ያለ ገንዘብ ያስገኝለት ነበር፤ አሁን ግን ለምንጊዜውም ተቶታል::

**§ 47ለ**
**በማቴዎስ ቤት**
**የተደረገ ግብዣ**
**(ማቴ 9÷10-13፤**
**ማር 2÷15-17፤**
**ሉቃ 5÷29-32)**

ኢየሱስ ያገለግል በነበረበት ዘመን አብሮ መብላት አንድ ዐይነት አስደሳች ነገር ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ቀረቤታንና ዝምድናን የማጠናከሪያ መንገድ ነበር:: ስለሆነም ምግብ አንድ ሰው በቤተሰቡም ሆነ ማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ደረጃ የሚያስጠብቅበትና የሚያጠናክርበት ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ አንድምታነት ነበረው:: ኢየሱስ ግን ምግብን የተጠቀመበት በዘመኑ የነበረው ጨቋኝና ሌሎችን የሚያገልል ማኅበረሰብን አቋም ለመቃወም እንደ ነበር እናስተውል፤ (1) መብል አንድ ሰው ማኅበራዊ



ኀላፊነቱንና ከእርሱ ዝቅ ላሉት ያለውን ንቀት የሚያሳይበት መሆኑን ተናገረ (ሉቃ 14÷1-14 ጋር ያነ)፤ (2) አብሮ በመብላት አማካይነት፣ «ኀጢአተኞች»ንና ሰዎች ያገለሏቸውን የሚያቅፍ አዲስ ማኅበረሰብ መሠረተ (ማቴ 9÷10-17 ጋር ያነ)፤ (3) የመብል ጊዜ በሰዎች መካከል ልዩነትን የሚፈጥር ሥርዓትን እንደማይቀበል ኢየሱስ አመልክቷል (ማር 7÷1-25 ጋር ያነ)::[27]

**ሉቃ 5÷29-30**
**ማቴ 9÷10-11፤**
**ማር 2÷15 ጋር**

[29]ሌዊም ለኢየሱስ በቤቱ ትልቅ ግብዣ አደረገ፤ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ሌሎች ሰዎችም («ኀጢአተኞችም»[ማር]) ከእነርሱ ጋር በማእድ ተቀምጠው ነበር (የተከተሉት ብዙ ስለ ነበሩ[ማር]):: [30]ፈሪሳውያንና ጸሐፍታቸውም «ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢአተኞች ጋር የምትበሉትና የምትጠጡት ለምንድን ነው?» እያሉ በደቀ መዛሙርቱ ላይ አጕረመረሙ::

**ማር 2÷17**

[17]ኢየሱስም የሚናገሩትን ሰምቶ፣ «ሐኪም የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች አይደሉም፤ እኔ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ወደ ንስሐ ልጠራ አልመጣሁም» አላቸው::

**ማቴ 9÷13**

[13]ሄዳችሁ፣ ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ፤ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም የሚለውን ቃል ትርጉም አጥኑ::»

ማቴዎስ ኢየሱስን ቤቱ በመውሰድ በጣም የከበረ የሚመስል ነገር አደረገለት፤ ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ግብዣ አደረገ (ማር 2÷15):: እነማንን ጨምሮ ጋብዞ ይሆን? ማንኛችንም እንደምናደርገው የቅርብ ወዳጆቹን ነበር የጋበዘው:: ችግሩ የማቴዎስ ወዳጆች ኀጢአተኞችና እንደ እርሱ ቀረጥ ሰብሳቢዎች መሆናቸው ነበር

---

[27] Dietmar Neufeld, “Jesus’s Eating Transgressions and Social Impropriety in the Gospel of Mark: A Social Scientific Approach,” *BTB* 30/1(2000): 15-26.

(ማቴ 11÷19፤ 18÷17፤ 21÷31-32፤ ሉቃ 15 1 ጋር ያነ)::[28] ይህ ዐይነተኛ ወንጌልን የማዳረስ ዘዴ ነው:: ኀጢአተኞች ከኢየሱስ ጋር ሲገናኙ እነርሱ ያገኙትን ደስታ ወዳጆቻቸው በሙሉ እንዲያገኙ ይፈልጋሉ::

ማቴዎስ የሰጠው ምላሽ ከኀጢአተኞች የሚጠበቅ የመሆኑን ያህል ፈሪሳውያንና ጸሐፍቶቻቸው የሰጡት ምላሽ ደግሞ እንዲሁ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ የሚሰጠው ዐይነት ምላሽ ነበር:: «ብጤ ከብጤው ይውላል» የተሰኘውን ምሳሌ አላግባቡ በመረዳታቸው ኢየሱስን ተቃውመዋል:: ያንን ግን በተዘዋዋሪ ነበር የሚያደርጉት:: ደቀመዛመርቱ ላይ አጉረመረሙ እንጂ፣ ፊት ለፊት ኢየሱስን አልተቃወሙም (ሉቃ 5÷30):: በፈሪሳውያኑ ተቃውሞና ማጉረምረም ደቀ ማዛሙርቱ ተደናግጠዋል:: በዘመናቸው ሁሉ ለእነዚህ ሰዎች አክብሮት ነበራቸው:: አሁን ግን ራሳቸውን ሌላ ምድብ ውስጥ አግኝተውታል::

በተጨማሪም፣ ከማቴዎስ ጋር አብረው በመብላታቸው ፍርሃትና መሸማቀቅ ሳያሳድርባቸው አልቀረም:: እነዚህ ሰዎች ሥነ ሥርዐት ጠብቀው የሚኖሩ ነበሩ:: ማቴዎስ ላይ ይደርስ የነበረውን መገለል በቅርብ ሲከታተሉ ነበር:: ምናልባትም ሌዊን አስመልክቶ በየጊዜው ይሰነዘር በነበረው ሐሜት እነርሱ ራሳቸውም ተሳታፊ ሳይሆኑ አልቀሩም:: ኢየሱስን ተከትለው ወደ ሌዊ ቤት የመሄዱን ሐሳብ ደጋግመው ሳያወጡ ሳያወርዱ አልቀሩም:: ምናልባትም ከኢየሱስ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለማቋረጥ ፈተና ሆኖባቸውም ይሆናል::

ኢየሱስ ግን ይመካከሩ የነበረውን ሰምቶ በአንድ ውብ ምሳሌ አማካይነት ይፋ አወጣው:: ታላቁ ሐኪም ኢየሱስ ሰዎች ስለ እርሱ ለሚያቀርቡት ሐሳብ ደንታ አልነበረውም:: እንደ ሐኪምነቱ የእርሱ ምኞት ብዙ ገንዘብ ማሰባሰብ አልነበረም:: ይልቁንም ለሕሙማን ይራራ

[28] ሉቃስ ዝቅተኛ ለነበሩትና ለጠፉ ሰዎች በጣም ከመራራቱ የተነሣ «ኀጢአተኞች» ከማለት ይልቅ፣ «ሌሎች» ማለትን መርጧል::



ነበር:: «የፈሪሳውያን አስተሳሰብ ሰዎችን መገምገም ላይ ያበቃል፤ ኢየሱስ ግን ሰዎችን ወደ መፈወስ ዘልቆ ይሄዳል፤ ኀጢአተኞች ሕሙማን በመሆናቸው ርዳታ ያስፈልጋቸዋል እንጂ እንዲበከሉ ተትተው መጣል የለባቸውም» (Nolland, ገጽ 250)::

ኀጢአተኞችን ስለ መውደድና ዓለምን በወንጌል ስለመድረስ ብዙ እንናገራለን፤ ይሁን እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣታቸው በፊት ከማንኛውም ችግራቸው እንዲላቀቁ እንጠብቀለን:: ያጨሱት ሲጋራ ከሸተተን በጣም እንናደዳለን:: «አሜን» ከማለት ይልቅ፣ «ትክክል» ማለታቸው ያስቆጣናል:: ምናልባት ጥሩ ያልሆነ ቃል ከአንደበታቸው ይወጣ እንደ ሆነ በማሰብ የሚናገሩትን በጥንቃቄ እናደምጣለን:: ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን የሚስተናገዱባት ሆቴል ሳትሆን፣ ኀጢአተኞች የሚታከሙባት ሆስፒታል መሆኗን መገንዘብ ይኖርብናል::

«ሄዳችሁ ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ የሚለውን ቃል አጢኑ» የሚለውን ከሆሴዕ በመጥቀስ የጻፈ ማቴዎስ ብቻ ነው:: «ሄዳችሁ አጢኑ ወይም ተማሩ» የሚለው የሃይማኖት መምህራን፣ «የቤት ሥራ» ባልሠሩ ተማሪዎቻቸው ላይ የሚጠቀሙት የተለመደ አነጋገር ነበር:: ኢየሱስ በጣም ምሁራን ነን የሚሉትን ገና እንደ ጀማሪ ተማሪ እያያቸው ነበር:: ይህ ደግሞ የስድብ ያህል በጣም ያማቸዋል:: ይሁን እንጂ ነገር የተዘበራረቀባቸው በመሆኑ እንዲህ መባል ይገባቸው ነበር:: ትልቁ የእነርሱ ትኩረት ሃይማኖታዊ ሥርዐታቸው ላይ እንጂ ሰዎች ላይ አልነበረም ስለሆነም ሆሴዕ 6÷6 ለእነርሱ መጠቀሱ ተገቢ ነበር:: በሴማውያን የአነጋገር ፈሊጥ መሠረት፣ «ይህ ማለት ያ» ነው፣ «ከዚህኛው ያኛው ይበልጣል» በሚል ሁኔታ ተረድተውታል:: ጉዳዩ እግዚአብሔር መሥዋዕታቸውን አለመፈለጉ ሳይሆን፣ ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን መፈለጉ ነበር:: ብዙ ጊዜ ግን ብሉምበርግ እንዳመለከተው ቤተ ክርስቲያን ይህን ትዘነጋለች::

እንደ ፈሪሳውያን ሁሉ ብዙዎቻችን በማኅበረሰቡ ያሉ ደካሞችን ችላ እንላለን፤ ከዚህ በከፋ መልኩም እናገልላቸዋለን፤ ይሁን እንጂ ወንጌላዊነታችን፣ ወንጌልን ለማዳረስ ያለን ጥረት ማኅበረሰባዊ አገልግሎት ሁሉ ቤት የለሾችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፣ የአደገኛ ዕፅዋት ሱሰኞችን፣ ዕፅ አዘዋዋሪዎችን፣ የኤድስ ለስባዎችንና የመሳሰሉ በቁጥር አነሥተኛ የሆኑትን፣ እንዲሁም፣ የጋብቻ መፍረስ የገጠማቸውን፣ ብቸኛ ወላጆችን፣ ጧሪ የሌላቸው አረጋውያንን፣ አልኮሊስቶችንና ሌሎች እነርሱን የመሳሉትን ሁሉ ማሰብ ይኖርበታል። እርግጥ ነው፣ ከኀጢአተኞች ጋር በኀጢአታቸው አንተባበርም፤ ይሁን እንጂ ከእነርሱ ጋር በመሆን የዘመናችን ፈሪሳውያን የሚጸየፉትን ዐመፅና የዚህ ዓለም ክፉ ነገር መጋፈጥ እንችላለን (ገጽ 157)።

**§ 48**
**መብል መጠጥ**
**እና ጾም፤**
**አሮጌና አዲሱ**
**(ማቴ፣ 9÷14-17፤**
**ማር 2÷18-22፤**
**ሉቃ 5÷33-39)**

ማቴዎስ ያዘጋጀው ግብዣ ኢየሱስ ላይ አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ተቃውሞ አስነሥቷል፤ (1) ከኀጢአተኞች ጋር ትተባበራለህ ተባለ፤ (2) ከመጾም ይልቅ መብላት ታዘወትራለህ ተባለ። ይህ ታሪክ የማቴዎስ ግብዣ «ክፍል 2» ሲሆን ሉቃስ ከሚያቀርባቸው ያለመግባባት ታሪኮች ማዕከል ነው (ሉቃ 5÷1-6:16)። መሠረተ ሐሳቡ የክርስቶስ ወንጌል፣ «አሮጌውን ወደ መጣፍ ደረጃ ዝቅ አለማለቱ ነው (ቁ 36) በአሮጌው ነገር የማይወሰን መሆኑ ነው (ቁ 37-38)» Nolland, ገጽ 250)

**ማር 2÷18-20**
**ሉቃ 5÷33**
**ማቴ 9÷14-15**
**ጋር**

[18]የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጾሙ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎችም (የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት[ማቴ]) መጥተው ኢየሱስን፣ «የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት (አብዛኛውን ጊዜ[ሉቃ]) ሲጾሙ የአንተ ደቀ መዛሙርት የማይጾሙት ለምንድነው አሉት። (ዘወትር ይበላሉ፣ ይጠጣሉ[ሉቃ]) [19]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሲጾሙ (ሲያዝኑ[ማቴ]) ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሲጾሙ አይችሉም፤ [20]ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ።

እንደ ሕጉ በዓመት ውስጥ የታዘዘው አንድ ጾም ብቻ ሲሆን፣ ይኸውም የቤዛ ቀን ነበር። ፈሪሳውያን ግን በጣም ሃይማኖተኞች መሆናቸውን ለማሳየት በየሳምንቱ ሰኞና ሐሙስን ይጾሙ ነበር። በጣም የሚገርመው ማቴዎስ ግብዣውን ያደረገው፣ «እውነተኞቹ ሃይማኖተኞች» በሚጾሙበት ቀን መሆኑ ነበር።

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ይልቅ ከፈሪሳውያን ጋር መወገናቸው ደግሞ ሌላው አስገራሚ ነገር ነበር። በመሠረቱ ግን ዮሐንስ ፈሪሳውያንን የእፉኝት ልጆች በማለት ሲገሥጻቸው ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ግን አጠንክሮ ያመለክት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ዮሐንስ እስር ቤት ስለነበር እነዚያ ልበ ሙሉ ደቀ መዛሙርት (በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት የኢየሱስ ተከታዮች ያልሆኑ) እርሱን ከእስር ለማስፈታት ኢየሱስ አንድ ነገር ባለማድረጉ ከፍቷቸው ሊሆን ይችላል። ከዚህም በላይ ኢየሱስና ዮሐንስ የተለያየ የአሠራር መንገድ ይከተሉ እንደ ነበር መገንዘቡም አስፈላጊ ነው (ማቴ 11÷18-19)። ዮሐንስ ጾም የሚያበዛ ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን እንደዚያ አልነበረም። ምናልባትም ይህ ለዮሐንስ ደቀ መ[illegible]ሙርት ግራ የሚያጋባና የሚያበሳጭ ሆኖባቸው ይሆናል።

ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ጥልቅና ምክንያታዊ ነበር። ሙሽራ ባለበት ቦታ ግብዣና ደስታ ይኖራል። ለዚህ ነበር ኢየሱስ፣ «ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይችላሉን?» በማለት የጠየቀው። ይህን ጥያቄ በተመለከተ ጥቂት ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል። በመጀመሪያ፣ በግሪክኛው አቀራረብ ጥያቄው «በፍጹም ሊጾሙ አይችሉም» የሚል አሉታዊ መልስ በሚጠብቅ ሁኔታ ነው የተቀመጠው። ሁለተኛው፣ ኢየሱስ ራሱን ዮሐንስ በሰጠው መጠሪያ፣

ያም ሙሽራው በማለት መጥራቱን እናያለን። ስለሆነም ኢየሱስ የራሳቸው መምህር ዮሐንስ ያስተማራቸውን እያሳሰባቸው ነበር ማለት ነው (ዮሐ 3÷29)።

ዋናው መልእክት ሰርግ ላይ ያለ ሰው ሊጾም ወይም ሊያዝን አለመቻሉ ነው። የኢየሱስ አገልግሎት ደስታና ሐሤት ያለበት ሊሆን ይገባ ነበር። በመሠረቱ ግን እንደ ዮሐንስ ሁሉ ኢየሱስም ንስሐን ሲሰብክ ነበር፤ ብዙ ጊዜ ደግሞ ንስሐ ከጾም ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር ሁኔታው ግር የሚል ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆይ ጌታ ስለሚወሰድባቸው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚያዝኑበት ጊዜ ይመጣል። «መወሰድ» [*aparthe*] የሚለው ቃል በኃይል ተመንጭቆ የሚወሰድ ነገርን ነው የሚያመለክተው። በተዘዋዋሪ ኢየሱስ ስለ መስቀል ሞቱ እየተናገረ ነበር። ተከታዮቹ ለሦስት ቀን ያህል አምርረው ያለቅሳሉ። ሌላው ቀርቶ በዕርገቱና በዳግም መምጣቱ መካከል ባለው ጊዜ ከእነርሱ ጋር ባለመኖሩ ተከታዮቹ እያዘኑ ናቸው። ይህ ጊዜ የሚጾሙበትና የሚያዝኑበት ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ መንፈሱ ከእኛ ጋር በመሆኑ እንጽናናለን። ይህ ራሱን የቻለ በረከት ቢሆንም ሙሉ በሙሉ በእጃችን የገባ ግን አይደለም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት መጥታለች ሆኖም እውን አልሆነችም።

ሉቃ 5÷36-39
ከማቴ 9÷16፤
ማር 2÷21 ጋር

36ደግሞም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤ «ከአዲስ ልብስ ላይ እራፊ ቀዶ በአሮጌ ልብስ ላይ የሚጥፍ ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ አዲሱን ልብስ ይቀደዋል (አዲሱ እራፊ ካረጀው ልብስ ላይ ተቦጭቆ ቀዳዳውን የባሰ የሰፋ ያደርገዋል[ማቴ፣ማር]) አዲሱም እራፊ ለአሮጌው አይስማማውም። 37አዲስ የወይን ጠጅም በአሮጌ አቁማዳ ጨምሮ የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል፤ የወይን ጠጁም ይፈሳል፤ አቁማዳውም ከጥቅም ውጪ ይሆናል። 38ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ መጨመር አለበት። 39እንግዲህ አሮጌ የወይን ጠጅ ከጠጣ በኋላ፣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ ምክንያቱም አሮጌው የተሻለ ነው ስለሚል ነው።»



የመጀመሪያው የኢየሱስ ምሳሌ ስለ ልብስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ስለ ወይን ጠጅ ነው። ከሁለቱም የሚነመለከተው ዐቢይ ትምህርት ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እስካለ ድረስ ደቀ መዛሙርቱ መጾማቸው ተገቢ አለመሆኑን ነው። ደስ የሚሰኙበት እንጂ የሚጾሙበት ጊዜ አይደለም። በተጨማሪም ተገቢ ያልሆነ ሥራ ከፍተኛ ጥፋት ሊያስከትል እንደሚችል ከሁለቱም ምሳሌዎች መመልከት ይቻላል።

ሁለተኛው ትምህርት ስለ አሮጌና አዲሱ ነው። አዲሱ ከአሮጌው ጋር አይስማማም። የኢየሱስን አገዛዝ ወስደን በአንድ ዓይነት ሃይማኖታዊ አስተምህሮ በተለይም ከፈሪሳውያን ትምህርት ጋር ለማስማማት ብንሞክር በፍጹም የማይቻል ይሆንብናል። ሁለቱም ተያይዘው ይጠፋሉ። ኢየሱስ ለውጥና ፍጹም አዲስ የሆነ ሥርዐት እንዲኖር እየተጣራ ነው። ምሳሌውን ያቀረበው ከብሉይ ኪዳን ሲሆን (ለምሳሌ መዝ 102:26-28) በመላው አዲስ ኪዳንም ጥቅም ላይ ውሏል (ሮሜ 13÷12-14፤ ገላ 3÷27-28፤ ኤፌ 4÷ 22-24፤ ቆላ 3÷9-10፤ ራእ 21÷1፣5)።[29]

ሰዎች ከአዲሱ ይልቅ አሮጌውን የመምረጥ ዝንባሌ እንዳላቸው (5÷39) የሚናገረው ሉቃስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ስለ ትምህርቱ አቀረበ እንጂ በሁኔታው መስማማቱን እየገለጸ አይደለም። አሮጌው ወይን የተሻለ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። ሆኖም ተለዋጭ ዘይቤው የሚያበቃው እዚህ ላይ ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱ (ወንጌል) ከአሮጌው (ሕግ) የበለጠ ነው። እዚህም ላይ ቢሆን ተመሳሳይ ነገርን እያየን ነው፤ ሰዎች ይበልጥ የሚወዱት አሮጌውን

[29] J.D.M. Derrett, "Modes of Renewal (Mk 2:21-22)" *EvQ* 72/1 (2000): 3-12 ይመ።

ነው:: አሮጌ መንገድን ስለ ለመዱ በዚያው መቀጠል ይፈልጋሉ:: ምንጊዜም ቢሆን ሃይማኖት የሚያደርገው ይህን ይመስላል::

እየተነጋገርን ያለነው ቅደም ተከተላዊ ጉዳይ አይደለም፤ ዛሬም ቢሆን ለአንዳንዶች ወንጌል አርጅቶባቸዋል:: ከጸጋ ይልቅ ከሕግ ጋር መሆን ይበልጥ ተስማምቷቸዋል:: ምንም እንኳ ሕግ ፈራጅ ቢሆንም ምን እንደሚጠበቅብን አስረግጦ ይነግረናል:: ኢየሱስ ግን ፍጻሜያችን የት ላይ እንደ ሆነ ምንም ማረጋገጫ ሳይሰጠን እንዲሁ እንድንከተለው ብቻ ነው የጠራን:: ማቴዎስና ኀጢአተኞች ወዳጆቹን የመሳሰሉ ሰዎች ወዳሉበት ሁኔታ መቼ ሊጠራን እንደሚችል ማን እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይችላል:: ሕጉ የሚያቀርበው መመሪያ የጨለመ ቢሆን እንኳ መንገዱ የታወቀ ነው፤ ወንጌል ግን ምንም እንኳ ነጻ የሚያወጣ ቢሆንም ስፍር ቁጥር የሌለው ነገርን እንድንጠብቅ ስለሚያደርግ መንገዱ አስፈሪ ሊሆን ይችላል::

**§ 49**
**በቤተ ሳይዳ አንድ ሽባ በሰንበት ቀን መፈወሱ**
**(ዮሐ 5÷1-9)**

ይህ ኢየሱስ የፈወሰው ሁለተኛው ሰው መሆኑ ነው (§ 53፤ ማቴ 9÷1-8፤ ማር 2÷1-12፤ ሉቃ 5÷17-26 ጋር ያነ):: ኤደርሼይም ስለ ሁለቱ ተመሳሳይነት አራት ነጥቦችን ያቀርባል፤ (1) ሁለቱንም ጊዜ ኢየሱስ የተጠቀመው፣ «ተነሥ! መተኛህን ተሸክመህ ሂድ» በሚል ተመሳሳይ ቃል ነበር (ማር 2÷9፤ ዮሐ 5÷8)፤ (2) በአንደበታቸው ባይናገሩትም ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅር በማለቱ እንደ ከሃዲ ተቆጥሯል (ዮሐ 5÷18):: ከዚህም የተነሣ የሃይማኖት ባለሥልጣናት ሊገድሉት ፈልገዋል፤ (3) ሁለቱንም ጊዜ ዋና ጉዳይ ሆኖ የቀረበው የኢየሱስ ሥልጣን ነበር (ዮሐ 5÷27)፤ (4) ሁለቱንም ጊዜ ኢየሱስ ለነበረው ሥልጣን ሥራውን እንደ ማስረጃ እንዲመለከቱ ጠይቋል (ማር 2÷10፤ ዮሐ 5÷36)::



**ዮሐ 5÷1-5**

[1]ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበር፤ ኢየሱስም
ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ:: [2]በኢየሩሳሌም በበጐች በር
አጠገብ፣ አምስት ባለ መጠለያ መመላለሻዎች የነበሯት፣
በአራማይክ ቋንቋ ቤተሰይዳǁ የተባለች አንዲት መጠመቂያ
አለች:: [3]በእነዚህም መመላለሻዎች ውስጥ ብዙ አካለ ስንኩላን፣ ዐይነ ስውሮች፣
አንካሶችና ሽባዎች ይተኙ ነበር:: [5]በዚያም ለሠላሳ ስምንት ዓመት ሕመምተኛ ሆኖ
የኖረ አንድ ሰው ነበር::

*ǁ2 አንዳንድ ቅጂዎች ቤተዛታ ሌሎች ቅጂዎች ቤተሰይዳ ይላሉ፤ [4]ዐልፎ ዐልፎ የጌታ መልአክ ወርዶ ውሃውን በሚያናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ ወደ መጠመቂያይቱ የገባ ካደረበት ማንኛውም በሽታ ይፈወስ ነበር::*

የኢየሱስ የገሊላ አገልግሎት ከበዓሎች በአንዱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ተቋርጦ ነበር:: የትኛው በዓል እንደ ነበር ማወቅ ባንችልም ሔንድሪክሰን የፋሲካ በዓል ሊሆን እንደሚችል ጠንካራ ምክንያት አቅርቧል (ገጽ 188-189):: ይህ ትክክል ከሆነ የኢየሱስ ሁለተኛው የአገልግሎት ዓመት ጅማሬ ነበር ማለት ነው::

ኢየሱስ ወደዚህ አምስት ባለ መጠለያ መመላለሻዎች ወደ ነበሩት መጠመቂያ ሄደ:: መጠመቂያው ቤተሰይዳ ማለትም፣ «የምሕረት ቤት» በመባል ይጠራ ነበር:: ቦታው በበጐች በር አጠገብ የነበረ ሲሆን ስያሜውን ያገኘውም ለመሥዋዕት የሚቀርቡ በጐች ወደ መቅደሱ የሚገቡበት ስለሆነ ሊሆን ይችላል::[30] በሐኪም ቤት ውስጥ እንዳለና ብዙ

[30] ይህ መጠመቂያ የት እንደ ነበር ከስድስት ያላነሡ ቦታዎች ቀርበዋል:: ዊያንድ እንደሚለው ይበልጥ ትክክል የሚሆነው የቅድስት ሐና ቤተክስቲያን አጠገብ ያሉ ሁለት ምንጮች ናቸው:: ከዚህም በላይ ቁ2 በጣም አስቸጋሪ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ «በር» የሚለው ቃል በኋላ የተጨመረ እንጂ ግሪክኛው ቅጁ ውስጥ ማግኘት አይቻልም:: ስለሆነም የምንነጋገረው፣ «የበጐች መጠመቂያ» ስለሚለው እንጂ «የበጐች በር» ስለሚለው መሆን የለበትም ማለት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ቤተ ሰይዳ፣ ቤዛታ፣ ቤተ ዛታ፣ ወዘተ የተሰኙትን ጨምሮ ቤተ ሴይዳ የሚለውን ቃል በተለያየ ሁኔታ

ሕመምተኞች እንደሚታከሙበት ክፍል ዐይነት ነበር:: ፈውስ በመፈለግ ሰዎች ወደዚያ ቦታ ይመጡ ነበር::

ቁጥር 3-4፣ «ዐልፎ ዐልፎ የጌታ መልአክ ወርዶ ውሃውን በሚያናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ ወደ መጣመቂያዪቱ የገባ ካደረበት ማንኛ ውም በሽታ ይፈወስ ነበር» ስለ ተባለበት ምክንያት ይገልጻል:: ይሁን እንጂ፣ ከአራተኛው መቶኛ ዓመት በፊት በነበሩ ቅጆች ውስጥ የማይገኝ በመሆኑ አደሱ መደበኛ ትርጉም ውስጥ አልተካተተም::[31] ታዲያ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይህን የጨመሩት ለምንድነው? የምናቀርበው ሐሳብ ከግምት ያለፈ ባይሆንም፣ ቀደም ሲል በሁለተኛው መቶኛ ዓመት የነበረ ጸሐፊ[32] ቁጥር 7ን ለማብራራት በማስተወሻ መልክ በቅንፍ ጽፎት ይሆናል:: በኋላም የዋናው አካል ክፍል ሆነ ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል:: ይህ ተጨማሪ ክፍል ኢየሱስ እያገለገለ በነበረ ዘመን የነበረ አስተሳሰብን የሚያንጸባርቅ ነው ማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ፣ ዮሐንስ (ወይም ይህን ማስታወሻ የጨመረው ሰው ጭምር) ዐረፍተ ነገሩ እውነት መሆኑን ተቀብሎአል በማለት ማሰብ የለብንም፤ ያንን እንደ እውነት

የሚያስቀምጡ ቅጆች አሉ:: D.J. Wieand, "John 5:2 and the Pool of Bethesda," *NTS* 12 (1966): 392-404 ላይ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ጥረት አድርጓል:: ይሁን እንጂ የምንባቡ ታሪካዊ ይዘትም ሆነ ነገረ መለኮታዊ መልእክት በተነሡት ጥያቄዎች ጉዳት ላይ አልወደቀም:: የአሁን ጊዜን በሚያመለክት ሁኔታ፣ «በኢየሩሳሌም ቤተ ሳይዳ የተባለች አንዲት መጠመቂያ አለች» የሚለውን መሠረት በማድረግ D.B. Wallace የዚህ መጠመቂያ መመላለሻዎች በመጥፋታቸው ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ከ70 ዓ.ም. በፊት መሆን አለበት በማለት ይከራከራል:: ("John 5:2 and the Date of the Fourth Gospel," *Biblica* 71[1990]: 177-205)::

31 ይሁን እንጂ መካተታቸውን አስመልክቶ Zane Hodges "The Angel at Bethesda," *BibSac* 136 (1979): 25-39, contra Bruce Metzger, *A Textual Commentary on the Greek New Testament* (London: UBS, 1971), ገጽ 209 ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል::

32 Tertullian (c.145-200 ዓ.ም.) ይህን ምንባብ ያውቅ ነበር:: ይህን በተመለከተም: «መልአኩ ወደ ምድር በመውረድ የቤተ ሳይዳን መጠመቂያ ያናውጥ ነበር፤ በተለያየ ሕመም ይሰቃዩ የነበሩ የሚወርድበትን ጊዜ ጠብቀው ወደ ውሃው ለመግባት የመጀመሪያ የሆነ ሰው ከሕመሙ ይፈወስ ነበር» ብሏል (*On Baptism* V)::



የተቀበለ ተራው ሕዝብ ነበር:: እግዚአብሔር በእንዲህ ያለ ሁኔታ ሰውን ሰቀቀን ላይ በሚጥል መንገድ ይሠራል ብሎ ማሰብም ምክንያታዊ አይሆንም:: ይህን ያህል ከባድ ሕመም ያልነበረባቸው ሌሎች ቀድመው ውሃው ውስጥ መግባታቸውና መፈወሳቸው ፍትሐዊ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል:: እግዚአብሔር በእንዲህ ያለ ሁኔታ ይፈውስ እንደ ነበር ሌላ ምሳሌ ማግኘት አይቻልም:: ስለሆነም፣ (1) ቁጥር 3 እና 4 የመጀመሪያው ቅጂ ክፍል መሆናቸውን አለመቀበል ይኖርብናል ማለት ነው፤[33] (2) ዐረፍተ ነገሩ እውነት መሆኑን አለመቀበል ይኖርብናል ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ (3) በኢየሱስ አገልግሎት ዘመን የነበረውን አስተሳሰብ በትክክል የሚገልጽ እንደ ሆነ መቀበል ይኖርብናል ማለት ነው::

መጠመቂያው ቦታ ከነበሩ አካለ ስንኩላን አንዱ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ በበሽታ ሲሰቃይ ነበር:: ይህን ያህል ዓመት ታማሚ እንደ ነበር እንጂ ያን ያህል ጊዜ መጠመቂያው ቦታ ላይ ነበር ብለን ማሰብ የለብንም:: ምንም እንኳ በዚያ የነበሩት ብዙ ሕመምተኞች ቢሆንም፣ ኢየሱስ ግን አንዱን ብቻ በመምረጥ ነበር የፈወሰው:: እጁን በማንቀሳቀስ ብቻ ሁሉንም መፈወስ ይችል ነበር:: ግን አንዱን ብቻ መረጠ:: ለምን? ኢየሱስ ይህን ተአምር ያደረገው በርኅራኄ በመነሣሣቱ ብቻ አልነበረም:: እንዲያውም ሰንበትን አስመልክቶ በሚነሣ አለመግባባት ከሃይማኖት መሪዎቹ ጋር ፊት ለፊት ለመጋጨት የቈረጠ ይመስላል::

**ዮሐ 5÷6-9**

[6]ኢየሱስም ይህን ሰው ተኝቶ ባገኘው ጊዜ፣
ለብዙ ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንዳ ነበር ዐውቆ «ልትድን
ትፈልጋለህ?» አለው:: [7]«ሕመምተኛውም መለሰ፣ «ጌታዬ፣

33 እዚህ ላይ Metzger እና Hodges ላቀረቡት መከራከሪያና ዮሐንስ 5÷3-5 መካተት እንዳለበት ጥናታዊ ምላሽ ከቀረበው G.D Fee ጋር እንስማማለን:: "On the Inauthenticity of John 5:3-4" *EvQ* 54 (Oct 1982): 207-218.

ውሃው በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጠመቂያዴቱ የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፤
ለመግባትም ስሞክር ሌላው ይቀድመኛል» አለው:: 8ኢየሱስም «ተነሥ! መተኛህን
ተሸክመህ ሂድ» አለው:: 9ሰውዬውም ወዲያው ተፈወሰ፤ መተኛውንም ተሸክሞ ሄደ::
ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር::

ቁጥር 6 ላይ ኢየሱስ፣ «ልትድን ትፈልጋለህ?» በማለት ግራ የሚያጋባ ጥያቄ ሲያቀርብ እንመለከታለን:: በመጠመቂያው ቦታ መገኘቱ ይህን ግልጽ ማድረግ ይችላል:: ከሠላሳ ስምንት ዓመት ሕመም በኋላ ጤና ማግኘትን የሚጠላ ማነው? ግራ የሚያጋባ ቢሆንም ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሣ ጤነኛ መሆን የማይፈልጉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: አንዳንዶችም ከዓመታት ሕመም በኋላ ጤነኛ የመሆን ፍላጐታቸው ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል::

የሰውዬው ችግር በጣም ግልጽ ነበር፤ ወደ መጠመቂያው ለመግባት የሚረዳው ሰው አልነበረም:: ሕመም ያልጠናባቸው ሌሎች ቀድመው ወደ ውሃው ይገቡ ነበር፤ ኢየሱስ ግን ይህን ሰው ረዳው:: ይህን ሰው በሰንበት ቀን የፈወሰው ሆን ብሎ ነበር:: ይባስ ብሎም መተኛውን ተሸክሞ እንዲሄድ አዘዘው:: ሰውዬው ምንም ሳይናገር ሄደ፤ እሳቱ ግን መቀጣጠል ጀምሮ ነበር::

ከግርዛትና አመጋገብን በተመለከተ የተሰጡ ደንቦችን ጨምሮ ሰንበትን ማክበር አይሁዳውያንን በዙሪያቸው ከነበሩ ሕዝቦች ሁሉ የተለዩ ያደርጋቸዋል:: ከባሕላቸው ሁሉ ይህ ነቃፊና ተቺ አድርጓቸዋል፤ እነርሱም አጥብቀው ነበር የያዙት:: የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን በሰንበት ቀን እንዲያርፉ እግዚአብሔር የሰጠውን ቀላል ትእዛዝ ደቀ መዛሙርቶቻቸው እንዳይተላለፉ ለመርዳት ሰንበትን በተለያዩ ደንቦችና ሥርዓቶች አጥረውት ነበር:: በዚህ ብዛት ባለው አፈ ታሪክ ውስጥ ፈውስን አስመልክቶ ራሳቸውን የቻሉ ግልጽ ደንቦች ነበሩ:: ሰንበት ቢሆን እንኳ የአንድን ሰው ሕይወት ማዳን ይቻላል፤ ፈውስ ከሆነ ግን



እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ መጠበቅ ነበረበት:: ይህን ሰው ሲፈውስና መተኛውን ተሸክሞ እንዲሄድ ሲያዝዘው ኢየሱስ እያደረገ የነበረውን በሚገባ ያውቅ ነበር:: ሰንበት ስለ ማክበር የአይሁድ ሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች ከሚያቀርቡት መመሪያ ጋር ፊት ለፊት እየተጋጨ ነበር::

### § 49
### በሰንበት መፈወሱን አስመልክቶ የተነሣ አለመግባባት
### (ዮሐ 5÷10-18)

10አይሁድም የተፈወሰውን ሰው፣ «ሰንበት ስለሆነ
መተኛህን እንድትሸከም ሕጉ አይፈቅድልህም» አሉት::
11እርሱ ግን፣ «ያ የፈወሰኝ ሰው፣ መተኛህን
ተሸክመህ ሂድ ብሎኛል» ሲል መለሰላቸው:: 12እነርሱም፣
«መተኛህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ እርሱ ማነው?» ብለው
ጠየቁት::
13ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ወደ ሕዝብ መካከል ገብቶ ስለ ነበር ሰውዬው ማን
እንደ ፈወሰው አላወቀም::

ምንም እንኳ የሰንበት ሕግ (ዘፀ 20÷10) አከራካሪ ቢሆንም፣ ሰውየው ከባድ ሸክም መሸከም እንዳልነበረበት በጣም ግልጽ ነበር (ኤር 17÷19-27፤ ነህ 13÷15):: ይሁን እንጂ በሰንበት ዙሪያ የነበረው ትውፊት «ሸክም» ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ ተዘርዝረው የማያልቁ ብዛት ያላቸው ማብራሪያዎችን ጨምሯል:: አስቂኝ እስከ መሆን ደረጃ ድረስ በጣም ውስብስብ ነበሩ:: (See Edersheim, Appendix 17, II:777.) በተጨማሪም እነዚህ ትውፊቶች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ይህን ያህል ብዛት ያለው ነገር መጨመራቸው ራሱ የሚገርም ነው:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር የሰጠውን ሰንበትን የማክበር ደንብ በፍጹም ተላልፎ የማያውቅ መሆኑ ነው:: ሰንበትን ስለ ማክበር ፈሪሳውያን ያወጡትን ደንብና መመሪያ ግን ብዙ ጊዜ ይገዳደርና ይጻረር ነበር (§ 50,51,110 ጋር ያነ):: አሁን እያየን ባለው ታሪክ ግን ኢየሱስ ያንን ያደረገው ሆን ብሎ በዓላማ ነበር::

የዚያ ምስኪን ሽባ ደስታ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ የፍርሃትና በሌሎች የመገለል ጥላ አጠላበት:: የታዘዘውን ብቻ ነበር ያደረገው:: መተኛውን ተሸክሞ ሲሄድ ፈሪሳውያን ሲያገኙት በጣም ተቆጥተውታል:: ራሱን ከወቀሳ ነጻ ለማድረግ በማሰብ ወቀሳውን መኝታውን ተሸክሞ እንዲሄድ በነገረው ኢየሱስ ላይ አድርጓል:: ከሠላሳ ስምንት ዓመት ሽባነት በኋላ የፈወሳችሁ ሰው አድርጉ ያላችሁን ሁሉ እንደምታደርጉ በጣም ግልጽ ነው! ታሪኩን አሁን ካለንበት አንጻር ስንመለከት ግን በመጠኑም ቢሆን ቅር የሚያሰኝ ነው:: ግን እንዲህ ያለ ከባድ ተቃውሞ ሲገጥመው እንደዚያ የማያደርግ ማነው?

እዚህ ላይ አይሁድ[34] «መተኛህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ እርሱ ማነው?» እንጂ፣ «የፈወሰህ ማነው?» በማለት እንዳልጠየቁት ልብ እንበል:: ተአምሩን መቀበል ወይም ደግሞ ዋጋ መስጠት አልፈለጉም:: የእነርሱ ትኩረት ከባሕላቸው አንዱ የሆነው ሰንበትን ማፍረስ ላይ ነበር:: ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ፈቀቅ ብሎ ስለ ነበር ያ ምስኪን፣ ሰውዬው ይኸውና ብሎ ማሳየት እንኳ አልቻለም (ቁ 13)::

14ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያን ሰው በቤተ መቅደስ
አገኝቶ፣ «እነሆ፣ ተፈውሰሃል፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት
አትሥራ፤ ያስዚያ ከዚህ የባሰ ይደርስብሃል» አለው::
15ሰውዬውም የፈወሰው ኢየሱስ መሆኑን ሄዶ ለአይሁድ
ነገራቸው::

16አይሁድም በሰንበት ቀን እነዚህን ድርጊቶች
በመፈጸሙ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር:: 17ኢየሱስ፣ «አባቴ
እስካሁን እየሠራ ነው፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ»
አላቸው:: 18እንግዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን
አባቱ በማድረጉ፣ ራሱን እግዚአብሔር እኩል በማድረጉ፣ ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉ
ነበር::

ዮሐ 5÷14-18

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘው:: አካለ ስንኩላን በመቅደሱ ውስጥ ምንም ዐይነት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ስለማይፈቀድ ምናልባት ይህ ሰው ወደዚያ ሕንፃ ገብቶ እግዚአብሔርን ሲያመልክ የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል:: ኀጢአት በማድረግ ከቀጠለ ከሽባነት የከፋ ችግር ሊገጥመው እንደሚችል ኢየሱስ አስጠነቀቀው::

ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ሕመም በኀጢአት ምክንያት የሚመጣ እንደ ሆነ ነበር በስፋት የሚታመነው:: ስለሆነም የሰውዬው ሽባነት በፈጸመው ክፉ ተግባር ምክንያት የደረሰበት የእግዚአብሔር ቅጣት እንደ ሆነ ነበር መታሰቡ አይቀርም ነበር:: ሰውየው መንገዱን ካላስተካከለ እግዚአብሔር ከዚያ በሚብስ ሁኔታ ይቀጣዋል:: በመሠረቱ ኢየሱስ እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ መቀበሉ ግልጽ ነው (ዮሐ 9÷1-4 ጋር ያነ):: ታዲያ፣ እንደዚያ ሲል ምን ማለቱ ነበር? «ከዚህ የባሰ» የሚለው ምን ለማለት ነው? የኢየሱስ አባባል ፍርድን የሚያመለክት ነበር ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ ይመስላል:: ከዚህ ምዕራፍ ዐውደ ሐሳብም ጋር ይስማማል (ቁ 27-30):: በሌላ አነጋገር በቅርቡ ያገኘውን ጤንነት ለክፉ ተግባር ከተጠቀመበት ፍጻሜው ገሃነም ይሆናል ማለት ነው:: ከዚያም በላይ የሰውዬው ኀጢአት እንደ ስስት ሁሉ ሥጋዊ ሳይሆን አለማመን መሆኑን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል:: መጀመሪያውኑ ተአምር አልጠበቀም ነበር፤ ኢየሱስ ላይ አሳብቆአል፤ አሁን ደግሞ ለባለሥልጣናቱ አሳልፎ ሊሰጠው የፈለገ ይመስላል::

ምናልባት ይህ ሰው ክፉ ዓላማ እንዳለው ማሰቡ ትክክል ላይሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ «ጥቆማው» ኢየሱስ ላይ ችግር ማስከተል እንደሚችል እንዴት ሳያስብ ቀረ? ምናልባትም ፈዋሹ ማን መሆኑን

[34] እዚህም ላይ ቢሆን ዮሐንስ « አይሁድ» የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት ተቃዋሚ የሃይማኖት መሪዎችን ለመግለጽ ነው፤ (ለምሳሌ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን 1÷19፤ 7÷17፤ 9÷22፤ 18÷12, 14) ከ «አይሁድነት» ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለጽ ካልሆነ በቀር (ለምሳሌ በዓላትና ባሕሎችን)::

እንዲነግራቸው አይሁድ አጥብቀው ይዘውት ይሆናል:: ትክክሉን ማወቅ አንችልም:: ውጤቱ ምን እንደ ነበር ግን ማየት እንችላለን:: ባለ ሥልጣናቱ ሰንበትን በመሻር ኢየሱስን ያሳድዱት ጀመር::

እንደ እውነቱ ቢሆን ኖሮ አንድ ከገሊላ የመጣ የሥራ ሰው በኢየሩሳሌም በነበሩ ባለ ሥልጣናት ተቃውሞ በቀላሉ መሰበር ይችል ነበር:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ፣ «አባቴ እስካሁን እየሠራ ነው፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ» በማለት በድፍረት ነበር ለክሳቸው ምላሽ የሰጠው:: በሌላ አነጋገር፣ «ልጅ በአባቱ ይወጣል» ማለት ነው:: እንዲህ ያለው አነጋገር ደግሞ የበለጠ ቁጣ እንደሚያጭር ግልጽ ነበር::

እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከሥራው ማረፉ እውነት ነበር (ዘፍ 2÷3):: ይሁን እንጂ በእያንዳንዱ ቀን እያንዳንዷ ቅጽበት ሁሉ እግዚአብሔር ፍጥረቱን አጽንቶ መያዙ ይታወቃል:: እንደ አባቱ ሁሉ ኢየሱስም ዘወትር መሥራቱን ይቀጥላል:: በዚህ ጊዜ አይሁድ በጣም ተቆጡ:: ኢየሱስ ባሕላቸውን መተላለፍ ብቻ ሳይሆን በእነርሱ አስተሳሰብ ስድብ የመሰላቸውን ቃል ተናግሮአል:: የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ሲናገር ኢየሱስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል በማድረግ ደረጃ አስቀምጧል:: በመጀመሪያው መቶ ዓመት በነበረው ዓለም ልጅ ከአባቱ ጋር እኩል እንደሆነ አይታሰብም ነበር:: ስለሆነም ኢየሱስ እግዚአብሔር «አባቴ» ነው ማለቱና ከእርሱም ጋር እኩል እንደሆነ መናገሩ ተጠቅሶ የተመሠረተበት ክስ እጥፍ ድርብ ወንጀል ነበር ማለት ነው:: ኢየሱስ በሰጠው የመልስ መልስ (ቁ 19-30) እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን እያደረገ መሆኑን መናገሩ በጣም አስፈላጊ ነጥብ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው::[35] የተናገረውን በትክክል መረዳት ቢችሉም ለደቂቃ ያህል እንኳ እውነት መሆኑን ማመን አልፈለጉም::

[35] James McGrath "A Rebellious Son? Hugo Odeberg and the Interpretation of John 5:18," *NTS* 44/3 (1998): 470-473.



እንዲህ ያለው ስድብ ደግሞ የሚገባው ሞት ነበር:: ስለሆነም ይህንኑ እውን ለማድረግ ለበቀል ተነሣሡ::

**§ 49ሐ**
**የኢየሱስን አምላክነት ሥራ በተመለከተ የቀረበ ስብከት**
**(ዮሐ 5÷19-47)**

ይህ ስብከት አምላክነቱንና ማንነቱን በማሳየት ረገድ ኢየሱስ ካደረጋቸው ስብከቶች ሁሉ በጣም ግልጽ ነው:: ይሁን እንጂ በአይሁድ ፈሊጣዊ አነጋገር ካባ የተሸፋፈነ በመሆኑ በትክክል ለመረዳት እንደ አይሁድ ማሰብ ይጠይቃል:: በዘመኑ የነበረውን የአይሁድ ባሕልና የኢየሱስ አድማጮች የሰጡትን ምላሽ በመገንዘብ እንጂ ቃላቱን በመረዳት ብቻ ትክክለኛ አባባሉን ማግኘት አይቻልም:: ይህም በሦስት ምድቦች ሊከፈል ይችላል፤ (1) በኢየሱስና በእግዚአብሔር አብ መካከል ያለ ንጽጽር (ቁ. 19-23)፤ (2) ለሕይወትና ለፍርድ ትንሣኤ ማግኘት (ቁ 24-30) እና፤ (3) የተለያዩ የኢየሱስ ምስክሮች (ቁ 31-47):

**ዮሐ 5÷19-23**

[19]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት
እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ
ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ
ወልድ ደግሞ ያደርጋልና፤ [20]አብ ወልድን ስለሚወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤
ትደነቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል:: [21]ምክንያቱም አብ ሙታንን
እንደሚያስነሣ፣ ሕይወትንም እንደሚሰጥ፣ ወልድም ደግሞ ለሚፈቅደው ሁሉ
ሕይወትን ይሰጣል:: [22]አብ በማንም ላይ አይፈርድም፤ ነገር ግን ፍርድን ሁሉ ለወልድ
አሳልፎ ሰጥቶታል፤ [23]ይኸውም፣ ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወልድን ያከብሩት ዘንድ
ነው፤ ወልድን የማያከብር፣ የላከውን አብንም አያከብርም::

ከቁጥር 19-23 ያለውን፣ «ልጅ አባቱን ይመስላል» በሚል አንድ ዐረፍተ ነገር ማጠቃለል ይቻላል:: በአራት መንገዶች ኢየሱስና ያህዌ

ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆኑ አንድ ናቸው። ተመሳሳይ «እጆች» (ቁ 19)፣ ተመሳሳይ «ዐይኖች» (ቁ 20)፣ ተመሳሳይ፣ «እስትንፋስ» (ቁ 21) እና ተመሳሳይ «አንደበት» (ቁ 22) አላቸው። በሌላ አነጋገር ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ያደርጋል፤ እግዚአብሔር የሚያየውን ያያል፤ ተመሳሳይ የሕይወት እስትንፋስ አለው፤ ተመሳሳይ የፍርድ ቃል ያሰማል። የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት፣ ሁሉን ዐዋቂነት እንዲሁም ለመፍጠርና ለማጥፋት የሚያስችለውን ኀይል መጋራት ድፈረት ነው። ያም ሆኖ ግን ድፍረት የሚመስለውን የሆነውን አነጋገር የምናገኘው ቁጥር 23 ላይ ነው። ልብ አድርጋችሁ እንደ ገና አንብቡት። በአንድ አምላክ ብቻ አጥብቀው ያምኑ የነበሩት ወገኖች ለአብ እንደሚታዘዙ ሁሉ ለእርሱም መታዘዝ እንደሚገባቸው ኢየሰሱ እየተናገረው ነው። ያንን ካላደረጉም አምልኮአቸው ከንቱ ይሆናል።

ይህ የሚያስከትለው አንድምታ ከፍተኛ ነው! ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ችሎታና ሥልጣን አለው። ይህን አባባል ከተቀበሉ ኢየሱስ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ለማግኘት ለሚያደርገው ጥረት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል ማለት ነው። ወደ እግዚአብሔር አብ ይመራናል (ዮሐ 14÷6)። ከዚህም በላይ ኢየሱስን ችላ የምንል ከሆነ፣ እግዚአብሔር አብን ችላ እያልን ነው ማለት ነው። ይህ ለተቀረው የኢየሱስ ስብከት መድረክ ያዘጋጃል።

[24]እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። [25]እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። [26]አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ ወልድም በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና፤ [27]ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነም እንዲፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል።

ዮሐ 5÷24-30



[28]በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ [29]መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፤ ክፉ የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ። [30]እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤ የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው፣ የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክክል ነው።»

ቁጥር 21-23 ኢየሱስ አሁን እየተናገረ ወዳለው፣ ማለት ወደ ትንሣኤ ያመጣዋል። ኢየሱስ ለሚፈልጉት ሁሉ ሕይወት ይሰጣል፤ በእግዚአብሔር ሥልጣን ይፈርዳል። ስለሆነም ሙታንን ወደ ዘላለም ሕይወት ወይም አስፈሪ ወደ ሆነ ፍርድ ማስነሣት ይችላል።

ብዙ ጊዜ አእምሮአችን ወደ «መጨረሻ ዘመን» ጉዳዮች ያዘነብላል። ከቁጥር 28-30 ባለው መሠረት ይህ መሆኑ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ መንፈሳዊ ሙታን ለሆኑ አሁን እንኳ ኢየሱስ ሕይወት መስጠት እንደሚችል እዚህ ፊት ለፊታችን ያለው እውነት ሊያመልጠን አይገባም። አሁን እንኳ ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገሩ ሰዎች አሉ (ቁ 24)። ይህ ደግሞ ኃላፊና የአሁን ጊዜን እንጂ የወደፊት ጊዜን የሚያመለክት አይደለም። ኢየሱስ ስለ ዘላለም ሕይወት ሲናገር እዚህና አሁን ስለሚሆን ሕይወት መናገሩ ነው። በሌላ አነጋገር ትንሣኤ ቀደም ሲል ተጀምሮአል ማለት ነው። ኢየሱስን የሚሰሙና ሕይወታቸውን ለእርሱ የሚያስረክቡ የዘላለም ሕይወትን ምንነት ተለማምደዋል።

በኢየሱስ ስብከት አማካይነት በመንፈስ ሆነው ሙታን የሆኑት ወደ ሕይወት ይመጣሉ። ሞት የኀጢአት ተምሳሌት ስለ መሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በተደጋጋሚ ይጠቁሙብታል (ኤፌ 2÷1፤ ቆላ 2÷13፤ ራእ 3÷1)። ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው (ቁ 24-25፤ ራእ 20÷4-6 ጋር ያነ)።

በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ስለ ፍርድ ምስል የሚሰጥ ሐሳብ መኖሩ ትኩረት የሚያሻው ነው፤ ሰዎች የሚፈረድባቸው እንደ ሥራቸው አይደለም። በእምነት አማካይነት በጸጋ ድነናል። ይሁን እንጂ

ከሥራ ውጭ እምነትን የምናሳይበት ወይም በሥራ የማይታይ ትክክለኛ ተግባራዊ መንገድ ሊኖር አይችልም (ያዕ 2÷14-26)::

**ዮሐ 5÷31-40**

31እኔ ስለራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ ተቀባይነት
አይኖረውም:: 32ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ አለ፤ እርሱ ስለ
እኔ የሚሰጠውም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ
ዐውቃለሁ::
33ወደ ዮሐንስ ልካችሁ ነበር፤ እርሱም ስለ እውነት መስክሮአል፤ 34እኔ የሰው
ምስክርነት የምቀበል አይደለሁም፤ ይህን የምናገረው ግን እናንተ እንድትድኑ ነው::
35ዮሐንስ እየነደደ ብርሃን የሚሰጥ መብራት ነበረ፤ እናንተም ለጥቂት ጊዜ በብርሃኑ
ደስ ልትሰኙ ወደዳችሁ::
36እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የላቀ ምስክር
አለኝ፤ እንድፈጽመው አብ የሰጠኝ፣ እኔም የምሠራው
ሥራ አብ እንደላከኝ ይመሰክራል:: 37የላከኝ አብ ራሱ ስለ
እኔ መስክሮአል፤ እናንተም ከቶ ድምፁን አልሰማችሁም፤
መልኩንም አላያችሁም፤ 38የላከውንም ስላላመናችሁ ቃሉ በእናንተ አይኖርም::
39በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤
እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ 40እናንተ ግን ሕይወት እንዲኖራችሁ
ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም::»

በዚህ በስብከቱ የመጨረሻ ክፍል ኢየሱስ ስላሉት የተለያዩ ምስክሮች ዝርዝር አቅርቧል፤ እርሱ ራሱ (ቁ 31)፣ እግዚአብሔር አብ (ቁ 32፣ 34፣ 37)፣ መጥምቁ ዮሐንስ (ቁ 33፣ 35-36)፣ የራሱ ሥራ (ቁ 36) እና ቅዱሳት መጻሕፍት (ቁ 39)፣ በተለይም የሙሴ መጻሕፍት ናቸው (ቁ 45-47):: በአይሁድ ባሕል መሠረት ይህ አስፈላጊ ነበር:: በሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ካልተረጋገጠ በቀር ነገር ትክክል ነው አይባልም:: ኢየሱስ ግን ከአምስት ያላነሱ ታማኝ ምስክሮች በማቅረብ ከሚጠበቀው በላይ ርቆ ሄዷል::



በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ራሱ የራሱ ምስክር ነው:: ይሁን እንጂ አይሁድ የኢየሱስን ምስክርነት በተለይም ደግሞ ድጋፍ እስከሌለው ድረስ መቀበል አይፈልጉም:: «እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ ተቀባይነት አይኖረውም» በማለት የተናገረው ስለዚህ ነበር:: አይሁድ በሚገነዘቡት ወይም በሚቀበሉት መልኩ ምስክርነቱ እውነት ሊሆን አይችልም፤ ከዮሐንስ 8÷12-14 የምንመለከተውም ይህንኑ ነው:: ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ስለ ራሱ የሚሰጠው ምስክርነት እውነት ነው (ቁ 19-23):: እርሱ አይዋሽም:: ሊዋሽ አይችልም::

በሁለተኛ ደረጃ፣ እግዚአብሔር አብ ለኢየሱስ መስክሮአል:: ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ከሰማይ ስለ ተሰማው ድምፅና መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ስለ መውረዱ ነው ማለት እንችላለን (ማቴ 3÷17፤ ማር 1÷11፤ ሉቃ 3÷22):: ምናልባትም በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል እግዚአብሔር ስለ ሰጠው ምስክርነት ነው በማለት ልናሰፋውም እንችላለን (ይህ ግን በኋላ ለብቻው የምንመለከተው ይሆናል)::

በሦስተኛ ደረጃ፣ ዮሐንስ የሰጠው ምስክርነት የተሟላና ነገረ መለኮታዊ ይዘቱም «በሳል» ነበር:: አራተኛውን ወንጌል ብቻ እንደ ምስክር ብንወስድ እንኳ ስለ ኢየሱስ በጣም የሚያስገርሙ ግንዛቤዎችን ማግኘት እንችላለን፤ (1) እርሱ፣ ከዮሐንስ እጅግ የሚበልጥና ከእርሱ በፊት የነበረ መሆኑን (1÷27፣30፤ 3÷30)፤ (2) እርሱ፣ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን፣ (1÷29፣36)፤ (3) መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በእርሱ ላይ በመውረዱ መሲሕነቱ በመለኮታዊ ሁኔታ የተመሰከረለት መሆኑን (1÷31-33)፤ (4) እርሱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (1÷34)፤ (5) እርሱ፣ ክርስቶስ መሲሕ ነው (3÷28)፤ (6) እርሱ፣ ከሰማይ ነው (3÷31)፤ (7) የእግዚአብሔርን እውነት ይገልጣል (3÷32-34)፤ (8) ሊሰፈር ወይም ሊለካ በማይቻል ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል (3÷34)፤ (9) በእግዚአብሔር

የተወደደ ነው (3÷35)፤ (10) የእግዚአብሔር ሥልጣን በሙሉ አለው (3÷35)፤ (11) የዘላለም ሕይወት ምንጭ ነው (3÷36):: አብዛኛው ምስክርነት የተሰጠው በሰዶቃውያንና ፈሪሳውያን ፊት ነበር (ዮሐ 1÷19-28):: ከዚያም በላይ በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአይሁድ መሪዎች መካከል ግንኙነት ነበር (ዮሐ 3÷25):: ስለሆነም ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የተናገረውን በሚገባ ያውቃሉ ማለት ነው::

በአራተኛ ደረጃ የኢየሱስ ሥራ ስለ ራሱ ይመሰክራል:: በአንድ ዓመት አገልግሎት ዘመኑ ብቻ ኢየሱስ በይሁዳና (ዮሐ 2÷23) በገሊላ ብዙ ተአምራት አድርጐ ነበር:: ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል፣ መቅደሱን አንጽቷል፣ የሰዎችን ሐሳብ አንብቧል፣ በቅፍርናሆም የሹሙን ልጅ፣ እንዲሁም የጴጥሮስን አማትና ሌሎች ብዙዎችን ፈውሷል:: በእርግጥም የቀረበው ማስረጃ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማመን ከበቂ በላይ ነው::

በአምስተኛ ደረጃ፣ በትንቢት ብቻ ሳይሆን በምሳሌዎችና በጥላዎች አማካይነት (ሉቃ 24÷27፣44) ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ መስክረዋል:: የንጉሥ ጀምስ ትርጉም በመባል የሚታወቀው ነባሩ ትርጉም ቁጥር ዘጠኝን የሚያቀርበው፣ «ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሩ» በሚል ትእዛዝ ሲሆን፣ አቀራረቡ ከሰዋሰው አኳያ ትክክል ቢሆንም ይዘቱ ግን የሚያስኬድ አይሆንም:: «መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ» ከሚለው የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ጋር እንስማማለን:: ዛሬም ቢሆን ብዙዎች በተለይም አጥባቂ ክርስቲያኖች መካከል በእንዲህ ዐይነቱ ብዥታ ውስጥ እየኖሩ ያሉ አሉ:: ዘላለማዊ ሕይወት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ይመስላቸዋል:: ስለሆነም የሚገባውን ያህል ካጠናን መዳንና መቀደስ እንችላለን የሚል አመለካከት ያላቸው ይመስላል:: ድነት ግን በራሱ በጌታ እንጂ በመጽሐፍ አይደለም:: ስለ ኢየሱስ ብዙ የሚያውቁ፣ እርሱ ራሱን ግን የማያውቁ አያሌ ታላላቅ የመጽሐፍ



ቅዱስ ምሑራን አሉ:: ምንጊዜም ቢሆን መጻሕፍት ወደ ኢየሱስ ያመለክታሉ፤ ከዚህ ያለፈ ግን ማድረግ አይችሉም:: ድነት ያገኘነው በኢየሱስ በማመን እንጂ፣ ዕውቀት በማከማቸት አይደለም::

**ዮሐ 5÷41-47**

[41]«እኔ ከሰው ክብር አልቀበልም፤ [42]ነገር ግን
እናንተን ዐውቃችኋለሁ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር በልባችሁ
እንደሌለ ዐውቃለሁ:: [43]እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም
ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ:: [44]እናንተ እርስ በእርሳችሁ ክብር የምትሰጣጡ፣ ነገር ግን
ከአንዱ አምላክ የሚመጣውን ክብር የማትፈልጉ ከሆነ፣ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?
[45]«ከሳሻችሁ ተስፋ የጣላችሁበት ሙሴ እንጂ እኔ
በአብ ፊት የምከሳችሁ አይደለሁም፤ [46]ሙሴን ብታምኑ
ኖሮ እኔን ባመናችሁ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ የጻፈው
ስለ እኔ ነው::[47]እርሱ የጻፈውን ካላመናችሁ፣ እኔ
የምናገረውን እንዴት ታምናላችሁ?»

ይህ ሁሉ ከተባለና ከተደረገ የኢየሱስ ምስክሮች በሙሉ መለኮታዊ ናቸው ማለት ይቻላል:: የሃይማኖት መሪዎቹ ግን አንዱንም እንኳ መቀበል አልፈለጉም:: ኢየሱስ በሰዎች ምስክርነት የሚታመን ቢሆን ኖሮ ብዙ ደጋፊዎች ያገኝ ነበር:: የሚወዱት እንዲህ ያለውን ነገር ነበር (ማቴ 23÷5-7):: ይሁን እንጂ ኢየሱስ የእርሱ የራሱ ስለሆነ ሥልጣን በመናገሩ ፊት ለፊት ተቋቁሟቸዋል::

ፈሪሳውያን በኢየሱስ መታወካቸው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ራሱም በእነርሱ ታውኳል:: ጠንከር ባለ ሁኔታ ገሥጾአቸዋል፤ ተግሣጹ ግን ነገርን ግልጽ ለማድረግ በማሰብ እንጂ በጭካኔ አልነበረም:: ነገሩ እየተካረረ መምጣቱን ዐውቋል:: አንድ ቀን ፍርድ ይኖራል፤ ኢየሱስን ችላ የሚሉ ሁሉ ወደ ገሃነም ይጣላሉ:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ ራሱ ለመከራከር በቁጣ እየተናገረ እንደ ነበር ማሰብ የለብንም፤ እንደዚያ

የተናገረው የእርሱን ድርሻ ግልጽ ለማድረግ ብቻ ነው:: ከሳሻቸው የእኛ ነው የሚሉት ሙሴ እንጂ ኢየሱስ አይደለም:: እንኖርባቸዋለን እያሉ የሚመጻደቁባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት እነርሱ ራሳቸው የሚገድሉ ቃላት ይሆኑባቸዋል::

**§ 50**
**በሰንበት እሸት ስለ መቅጠፍ የተነሣ ክርክር**
**(ማቴ 12÷1-8፤ ማር 2÷23-28፤ ሉቃ 6÷15)**

በዚህና በቀጣዩ ክፍል የምናየው ሰንበትን በተመለከተ የተነሣ ከባድ ክርክር ይሆናል፤ ጉዳዩ በሰንበት እሸት መቅጠፍንና እጁ የሰለለ ሰውን መፈወስ ይመለከታል:: «አዲሱ» የኢየሱስ አሠራር ከ«አሮጌው» የፈሪሳውያን መንገድ የማይስማማ ለመሆኑ አመላካች ምሳሌ ነው (ሉቃ 5÷27-29 ጋር ያነ):: ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን አዲስ መምህር ሆኗል::[36] ስለዚህም በሥልጣን ሕጉን መተርጐም ይችላል::

ሰንበት ለአይሁድ ሃይማኖት ይህን ያህል አንገብጋቢ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሣ ስለ ሰንበት አጠባበቅ ዝርዝር የአይሁድ ሕግ መጽሐፍ የሆነው ታልሙድ በጣም ሰፊ ገለጻ ያቀርባል:: ሚሽና (*Sanh* 7:4) ሰንበት ማፍረስን በድንጋይ መወገርን ከሚያስከትሉ ታላላቅ ወንጀሎች ተርታ አስቀምጦታል:: ስለዚህም መሞትን ከሚያስከትሉ ታላላቅ ወንጀሎች ተርታ አስቀምጦታል:: ስለዚህም ሰንበትን በተመለከተ ፈሪሳውያን የነበራቸውን ልምድ ኢየሱስ ማቃለሉ ይህን ያህል ቢያስቆጣቸው የሚገርም አይሆንም ማለት ነው::[37]

---

[36] F.W. Beare, "The Sabbath Was Made for Men" *JBL* 79 (1960): 130-136 ላይ እነዚህ ታሪኮች ሰንበትን በተመለከተ በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት በቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ የነበረውን አለመግባባት ያንጸባርቃሉ የሚል ገለጻ አቅርቧል (ገላ 4÷10፤ ቈላ 2÷16፤ ሮሜ 14÷5 ጋር ያነ):: ቤተ ክርስቲያን ከምኩራብ ስትለይና ብዙ አሕዛብን ስትቀበል ይህ የሰንበት ጉዳይ ለጥንት አማኞች የተለያዩ ጥያቄዎችን ያስነሣል::

[37] ይሁንና የሰንበት አከባበር ዝርዝር እንደ ነበር ማሰብ የለብንም:: ይህ ጉዳይ በአይሁድ ጽሑፍ ከፍተኛ ክርክር አስነሥቶአል (cf. Book of Jubilees,



ይህ አለመግባባት ለረጅም ጊዜ ሲብላላ የነበረ ነው:: ክርስቶስ ላይ ከቀረበው ክስ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ምን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ መመልከት ይቻላል (1) ስድብ (ሽባውን መፈወሱ፤ ማቴ 9÷1-8)፣ (2) የኀጢአተኞች ወዳጅ መሆኑ (ሌዊ ቤት በነበረው ግብዣ፤ ማቴ 9÷9-13)፣ (3) ጾምን ችላ ማለቱ (በመጾምና አለመጾም ምክንያት በተነሣው አለመግባባት፣ ማቴ 9÷14-17)፣ (4) ሰንበትን አስመልክቶ የተነሣ አለመግባባት (አንካሳውን መፈወሱ፤ ዮሐ 5)::

**ሉቃ 6÷ 1-2**

[1]በአንድ የሰንበት ቀን ኢየሱስ በዕርሻ መካከል ያልፍ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱም (ስለራባቸው[ማቴ]) እሸት ቀጥፈው በእጃቸው እያሹ ይበሉ ነበር:: [2]ከፈሪሳውያን መካከል አንዳንዶቹ ግን፣ «በሰንበት ቀን ሊደረግ ያልተፈቀደውን ለምን ታደርጋላችሁ?» አሏቸው::

**ማር 2÷ 25-26**

[25]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ዳዊት በተራበና የምግብ ፍላጐት በጸናበት ጊዜ አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር ያደረገውን አላነበባችሁምን? [26]በሊቀ ካህናቱ በአብያታር ዘመን ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ፣ ካህናት ብቻ እንዲበሉት የተፈቀደውን የተቀደሰ ኅብስት ራሱ በልቶ አብረውት ለነበሩትም ሰዎች ሰጣቸው::»

**ማቴ 12÷ 5-6**

[5]ወይስ ካህናት ሰንበትን ሽረው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሥራ ቢሠሩ በደለ እንደማይሆንባቸው ከኦሪት ሕግ አላነበባችሁም? [6]ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ከቤተ መቅደስ የሚበልጥ በዚህ አለ::

---

Damascus Document, Mishnah) :: ሰበት በግድ ሕዝብ ላይ የተጫነ እንደ ነበርም ማሰብ የለብንም:: እንዲያውም ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠ ልዩ ስጦታ ነበር የሚቆጠሩት:: Anthony Saldarini, "Comparing the Traditions: New Testament and Rabbinic Literature," *BBR* 7 (1997): 195-204.

ሰንበትን በተመለከተ በኢየሩሳሌም የተነሣው ጭቅጭቅ ከሁለተኛው የኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ፋሲካ (ዮሐ 5) ከተመለሰ በኋላ ወደ ገሊላም ተዛምቶአል:: እሸት የሚደርሰው በሚያዝያ አካባቢ ነበር:: እንግዲህ ሉቃስ 6÷1 የቀረበው ተለዋጭ ዐውድ (*deuteroprote = መጀመሪያ ወር ሁለተኛ ሰንበት*) ትክክል ከሆነ ይህ ስንዴ ከመድረሱ ከአንድ እስከ ሦስት ሳምንት በፊት የሚደርሰው የገብስ እሸት ነበር ማለት ነው::

በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት ከሰዎች እርሻ እሸት ቀጥፎ መብላት የተፈቀደ ነበር (ዘዳ 23÷25):: በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን ውስጥ በሰንበት እሸት ቀጥፎ መብላትን የሚከለክል ምንም ሕግ አልነበረም:: ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ላይ ያቀረቡት ስሞታ ትውፊትን እንጂ በጽሑፍ የሰፈረውን ሕግ መሠረት ያደረገ አልነበረም:: በዚህ ትውፊት መሠረት ደቀ መዛመርቱ ጥቂት በደሎችን ፈጽመዋል:: እሸት በመቅጠፋቸው፣ የማጨድን ያህል በደል ፈጽመዋል፤ እሸቱን በእጃቸው በማሸታቸው፣ እህል የመውቃትን ያህል በደል ፈጽመዋል (ዘፀ 34÷21 ጋር ያነ)::

ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርቱን የከሰሳቸው በቃል ሲተላለፍ የኖረውን ሕግ ባለ ማክበራቸው ነበር:: ኢየሱስ ደግሞ በጽሑፍ በሰፈረው ሕግ መሠረት ያደረጉት ትክክል እንደ ነበር ያመለክታል:: በአብያታር ዘመን ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ለካህናት ብቻ የተፈቀደውን ገጸ ኅብስት በልተው ነበር (1ሳሙ 21÷1-6 ጋር ያነ)::[38]

[38] ዳዊት በኖብ ያገኘው ካህን አብያታር እንዳልነበረ ግልጽ ነው:: አባቱ አቢሜሌክን ነበር ያገኘው:: ያም ቢሆን ኢየሱስ «በአብያታር ዘመን» እንጂ፣ አብያታር ሊቀ ካህናት በነበረበት ዘመን አላለም:: ይህ ሁኔታ በሚፈጸምበት ጊዜ አብያታር በሕይወት መኖር ብቻ ሳይሆን በቦታውም ነበር:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳኦል በኖብ የነበሩ ካህናትን በሙሉ ሲገድል፣ በሕይወት የተረፈውና ወደ ዳዊት ሸሽቶ የመጣው አብያታር ብቻ ነበር:: በኋላ ላይ ዳዊት ሊቀካህናት አድርጎ መሾሙ ይህን ያህል የሚያስገርም አይሆንም::



«አላነበባችሁም?» የሚለው ጠንከር ያለ የኢየሱስ አነጋገር ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በቃል ሲተላለፍ ለኖረው ሕግ ቅድሚያ መስጠታቸውን የሚያመለክት ነው:: በጽሑፍ የሰፈረውን ቃል በሚገባ ያውቃሉ:: ይሁን እንጂ ከዐላማው ሺህ ጊዜ ሺህ ክንድ ያህል ርቀዋል::

ይህን የተቀደሰ ገጸ ኅብስት መብላት የሚፈቀድላቸው ካህናት ብቻ ነበሩ (ዘሌ 24÷5-9):: ዳዊትና አብረውት የነበሩት ግን ምንም የበደለኝነት ስሜት ሳያድርባቸው እንደዚያ አድርገዋል:: ለምን? ምክንያቱም፣ (1) ችግር ላይ ነበሩ፤ ይህ ደግሞ ከሃይማኖታዊ ሥርዓት ይበልጣል፤ (2) በዳዊት መሪነት የእግዚአብሔርን ሥራ እየሠሩ ነበር:: ስለዚህም ሕጉ ከሚያስቀምጠው ገደብ በማለፍ እንኳ ቢሆን ማንኛውም የእግዚአብሔር በሆነ ነገር የመጠቀም መብት ነበራቸው:: በምሳሌያዊ መልኩ ኢየሱስ የዳዊት ፍጻሜ ነበር:: ስለሆነም ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር በሆነ ነገር ሁሉ ላይ የመጠቀም መብት ነበራቸው::

በኢየሱስና በዳዊት መካከል ያለው ንጽጽር ሰብዕናቸውን እንጂ ሥራቸውን የተመለከተ አይደለም:: ኢየሱስ የዳዊት ሥርወ መንግሥት ፍጻሜ ነው:: በእነዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ፊት ኢየሱስ እንዲህ ያለ ንጽጽር ማቅረቡ ከፍተኛ ድፍረት ነበር::

በሁለተኛ ደረጃ ካህናቱ በሰንበት ቀን መቅደስ ውስጥ ተግባራቸውን ሲፈጽሙ በሌላ በኩል እንዲያርፉ የተሰጠውን ሕግ እያፈረሱ ነበር:: የሰንበት መሥዋዕት የሚጠይቀው ደምና ሥራ ለሌሎች ሰዎች ሕግን እንደ መተላለፍ ይቈጠርባቸው ነበር፤ ለካህናቱ ግን ሰንበትን እንደ መሻር እንደማይቈጠርባቸው ግልጽ ነው:: የዚህም ምክንያት ከመቅደሱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እያገለገለ ስለ ነበር ነው:: ኢየሱስ ደግሞ ከመቅደሱ የበለጠ፣ ከዚያም በላይ፣ ከራሱ ከዳዊት እንኳ የበለጠ ነበር (ማቴ 22÷41-45 ጋር ያነ):: ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን

እያገለገሉ ስለ ነበር እጥፍ ድርብ በሆነ ሁኔታ ከበደል ነጻ ናቸው ማለት ነው::[39]

ማቴ 12÷7

[7]ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ
የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ ብታውቁ ኖሮ፣
በንጹሐን ላይ ባልፈረዳችሁ ነበር::

ማር 2÷27-28

[27]ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ «ሰንበት ለሰው
ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም፤ [28]ስለዚህ
የሰው ልጅ ለሰንበት ጌታዋ ነው::»

ሰንበትን በተመለከተ ኢየሱስ ሦስት መደምደሚያ ሐሳቦችን አቅርቧል፤

(1) ከሆሴዕ 6÷6 የተወሰደው ጥቅስ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች መካከል እግዚአብሔር ቅድሚያ የሚሰጠውን በድጋሚ ያቀርባል:: ሕግና ደንብን ከማክበር ይልቅ እግዚአብሔር ይበልጥ ደስ የሚሰኘው ፍቅርና ምሕረት በማድረግ ነው፤

(2) ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሰንበት በረከት እንጂ ሸክም ሊሆንባቸው አይገባም:: ሰንበት ሁለት ዐላማዎች አሉት፤ ዕረፍትና አምልኮ:: ዕረፍት ለአካል አስፈላጊ ነው፤ ዋናው ዐላማው ግን ለአምልኮ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት ነው:: የፈሪሳውያን ሰንበት አከባበር መንገድ ግን ሁለቱንም አያሟላም::

(3) ከዮሐንስ በቀር ሦስቱም ወንጌሎች ኢየሱስ ሰንበት ላይ ባለ ሥልጣን መሆኑን በጉልህ አመልክተዋል:: ሕግን የመስጠትም ሆነ የመተርጐም ሥልጣን አለው፤ እንዲያውም ሰንበታችን እርሱ ነው (ዕብ 4):: ከዚሁ ጋር አብሮ ሰንበትን በተመለከተ

[39] ከትንሹ ወደ ትልቁ በማምራት ኢየሱስ በአይሁድ ዘንድ ተቀባይነት በነበረው ነገረ አመክንዩ መጠቀሙ ነበር:: (*qal wa- homer*) ይሁን እንጂ Rabbi D.M. Cohn – Sherbok ኢየሱስ ሥነ አመክንዮ በዘመኑ በነበሩ የአይሁድ ሕግ መምህራን ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል በዚህ መጣጥፍ ምክንያት አቅርቧል ("An Analysis of Jesus' Arguments Concerning the Plucking of Grain on the Sabbath," *JSNT* 2 [1979]: 31-41.



የተነሡ እነዚህ ሁለት አለመግባባቶች፣ «እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ» ከሚለው ከማቴዎስ 11÷28-30 ሥር ያስቀመጠው ፋይዳ የሚሰጠው ጉዳይ ይመስላል::

ከዚህ በመነሣት ሁለት ተጨማሪ መደምደሚያዎች ላይ መድረስ ይቻላል::

(4) የሰዎች ባሕል ከእግዚአብሔር ቃል በልጠው መታየት የለባቸውም:: ብዙ ጊዜ ግን ሃይማኖተኞች የሰዎችን ሃይማኖታዊ ወግ ለመደገፍ የእግዚአብሔርን ቃል ሲጠቀሙበት ይታያል:: እንዲህ ስናደርግ ግን የሕጉን መንፈስ በሕጉ ፊደል እየተጋፋን ነው ማለት ነው::

(5) ኢየሱስ 1ሳሙኤል 22ን ጠቅሶ መናገሩ በተወሰነ መልኩም ቢሆን አስተምህሮን ለማጽናት ታሪካዊ ሐቅን መጠቀም እንደሚቻል ምሳሌ ሊሆን ይችላል::[40] ትክክለኛ ምክንያታዊነትን መሠረት ያደረገ እስከሆነ ድረስ ታሪካዊ እውነት ለወቅቱ ሥነ ምግባርና የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንደ መመሪያ ማገልገል ይችላል::

**§ 51**
**በሰንበት እጁን ያሰለለውን በመፈወሱ የተነሣ አለመግባባት**
**(ማቴ 12÷9-14፤ ማር 3÷1-6፤ ሉቃ 6÷6-11)**

እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የተፈጸሙት በአንድ ሰንበት ውስጥ አለመሆኑን የሚነግረን ሉቃስ ብቻ (6÷6) ነው:: ካለፈው ታሪክ እንደተመለከትነው ደቀ መዛሙርቱ ካደረጉት የተነሣ ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር ተከራክረው ነበር:: ከሁለተኛው ታሪክ የምንመለከተው ግን እጁ የሰለለውን ሰው መሐል በማቆም አለመግባባት እንዲኖር ምክንያት የሆነው ኢየሱስ

[40] J.M. Hicks, "The Sabbath Controversy in Matthew: An Exegesis of Mattthew 12:1-14," *RestQ* 27/2 (1984): 79-91.

ራሱ ነበር (ሉቃ 6÷8)። ይህም በሰንበት ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባት ወደ አዲስ ደረጃ ያሸጋግረዋል። ሰንበት የተሠራው ለሰዎች ጥቅም መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሰንበት ለሌሎች መልካም ነገር የምናደርግበት አጋጣሚ ሊሆነን ይገባል።

ሉቃ 6÷6-8
ማቴ 12÷10 ጋር

[6]በሌላ ሰንበት ቀንም ወደ ምኵራቡ ገብቶ
ያስተምር ነበር፤ በዚያም ቀን እጁ የሰለለ አንድ ሰው
ነበረ። [7]ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ሲከሱት («በሰንበት ቀን
መፈወስ ተፈቅዶአል»? ብለው ጠየቁት[ማቴ]) ምክንያት በመፈለግ፣ ይፈውሰው እንደ ሆነ
ለማየት ይጠባበቁት ነበር። [8]ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እጁ የሰለለውን ሰው፣
«ተነሥተህ በመካከል ቁም» አለው፤ ሰውየውም ተነሥቶ ቆመ።

በሰንበት መፈወስን በተመለከተ በቃል ይተላለፍ የነበረው ሕግ ያለው ደንብና መመሪያ ግልጽ ነበር። ሕይወትን ለማዳን መድኃኒት መስጠት ይቻላል፤ ከዚህ ማለፍ ግን አይቻልም። አንድ ሰው አዳልጦት ቢወድቅና ጭንቅላቱ ቢጐዳ ደሙን ማቆም ይቻላል፤ የተሰበረ እግር መጠገን ግን አይፈቀድም። እጀ ሰላላነት ሕይወትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ባለመሆኑ ይህን ሰው በሰንበት መፈወስ እንደ ሕገ ወጥነት ታይቷል። ኢየሱስ ግን የልባቸውን ሐሳብ ዐውቆ በራሳቸው መከራከሪያ ፊት ለፊት ተጋፈጣቸው። ጀሮም የተባለው የጥንት አዋቂ ይህን ክፍል በተመለከተ አስተያየት ሲሰጥ ይህ ሰው ግንበኛ ሳይሆን እንዳልቀረ አመልክቷል። ስለሆነም ለኑሮ የሚያስፈልገውን እንዳያገኝ ችግር ገጥሞታል። ከተፈወሰ በኋላ እንኳ ቢሆን እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ መሥራት አይችልም። በፈሪሳውያን አመለካከት ኢየሱስ ሕግን ተላልፎአል።

ማር 3÷4-5

[4]ኢየሱስም፣ «በሰንበት ቀን የተፈቀደው
መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት ማዳን ነውን
ወይስ ማጥፋት?» አላቸው። እነርሱ ግን ዝም አሉ።
[5]በልባቸው ደንዳናነት አዝኖ በዙሪያው የቆሙትን በቁጣ
ተመለከታቸውና ...



ማቴ 12÷11-12

[11]እርሱም፣ «ከእናንተ መካከል የአንዱ ሰው በግ
በሰንበት ቀን ጉድጓድ ቢገባበት በጉን ከገባበት ጉድጓድ
ጐትቶ አያወጣውምን? ስለዚህ በሰንበት ቀን በጎ ማድረግ
ተፈቅዶአል» አላቸው።

ኢየሱስ ላቀረበው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነበር። ሃይማኖታዊ ቀናተኛነትና ነገረ መለኮታዊ አመለካከትን ለመደገፍ የሚደረግ ሙከራ ግን ዐይኖቻቸውን አሳውሯል። በዚህ ኢየሱስ በጣም ተቆጥቶ ነበር። ብዙ ጊዜ ግን ሲቆጣ አንመለከትም። ሰዎች ባሕልና ወጋቸውን ከሰብዓዊ ፍጡር በላይ አድርገው ሲመለከቱ ሲያይ ግን መቆጣቱ ይታወቅ ነበር። በቁጣ እየነደዱ የነበሩ የኢየሱስ ዐይኖች ወደ ጥልቅ ነፍሶቻቸው ዘልቀው ሲገቡ ምንኛ በድንጋጤ አንገታቸው ተሰብሮ ይሆን። ቁጣን ጨምሮ ኢየሱስ ማንኛውም ዐይነት ሰብዓዊ ስሜት ነበረው (ክፍል 123 ይመ)።[41] እዚህ ላይ ቁጣው ፈሪሳውያን ላይ ያነጣጠረ ነበር፤ መቅደሱን ባነጻ ጊዜ ሰዱቃውያን ላይ፣ ሕፃናት ወደ እርሱ እንዳይመጡ በተከለከሉ ጊዜ ደግሞ የገዛ ደቀ መዛሙርቱ ላይ ተቆጥቷል (ክፍል 123)። የምንቆጣው ለጽድቅ ተቆርቁረን ሲሆን ይችላል፤ ይህም ቢሆን ቁጣችን ጽድቅን መሠረት ያደረገና ትክክለኛ «ዐላማ» ላይ ያረፈ መሆን ይኖርበታል።

ለጥያቄው መልስ ስላልሰጡት እርሱ ራሱ መልሱን ሰጠ። ከትውልድ ትውልድ በቃል ሲተላለፍ የኖረው ሕግ በሰንበት ቀን ገደል የሚወድቁ እንስሳትን ማዳን እንደሚገባ ይቀበላል (*b Sabb.* 128b)። እዚህም ላይ ኢየሱስ ከታናሹ ወደ ታላቁ የሚሸጋገርን የአይሁድ ሥነ አመክንዮ ተከትሏል። የሰው ልጅ ከእንስሳ ይልቅ ዋጋ አለው። ስለሆነም በሰንበት ቀን ሕይወታቸውን ከማዳን አልፎ ለሰዎች መልካም ነገር

---

[41] Cf. W. Hanson, "The Emotions of Jesus," *CT* (February 3, 1997): 43-46.

ማድረግም ሕጋዊ ነበር ማለት ነው። ኢየሱስ ግን እዚህም ላይ አላበቃም፤ ሰንበት ለሌሎች መልካም ነገር የምናደርግበት አጋጣሚ ብቻም አይደለም፤ ሰዎች ችግር ላይ መሆናቸውን እያየን ምንም አለማድረግ ከነፍስ ገዳይነት ያልተናነሰ ወንጀል ነው (ማር 3÷4)።

ማቴ 12÷13
[13]ከዚያም ሰውየውን፥ «እጅህን ዘርጋ» አለው፤
ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እንደ ሌላኛውም እጁ ደህና
ሆነለት።

ማር 3÷6
ሉቃ 6÷11 ጋር
[6]ፈሪሳውያንም (በቁጣ ተሞሉ[ሉቃ]) እንዴት
ሊያጠፉት እንደሚችሉ ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር
መመካከር ጀመሩ።

ሰውየው የተፈወሰው እጁን ሲዘረጋ ይመስላል። ሌላው ቀርቶ ለረጅም ጊዜ በድን ሆነው የነበሩ የጡንቻ ሕዋሶቹ እንኳ ተፈውሰው ነበር። እንደ ሌላው እጁ ሁሉ ጤነኛ ሆኖለት ነበር። ይህን ሲመለከቱ ፈሪሳውያን በጣም ተቆጥተው ሥራ ጀመሩ። ሉቃስ የተጠቀመው ማስተዋል የጐደለው ቁጣ በሚያሳይ ቃል ነው። እንዴት አድርገው ኢየሱስን እንደሚገድሉ ለመጀመሪያ ጊዜ መመካከር ያዙ። በጣም እንግዳ የሆነው ደግሞ ከሄሮድስ ወገኖች ጋር መተባበራቸው ነበር። የእነዚህን ወገኖች ማንነት በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፤ ፖለቲካዊ አሰላለፋቸው ከሄሮድስ ጋር የወገነ መሆኑ ግን ምንም ጥርጥር የለበትም። ይህ ደግሞ ከፈሪሳውያን ጋር የማያስማማቸው ጉዳይ ነበር። እስከምናውቀው ድረስ እነዚህ ሁለት ወገኖች ስምምነት ሲያደርጉ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው።



## § 52 ከአደጋ መሸሹና ባሕሩ ዳርቻ የተሰበሰቡ ብዙ ሰዎች (ማቴ 12÷15-21፤ ማር 3÷7-12)

[ማር3:]7ኢየሱስም (ሐሳባቸውን ዐውቆ[ማቴ]) ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ወደ ባሕሩ ሄደ፤ ከገሊላ የመጣ እጅግ
ብዙ ሕዝብም ተከተለው፤ [8]የሚሠራውን ነገር የሰሙ
ሰዎችም ከይሁዳ፥ ከኢየሩሳሌም፥ ከኤዶምያስ፥ በዮርዳኖስ
ማዶ ካለው አገር እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና አካባቢ
ወደ እርሱ መጡ። [9]የተሰበሰበውም ሕዝብ እንዳያጨናንቀው
አነስተኛ የሆነ ጀልባ እንዲያዘጋጁለት ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው። [10]ብዙዎችን ፈውሶ
ስለ ነበር፥ በሕመም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊዳስሱት ይሽቀዳደሙ ነበር። [11]ርኩሳን
መናፍስትም ባዩት ቁጥር ከፊቱ እየወደቁ፥ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!» በማለት
ይጮኹ ነበር። [12]እርሱ ግን ማንነቱን እንዳይገልጹ አጥብቆ ይገሥጻቸው ነበር።

የውጊያው መስመር በማያሻማ ሁኔታ ተሰምሯል። እጁ የሰለለውን ሰው በሰንበት ቀን ከፈወሰ ወዲህ ፈሪሳውያን ከሄሮድስ ወገኖች ጋር በመተባበር ኢየሱስን ለመግደል እየመከሩ ነበር። ኢየሱስ ግን በቀላሉ ለአደጋ መጋለጥ ከሚችልበት ከተማ ወጥቶ ሄደ። የገሊላ ባሕር የስብከት ሥራውን ለመቀጠል በጣም አመቺ ቦታ ነበር። ሕዝቡ እየወደደው መጥቷል፤ በእንዲህ ዓይነቱ የአደባባይ ስብሰባ ደግሞ በአድማ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን በቀላለ ማየት ይቻላል፤ ድንገት ገፍተው ቢመጡ እንኳ በጀልባ ሆኖ ባሕሩ አካባቢ ወደ ነበሩ ሌሎች ቦታዎች መሄድ ይቻላል።

የኢየሱስ በሽተኞችን መፈወስና አጋንንትን ማስወጣት ወሬ እየሰፋ በመሄድ ወደ እርሱ የሚመጡ ሰዎችም ብዛት እየጨመረ ሄዷል። ይጠበቅ እንደ ነበረው ሰዎች ያልመጡት ከሰማርያ ብቻ ነበር። አካላቸው የተጣመመና የታመመ ሰዎችን እየተሸከሙ ከየአቅጣጫው (ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው) ወደ ኢየሱስ ያመጡ ነበር። ወደ ኢየሱስ ሲመጡ እርሱን ለማግኘት ግፊያ ውስጥ መግባት ነበረባቸው። ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ የተፈጠረው መጨናነቅ ለእርሱም ሆነ ለሌሎች

አደገኛ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር::[42] ስለሆነም ኢየሱስ በሕዝቡ እንዳይጨናነቅ ጀልባ ላይ ሆኖ ማስተማር ጀመረ::

| ስፍራው | ወንጌሉ | ርቀቱ (በኪ.ሜ) | አቅጣጫው |
|---|---|---|---|
| ሶሪያ | ማቴ | 60 | ሰሜን |
| ገሊላ | ማቴ፣ ማር | 20 (በግምት) | ደቡብ ምሥራቅ |
| ዐሥር ከተሞች | ማቴ | 60 | ደቡብ ምሥራቅ |
| የዮርደኖስ ማዶ አገሮች | ማቴ፣ ማር | 30-90 | ደቡብ |
| ኢየሩሳሌም | ማቴ፣ማር፣ሉቃ | 75 | ደቡብ |
| ይሁዳ | ማቴ፣ማር፣ሉቃ | 65-90 | ደቡብ |
| ኤዶምያስ | ማር | 100-120 | ሰሜን ምዕራብ |
| ጢሮስ | ማር፣ሉቃ | 40 | ሰሜን ምዕራብ |
| ሲዶና | ሉቃ | 60 | ሰሜን ምዕራብ |

አጋንንቱ ልዕለ ተፈጥሯዊ ዕውቀት ስለ ነበራቸው፣ ኢየሱስ ማን መሆኑን ዐውቀው ነበር:: ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ ኢየሱስ ስለ ማንነቱ እንዳይናገሩ ከለከላቸው (ከማር 1÷34፣43-45 ጋር ያነ)፤ (1) ከሁሉም ይልቅ የበለጠው ምስክርነት ከአጋንንት እንዲመጣ ባለመፈለጉ፤ (2) ሕዝቡ ስለ እርሱ ማንነት ለመስማት ዝግጁ ስላልነበሩ፤ እምነታቸው ገና በእንጭጭ ደረጃ መሆኑ፤ (3) ሕዝቡ በከፍተኛ ስሜት ተነሣስተው ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ስለ ነበር:: ኢየሱስ ተጨማሪ ታዋቂነትን አለመፈለጉ፤ (4) በኢየሱስ ላይ የነበረው ጥላቻና ተቃውሞ ይበልጥ መቀጣጠል ስላልነበረበት::

[42] ማርቆስ ቃል በቃል በሆነ ትርጉም፣ «ሊወድቁበት ነበር» የሚል ሥዕላዊ ገለጸ ተጠቅሟል::



ማቴ 12÷17-21

17ይህም የሆነው በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ
ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፤ 18እነሆ
የመረጥሁት፣ የምወደውና በእርሱ ደስ የሚለኝ አገልጋዬ፣
መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ለአሕዛብ ፍትሕን ያውጃል::
19አይጨቃጨቅም ወይም አይጮኽም፤ ድምፁም በአደባባይ አይሰማም:: 20ፍትሕን
ለድል እስኪያበቃ ድረስ፣ የተቀጠቀጠውን ሸምበቆ አይሰብርም፤ የሚጤሰውንም የጧፍ
ክር አያጠፋም:: 21አሕዛብ በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ::

ይህ በማቴዎስ ወንጌል የሚገኝ በጣም ረጅሙ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ከማሶሬቲክ ቅጂ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታም አለ:: መዝሙሩ በኢሳይያስ 42÷1-4 መሠረት ብዙ መከራ ከደረሰበት አገልጋይ የመጣ ነው:: ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ይህን ዐይነት መለኮታዊ ማረጋገጫ ሰምተን ነበር (ማቴ 3÷17):: የመሲሑን አገልግሎት በተመለከተ የቀረበው ገለጻ የኢየሱስን ጨዋነት ይበልጥ ያጕላዋል:: ፈውስ ፍለጋ ለሚያጨናንቁት ሰዎች ጨዋ ነበር:: አካላዊ ችግራቸውን ርኅራኄ በሞላበት ሁኔታ አገለገለ:: ሌላው ቀርቶ ለሚቃወሙት ፈሪሳውያን እንኳ ጨዋ ነበር:: ኢየሱስ የነበረውን ታዋቂነት ተጠቅሞ ዐመፅ ከማነሣት ይልቅ ሕዝቡም ሆነ አጋንንቱ ፀጥ እንዲሉ አደረገ::

ይህ ጥቅስ መሲሑን አስመልክቶ አይሁድ ከነበራቸው አስተሳሰብ ጋር የሚነጻጸር ሁለት ንጽጽሮችን ይዟል:: የመጀመሪያው ጨዋ መሆኑ ነው:: እነርሱ እንደ ጠበቁት ዐመፅን ወይም ሁከትን የሚያነሣሣ አይሆንም:: በሰይፍ ሳይሆን፣ በሰላም ፍትሕ ያሰፍናል:: «ድምፁም በአደባባይ አይሰማም» ሲል ኢየሱስ ኀጢአትን አያወግዝም ማለት አይደለም (ከማቴ 12÷25-45 ጋር ያነ):: እንዲህ ሲባል ኢየሱስ ራሱን አይክብም (ወይም ለራሱ ለመከላከል) ሽብር አያስነሣም ማለት ነው::

በሁለተኛ ደረጃ፣ የዓለም ሁሉ አዳኝ እንጂ፣ የአንድ ሕዝብ ብቻ ጀግና አይሆንም:: አሕዛብም ጭምር ስሙን ይጠራሉ:: የኋላ ኋላ ወደ

መሲሑ ከሚመጡት አንጻር በዚያ ጊዜ የነበረው ብዛት ያለው ሕዝብ እንኳ እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም::

**§ 53**
**የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥ**
**(ማር 3÷13-19፤ ሉቃ 6÷12-16፤ ማቴ 10÷2-4 ሐሥ 1÷13 ጋር ያነ)**

[ሉቃ 6:]12ከእነዚያም ቀናት በአንዱ ኢየሱስ ሲጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ:: 13ሲነጋም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ከእነርሱ ዐሥራ ሁለቱን መረጠ፤ እነዚህንም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤

[ማር 3:]14ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ 15አጋንንትን እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው::

ምንም እንኳ ትዕይንቱ በአምስት ቁጥሮች ብቻ የተካተተ ቢሆንም፣ በኢየሱስ የአገልግሎት ወቅት ከነበሩት እጅግ ዋነኛ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነበር:: በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣም ሌሊቱን ሁሉ ሲጸልይበት አድሯል:: ጥርት ባለ አእምሮ እንዲህ ያለውን ከባድ ውሳኔ ማድረግ እንዲቻል ሌሊቱን በጥሩ እንቅልፍ ማሳለፍ ተገቢ መሆኑን እንስማማ ይሆናል:: ኢየሱስ ግን ይህንንም ሆነ ሌሎች ውሳኔዎችን ያደረገው በጸሎት ነበር::

ኢየሱስ ይከተሉት ከነበሩ ብዛት ያላቸው ሰዎች መካከል ይበልጥ ጊዜውን ከእነርሱ ጋር ለማሳለፍ የመረጠው ዐሥራ ሁለት ብቻ ነበር:: አሁንም ቢሆን ሕዝቡን እያስተማረ ነበር፤ ይሁን እንጂ ዕቅዱንም ሆነ ባሕርዩን በግል ለዐሥራ ሁለቱ ያካፍል ነበር:: ዝናውና ታዋቂነቱ በገነነበት ጊዜ እንኳ ኢየሱስ ዓለምን በወንጌል መገለባበጥ የሚቻለው ሰፋ ያለ ጊዜ ጥቂቶች ላይ በማጥፋት እንደ ሆነ ይገነዘብ ነበር:: አመርቂ ውጤቱም ታይቷል:: ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ዐሥራ አንዱ በክርስቶስ የማዕዘን ድንጋይነት የምትሠራው ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሆነዋል:: (ኤፌ 2÷19-20)::



በአዲስ ኪዳን (አፓስቶሎስ፣ (*apostolos*) የሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች አሉት::[43] በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ፣ «ለዐላማ የተላከ» ማለት ነው:: በተጨማሪም የተላከው ሰው የላኪው ሥልጣን ይኖረዋል:: ስለሆነም እነዚህ የተመረጡ መልእክተኞች የክርስቶስ ዐይነት ሥልጣን ይኖራቸዋል ማለት ነው:: እዚህ ላይ በተለይ እየተነጋገርን ያለነው የቤተ ክርስቲያን መሠረት ስለሆኑት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ነው:: የመንግሥትን ወንጌል በተለይም ኢየሱስ ከሄደ በኋላ መስበክ የእነርሱ ሥራ ነበር:: የእርሱን ንጉሥነት እንዲያውጁ በኢየሱስ ሥልጣን ወደ ዓለም ሁሉ ተልከዋል:: የተለየ ኀይል ይኖራቸው ዘንድ ኢየሱስ አጋንንትን የማስወጣትና በሽተኞችን የመፈወስ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል (ማቴ 10÷1፤ ሐሥ 1÷8):: ኢየሱስ ራሱ ለአገልግሎት የተላከ ስለ ነበር ሐዋርያ መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ይረዳል (ዕብ 3÷1)::

**ማር 3÷16-19**

16የሾማቸውም ዐሥራ ሁለቱ እነዚህ ናቸው፤ ጴጥሮስ ብሎ የጠራው ስምዖን፣ 17ቦአኔርጌስ ይኸውም፣ የነጐድጓድ ልጆች ብሎ የጠራቸው የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፤ 18እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣ በርተሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ተቃናቃኙ ስምዖን፣ 19እንዲሁም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ::

የሐዋርያቱ ስም ዝርዝር አራት ጊዜ ቀርቧል (ማቴ 10÷2-4፤ ማር 3÷16-19፤ ሉቃ 6÷14-16፤ ሐሥ1÷13):: እያንዳንዱ ዝርዝር ስሞቹን በተለያየ ቅደም ተከተል አቅርቧል:: ሦስቱ ክፍሎች የሚጀምሩት በጴጥሮስ፣ በፊልጶስና በያዕቆብ ነው:: ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ ከአንድ በላይ ስም እንደ ነበራቸው ማወቅ አለብን:: ስምዖን፣

---

[43] ለቀረቡት ማብራሪያዎች ሁሉ፣ F.H. Agnew, "The Origin of the N.T. Apostle-Concept: A Review of Research," *JBL* 105/1 (1986):75-96 ይመ::

ጴጥሮስ[44] በመባልም ይጠራል፤ ይሁዳ፣ ልብድዮስና ታዴዎስ ተብሎ ይጠራል፤ በርቶሎሜዎስ፣ ዮሐንስ 1 ላይ የተጠቀሰው ናትናኤል ሊሆን ይችላል፤ ቶማስ (አራማይክ) ዲዲሞስ (ግሪክ) ተብሎም ተጠርቷል፤ የሁለቱም ትርጉም፣ «መንታ» ማለት ነው።

ከዚህም በላይ ከሐዋርያት ጥቂቶቹ እርስ በርስ፣ ምናልባትም ከኢየሱስ ጭምር የተዛመዱ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታም ይኖራል። ማቴዎስ 27÷56፤ ማርቆስ 15÷40 እና ዮሐንስ 19÷25 በማነጻጸር ስንመለከት የዘብዴዎስ ልጆች የሆኑት ያዕቆብና ዮሐንስ የኢየሱስ አክስት ልጆች መሆን የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን እናያለን። የኋለኛው ያዕቆብ፣ ስምዖንና ይሁዳ ወንድማማች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ይታሰባል። በዮሴፍ ወንድም በኩል የኢየሱስ አጐት ልጆች መሆን የሚችሉበት ሁኔታም አለ (cf. Edersheim I:522)።

እስከ ሞት ድረስ ለኢየሱስ ታማኝ ያልነበረ ሐዋርያ የአስቆሮቱ ይሁዳ ብቻ ነው። ምናልባትም ከገሊላ ያልመጣ ብቸኛ ሐዋርያ ሳይሆን አልቀረም። ቂርያት የተባለው የትውልድ ቦታው የሚገኘው በይሁዳ ነበር (ኢያሱ 15÷25)።[45] ምንጊዜም ቢሆን ስሙ የሚጠቀሰው ከዝርዝሩ በስተ

[44] C. Roth, "Simon – Peter," *HTR* 54 (1961): 91-97 ላይ እንደሚለው፣ በመጀመሪያው መቶ ዓመት፣ «ስምዖን» የተሰኘው ስም የማይፈለግ እንደነበር አመልክቷል። «ስምዖን» ይባሉ የነበሩ የዘመኑ ዝነኛ ሰዎችን ከዘረዘረ በኋላ ሁሉም ይታወቁ የነበሩት በሌሎች ስሞቻቸው እንደ ነበር ይናገራል። ከዚህም በላይ የዚህ ዐይነቱ ሁኔታ የሚታየው፣ «ስምዖን» በተሰኘው ስም ብቻ ነበር። እኚሁ ሰው እንደሚሉት፣ «ስምዖን» የተሰኘው ስያሜ እንዲህ ያለ ክብር ሊሰጠው የቻለው፣ ምናልባት ሰውን ሁሉ በዚህ ስም መጥራት ተገቢ ስላልሆነ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ስለሆነም ኢየሱስ የስምዖንን ስም ጴጥሮስ ወደሚለው የለወጠበት ምክንያት ባሕላዊ እንጂ ነገረ መለኮታዊ አልነበረም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል።

[45] የትውልድ ቦታው፣ «ቂርያት» የተወሰደው፣ «አስቆሮቱ» ከተሰኘው ስሙ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ «አስቆሮቱ» ማለት፣ «የሚያቀልም» ማለት እንጂ «ቂርያት» ማለት እንዳልሆነ A. Ehrman ሥርወ ቃላዊ መረጃዎችን አቅረበዋል። ("Judas Iscariat and Abba Saqqara" *JBL* 97 (1978): 572-573, and C.C. Torrey ደግሞ «አስቆሮቱ» የሚለው፣ «ሳቃር» (Saqqar) ከተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል ጋር የተያያዘ ስላቃዊ መጠሪያ ሲሆን፣ ትርጉሙ



መጨረሻ ነው፤ ሁሌም ኢየሱስን አሳልፎ እንደ ሰጠ ይነገራል። ዐላማው ምን እንደ ነበር ምስጢር ነው። ወንጌሎች እንደሚያመለክቱት፣ ችግሩ ራስ ወዳድነት ብቻ ነበር ቢባል የሚበቃ ይመስለናል (ዮሐ 12÷4-6፤ ማቴ 26÷14-15)።

## የተራራው ስብከት

ይህ እስከ ዛሬ ከተሰበኩ ስብከቶች ሁሉ የላቀው ነው። በብዙዎችም ዘንድ በስፋት የሚጠቀስ ነው። በዚህ ስብከት ውስጥ የኢየሱስን ትምህርት ዋነኛ ገጽታ በአጭሩ እንመለከታለን፤ ትምህርቱ ሥር ነቀል፣ ጥልቅ ስሜትን የሚነካ፣ መንፈሳዊና ግብዝነትን በመቃወም ረገድም ብርቱ ነው። ለሚቀበለው ሁሉ የመድረክ ላይ ብርሃን ነው። የሚሰማውን ሰው ልብ ሁሉ ሰንጥቆ ያልፋል። ፈተና ላይ የወደቅነው እኛ እንጂ ይህ ትምህርት አለመሆኑን ባለመገንዘብ ከዐውዱ ነጥለን ልናወጣው እንሞክራለን።

ወደ ምንባቡ ከመግባታችን በፊት ጠቅላላ ስብከቱን በተመለከተ ሁለት ጥያቄዎችን ማቅረብ ይኖርብናል። የመጀመሪያው፣ ይህን ስብከት እንዴት መቀበል እንደሚገባን ነው፤ ሁለተኛው፣ ማቴዎስም ሆነ ሉቃስ የወሰዱት ከአንድ ምንጭ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት መረዳት እንደሚኖርብን ነው።

## የተራራውን ስብከት እንዴት መቀበል ይገባል?

አንዳንድ የተራራው ስብከት ትምህርቶች በጣም ከባድ ከመሆናቸው የተነሣ፣ እንዴት እንደምናስተናግዳቸው ሊያዳግተን ይችላል። ለመገንዘብ ቀላል ናቸው፤ ሆኖም ተግባር ላይ ማዋል ግን

«ሐሰተኛ» ማለት ነው የሚል ሐሳብ አቅርበዋል። ("The Name Iscariot," *HTR* 36 [1993]: 51-62).

አስጨናቂ ነው:: ይህ አስቸጋሪ ሁኔታ ሰዎች ስብከቱን በተለያዩ መንገዶች እንዲመለከቱ ምክንያት ሆኖአቸዋል::[46]

**(1)** የሽግግር ወቅት ሥነ ምግባራዊ መመሪያ (Albert Schweitzer Johannes Weiss) - አንዳንዶች ኢየሱስ፣ «የዘመን ፍጻሜ» እንደ ደረሰ ያስብ እንደ ነበር አመልክተዋል:: ስለዚህም ሥር ነቀልና ለውጥ አምጪ ሥነ ምግባራዊ መመሪያ እንደሚያስፈልግ አስቧል:: የታቀደው በጊዜያዊነት እንዲያገለግል ቢሆንም፣ በእንዲህ ያለ አስቸጋሪ ወቅት ግን ከምንም ይለቅ የተሻለ ነው:: እንደ ተባለው የዓለም ፍጻሜ ባለመሆኑ የሽግግር ለውጥ ሥነ ምግባራዊ መመሪያነቱ ተግባራዊ መሆን አልቻለም:: የተጠየቁት ምግባሮች ምክንያታዊም፣ በዚህ ባለንበት ዓለም ተግባር ላይ መዋል የሚችሉም አይደሉም:: ይህ አመለካከት ግን ሁለት ችግሮች አሉበት:: በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ተሳስቶ ነበር ብለን እንድናስብ ብቻ ሳይሆን፣ ያቀረበው ሥነ ምግባራዊ መመሪያ በጊዜው ለነበረው ችግር አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ላይ የተመሠረተ ነበር እንድንል ያደርገናል:: ሁለተኛ፣ በዚህ ስብከት ውስጥ አንድም ቦታ ሥነ ምግባራዊ መመሪያው ጊዜያዊ መሆኑን ወይም ለተወሰነ ዘመን ብቻ የሚያገለግል መሆኑን የሚያመለክት ምንም ፍንጭ ማግኘት አለመቻሉ ነው::

**(2)** Existential (Demythological) Approach – ይህ አመለካከት ኢየሱስ እነዚህን ቃላት የተናገረው (በእርግጥ የእርሱ ከሆኑ) የተወሰነ ሥነ ምግባራዊ መመሪያ ለመቅረጽ በማሰብ አልነበረም ይላል::

---

[46] D.Crump "Applying the Sermon on the Mount: Once You Have Read It What Do You Do With It," *CTR* 61 (1992): 3-14. አንዳንድ ጥልቅ ጥያቄዎችን ያቀርባል፤ ለጥያቄዎቹ የምንሰጠው መልስ ለዚህ ስብከት ያለንን አመለካከት ይወስናል:: ስብከቱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት «መግቢያ መስፈርት» ነውን? ስብከቱ ከጸጋና ሕግ ጋር ያለው ግንኙት ምንድነው? ስብከቱ ለዘመነ ክርስትና ወይም ለኃላፊም ሆነ የወደፊት ጊዜ ጠቀሜታ ያለው ነውን? ስብከቱ የቀረበው ለአማኞች ብቻ ነው ወይስ ለሰፊው ማኅበረሰብ? በተጨማሪ W.D. Davies and D.C. Allison, "Reflections on the Sermon on the Mount," *SJT* 44 (1991): 283-309.



ይልቁንም «መሆን በነበረበት» እና «ነገሮች አሁን ባሉበት» ደረጃ መካከል አንድ ዐይነት ንጽጽር በአማኙ ውስጥ ለማኖር ነበር:: ይህ ንጽጽር ራስን ወደ መመርመር ያደርሳል፤ ግለሰቡንም ወደ ንስሐና ግብረ ገባዊ ተሐድሶ ይመራል:: ስለሆነም የስብከቱ ዋጋ ያለው በአስተምህሮአዊ ይዘቱ ሳይሆን፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ በሚያስገኘው ለውጥ ነው ማለት ነው:: የዚህ አመለካከት ችግር ሰብከቱ በራሱ ያለውን ጠቀሜታ መካዱና ግለሰቡ የፈለገውን ዐይነት ሥነ ምግባራዊ ደንብ እንዲከተል መፍቀዱ ነው:: የስብከቱን ታሪካዊ ፋይዳ በማቃለል ረገድ የሚያመጣው ጥፋት ከፍ ያለ ነው::

ለዐውዱ ተአማኒነት ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጡ ሁለት ተመሳሳይ አመለካከቶችም ይኖራሉ:: አጠቃላይ መርሕ የተሰኘውን አመለካከት የሚያራምደው ምልከታ ኢየሱስ የተናገረው ለተወሰኑ ድርጊቶች ሳይሆን ሰፋት ላላቸው ሁኔታዎች መመሪያ እንዲሆን ነበር ይላል:: ከተግባር ይልቅ ዝንባሌ ላይ የሚያተኩረው ሁለተኛው ምልከታ ደግሞ ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው ስለ ተግባር/ምግባር ሳይሆን ከምግባሩ በስተጀርባ ስላለው ዝንባሌ ነበር:: ሁለቱም አቋሞች ተመሳሳይ ደካማ ጐን አላቸው፤ በመስፈርቱ መሠረት መኖር አለመቻልን ሰበብ በማድረግ የስብከቱን ኀይል ያቃልላሉ:: ይሁን እንጂ ተገቢ በሆነ ሁኔታ ከተቀበልነው የኢየሱስ ትምህርት ሰዎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ያበረታዋል::

**(3)** ሕገኛ አመለካከት - ይህ አመለካከት የተራራው ስብከትን የሚያቀርበው የእግዚአብሔር መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ሰነድ እንደሆነ አድርጎ ነው:: በግልም ይሁን በኅብረት ክርስቲያኖች ሊኖሩበት የሚገባ፣ «አዲስ ሕግ» ይደነግጋል:: እዚህ ላይ አንዳንዶች በጳውሎስ (ጸጋ) እና በኢየሱስ (ሕግ) መካከል እንኳ አለመጣጣም መኖሩን ተመልክተዋል:: ይህ አመለካከት ቀጣይ ወይም እያደገ የሚሄድ መገለጥን በተገቢው ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም:: ኢየሱስ

ከሕግ በታች ለነበሩ አይሁድ እንደ አንድ አይሁዳዊ አስተማረ:: እንዲህ ሲባል ግን ኢየሱስ ሕግን አልፎ አልሄደም ማለት አይደለም:: ግብረ ገባዊነትን፣ ጦርነትን፣ ፖለቲካን፣ ሕግን፣ ወዘተ በተመለከተ የተራራው ስብከት የመጨረሻው አሳሪ ቃል ሊሆን አይችልም ማለት ነው::

ከዚሁ የሚመሳሰል ሌላው አቀራረብ ደግሞ ቃል በቃል ወይም ፍጹማዊ ሲሆን፣ ሰዎች ሁሉ ለእያንዳንዱ ትእዛዝ መገዛት ይኖርባቸዋል የሚል ነው:: አውጉስጢኖስን፣ የአሲሲው ፍራንሲስንና ሊዮ ቶልስቶይን የመሳሰሉ ሰዎች ከሞላ ጐደል ይህን አቋም ደግፈዋል:: ይህን አቋም የያዙ ሁሉ የኢየሱስን ትምህርት ከልባቸው ቢቀበሉም፣ ከሚገባው በላይ ወጥረውት አስቂኝ ከዚያም አልፎ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሊከታቸው ይችላል (ከማቴ 5÷29 ጋር ያነ):: ስለሆነም አንዳንዶች ቃል በቃል መወሰድ አለበት የሚለውን አቋም ቢቀበሉም፣ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ክፍሎችን በተመለከተ፣ «ማምለጫ ቀዳዳ» (ለዘብተኛ አቋም) አድርገዋል:: አጠቃላይ በሆነ መልኩ እንዲህ ያለውን ተገቢ ግንዛቤ መሠረት ያደረገ ማብራሪያ መከተል ሊበረታታ የሚገባው ነው:: ይሁን እንጂ ከባሕላዊ አመለካከታችን ጋር እንዲጣጣም በማሰብ ከትክክለኛው የኢየሱስ ዐላማ እንዳንዘናጋ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል::

(4) ለወንጌል የሚያዘጋጅ መሆኑ (የሉተር አቋም) - ስብከቱ በጣም ከባድ የሆኑ መስፈርቶችን በማቅረብ ሰዎች ኀጢአተኛ መሆናቸውን እንዲገነዘቡና የክርስቶስ ቤዛነት ሥራ እንደሚያስፈልጋቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው:: ስለሆነም ሰዎች ኢየሱስን እንደ አዳኝ ይቀበሉ ዘንድ ያዘጋጃል:: ይሁን እንጂ የዚህ አቋም ችግር ዐውዱን በማብራራት ረገድ ፍትሐዊነት የጐደለው መሆኑ ነው:: ስብከቱ የተሰጠበት ዐላማ እንድንታዘዘው እንጂ በደለኞች መሆናችንን እንድንገነዘብ ብቻ አለመሆኑን ሌላው ቀርቶ ላይ ላዩን ያነበበ እንኳ በቀላሉ መገንዘብ ይችላል::



ሌላው ተመሳሳይ አመለካከት ደግሞ አስደንጋጭ ሁኔታን በመፍጠር ኢየሱስ የአድማጮቹን ትኩረት ለመሳብ የተጠቀመበት ግነት ነው ይላል:: ስለሆነም መለኪያ መስፈርቱን ባለንበት ደረጃ ላላ እንዲል ማድረግ ይቻላል ይላል:: እዚህም ላይ ቢሆን ችግሩ ከላይ እንዳለው ለዘብተኛ አቋም፣ ለእኛ እስኪመጥነን ድረስ የኢየሱስን ትምህርት ዝቅ ማድረግ ይቻላል ማለቱ ነው::


(5) አፈንጋጭ ምልከታ - አንዳንዶች እንደሚሉት የሰው ልጅ ሥልጣኔን ማዳን የሚችለው በዚህ ስብከት አማካይነት ነው:: ይህ ምግባራዊ መስፈርት (መስቀሉ ሳይሆን) የእግዚአብሔርን መንግሥት በመመሥረት ረገድ ቁልፍ ነው:: ይህ አመለካከት ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች በፊትና ከዚያ በኋላ በስድሳዎቹ ዓመታት ተቀባይነት ነበረው:: ሐቅን ያላገናዘበ ተስፈኝነቱም በኀጢአት የወደቀውን የሰውን ባሕርይ እንዲክድና የሰው ልጅ በሂደት መልካምና ለሌሎች ራሱን መሠዋት የሚችል እንደሆነ ያቀርባል:: ይህ ዐይነቱ ተምኔታዊነት ማራኪ ቢሆንም፣ ከእውነታው በጣም ያፈነገጠ ነው::

(6) መስተዳደራዊ ምልከታ (Darby and Scofield) - ይህ አመለካከት እንደሚለው ኢየሱስ የሺህ ዓመቱን መንግሥት መተዳደሪያ ደንብ እየዘረዘረ ነበር:: አይሁድ ኢየሱስን እንደ መሲሕ መቀበል ባለመፈለጋቸው እግዚአብሔር ስጦታውን ለወደፊት አድርጓል:: ስለሆነም ኢየሱስ ለሺህ ዓመት በዚህ ምድር በሚመሠርተው መንግሥት (ራእ 20÷1-6) ክርስቲያኖች የዚህ ዐይነት ሕይወት ይኖራቸዋል:: በአሁኑ ጊዜ ግን የሚደረስበት ወይም ተግባር ላይ መዋል የሚችል አይደለም:: ጥቂቶቹ ሥነ ምግባራዊ መመሪያዎች ግን አሁንም ቢሆን ይመለከቱናል:: ሆኖም አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስንመለከተው ግን ወደፊት የሚሆነው ነገር ቅምሻ ናቸው:: መስተዳድራዊው ምልከታ ቀድሞውኑ የተያዘ ግምታዊ አስተሳሰብንና ነገረ መለኮታዊ አመለካከትን


በዚህ ስብከት ላይ መጫን ይሞክራል:: ሆኖም ከዐውዱ ለምንመለከተው ሐሳብ ፍትሐዊነት የሌለው መሆኑን መመልከት ይቻላል::

(7) ትምህርተ ክርስቶሳዊ ምልከታ - በዚህ ስብከት መሠረት መኖር የቻለ ወይም የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው:: ስለሆነም የእግዚብሔር መንግሥት መተዳደሪያ ደንብ ነው ከማለት ይልቅ፣ የክርስቶስን ሕይወት የሚያንጸባርቅ ነው ማለቱ ይሻላል:: ይህ ግሩም ግንዛቤ ነው:: ሆኖም የክርስቶስን ባሕርይ መለማመድ የምንችልበትን መንገድ አያመለክተንም:: ከላይ የተመለከትናቸው ሰባት አመለካከቶች አንዳቸውም እንኳ የተሟሉ ካልሆኑ፣ የተራራው ስብከትን እንዴት መመልከት ነው የሚኖርብን? ቀጥሎ ያሉትን መመሪያዎች አቅርበናል::

(1) ***ለቤተ ክርስቲያን ጥሪ ያቀርባል::*** የሚናገረው በእግዚአብሔር መንግሥት ቋንቋ ነው:: ክርስቲያን ሊኖርበት የሚገባ መመሪያ ነው (ማቴ 7÷24፣26 ):: ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እውነትን ችላ ከሚሉ ከዚህ ዓለም ሰዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት መርኅ በመሆን ሊያገለግል ይችላል (ማቴ 5÷11-12)::



(2) ***ወደ መንግሥተ ሰማይ ያመለክታል::*** የተሰጠው በሕግ አስተዳደር ዘመን ቢሆንም፣ ፍጻሜውንም ግምት ውስጥ አስገብቷል:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥነ ምግባር ለሁሉም ዘመን ያገለግል ዘንድ ወደ ምድር ለማምጣት የተደረገ ሙከራ ነው:: ከዚህም በላይ፣ የመንግሥቱ ዜጎች በመለወጥ ሂደት ላይ ናቸው፤ ያም ክርስቶስን ወደ መምሰል ደረጃ እያደጉ ነው:: ሂደቱ የሚያበቃው ዘላለም ውስጥ ነው:: እስከዚያው ግን የክርስቲያኖች ግብረ ገባዊ አቋምን በተመለከተ አስቸኳይ ጥሪ ያቀርባል::





(3) ***ነፍስን ዘልቆ ይወጋል::*** የሰውን ልብና ዝንባሌ ያልፋል:: እንዲህም ሲባል ጸባይን በማሻሻልና በመስፈርቱ መሠረት በመኖር ሳይወሰን ወደ ጥልቅ ሁለንተናችን ይዘልቃል ማለት ነው:: ኢየሱስ የሚፈልገው የሥነ ምግባር አርበኛን ሳይሆን፣ በእርግጥ የተለወጠ ሰውን ነው::

(4) ***የመስቀሉን ውጤት ይጠብቃል::*** ኢየሱስ የተናገራቸው ቃላት መሆን ባለበትና አሁን ባለው ሁኔታ መካከል አለመጣጣም እንዲኖር አድርጓል:: ምንም እንኳ ለዚህ አለመጣጣም የሚገባው ዋጋ መስቀል ላይ ቢከፈልም፣ የመስቀሉ ሥራ ብቻ ችግሩን አይፈታውም:: እንዲህም ሲባል፣ ክርስቲያን በተቻለው መጠን መሆን በነበረበትና አሁን ባለው ሁኔታ መካከል ያለውን አለመጣጣም በማጥበብ ግበረገባዊ ጥራት ያለው ሕይወት ይኖር ዘንድ ጥሪ እያቀረበለት ነው ማለት ነው::

(5) ***ሐቅን ማገናዘብ ይጠይቃል::*** ይህ ስብከት ሥር ነቀል ነው፤ በአንዳንድ መልኩም ግነት የሚታይበት ነው:: ምንም እንኳ ዓላማው መቀስቀስ ቢሆንም፣ መብራራት ያለበትም በዚህ ግንዛቤ መሠረት ቢሆንም፣ መልእክቱን ማለሳለስም ሆነ ገሸሽ ማድረግ አንችልም:: የእኛ ዋነኛ ግብ መሆን ያለበት የኢየሱስን ትምህርትና ከእኛ የሚጠብቀውን ተረድተን በዚያው መሠረት መኖር ብቻ ነው::

(6) ***የኢየሱስን ምስል ያቀርባል::*** ስብከቱ የኢየሱስ ባሕርይና ምግባር ምን እንደሚመስል በመጠኑም ቢሆን ግንዛቤ ያስጨብጣል:: በእርግጥም የራሱ የክርስቶስ ነፀብራቅ ነው ቢባልም ያስኬዳል:: በዚህ ትምህርት መሠረት የኖረ እርሱ ብቻ ነው:: ስለዚህም የተራራው ስብከት እውነተኛ ይዘት እርሱ ራሱ ነው::